# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 204 መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


pepsi



የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት

ልዩ ዕትም



# ለዓባይ የተዘረጉ ለጋስ እጆች

ሄለን ወንድምነው
ዜና ሀተታ

ዓባይ ወንዝ በኢትዮጵያውን የቁጭት፣ የእንጉርጉሮና የወቀሳ ዜማ ሆኖ ኖሯል:: ማደሪያ ቢስነቱም የሊቃውንትና ጠቢባን ርዕሰ ጉዳይ ነበር:: የዓባይ ውሃ መጠጥ ሆኖ እንዲጠጣ፣ መና ሆኖ እንዲጎረስ፣ ሲሳይ ሆኖ እንዲቆረስ፣ ለጨለማ ብርሃን እንዲሆን የእልፍ ኢትዮጵያውያን ምኞት ነበር::

በትችትና ምኞት የተነገረውን የዓባይ ወንዝ ግንድ ይዞ ዟሪነት ታሪክ ለመግታት፣ የልጅ ባዕድነቱን ለማክተም፣ የማደሪያ ቢስነት ትርክቱንም ለማስቆም፣ ለጨለማ ብርሃን እንዲሆንና የኢትዮጵያውያንን ህልም እውን ለማድረግ የዓባይ ግድብ ግንባታ በወርሀ መጋቢት 2003 ዓ.ም

ለዓባይ የተዘረጉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ለ13 ዓመታት ቦንድ የገዙት ጡረተኛ

ገጽ 4



ፎቶ - ዳኜ አበራ

### "ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁማ ዓላማዋን ማሳካት እንደምትችል በዓባይ ፕሮጀክት አሳይታለች"

- አቶ ሞቱማ መቃሳ
የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር አማካሪ

ገጽ 4

# ዓባይ ግድብን እየተቃወሙ በዓባይ ግድብ ሌላ ወንዝ የመገንባት ተቃርኖ

አዲሱ ገረመው

ግብጽ በግዙፍነቱ ከዓለም አንደኛ ሊሆን የሚችል ሰው ሰራሽ ወንዝ ለመስራት እቅድ ይዛ ወደ ተግባር ገብታለች:: ትልቁ ሰው ሰራሽ የግብጽ ወንዝ ውሃ ለማግኘት እንደምንጭነት ከሚጠቀማቸው የውሃ አካላት የዓባይ ወንዝ ዋነኛው ስለመሆኑም ተገልጿል:: ለመሆኑ የግብጽ ሰው ሰራሽ ወንዝ የመስራት እውነታ የዓባይ ወንዝና ግድብ ላይ ካላት አቋም አንጻር እንዴት ማየት ይቻላል?

በዓባይ ውሃ ፖለቲካ ላይ ሰፊ ጥናት ያደረገው ሃጋይ ኤርሊክ፤ የኢትዮጵያና ግብጽ ግንኙነት ከጥንት ጀምሮ ከውሃ ጋር የተሳሰረ ነው ይላል:: በጥንት ዘመናት በተነሱ የተፋሰሱ ኃያላንም ሆነ የመካከለኛው ምሥራቅ ኃይሎችና

ዓባይ ግድብን .. ወደ ገጽ 10 ዞሯል



ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory




Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት

ልዩ እትም

# ለዓባይ የተፈጸመ
# የፅዳት ሠራተኞቹ ገድል

**ዳግማዊት ግርማ**
**ዜና ሐተታ**

በዓለም ረጅሙ ወንዝ ነው። የመርዘሙን ያህል ለዘመናት ሳይከበር ኖሯል። በልኩ የተሰፋ ስራ አልነበረውም። ዓባይ የማበል ምልክት ተደርጎ ለዘመናት ተተርኮበታል። ማደሪያ የሌለው ግንድ ይዞ ዟሪም ተብሎ ያውቃል። በመኖር ዘመኑ ከሀገሩ በላይ ለጎረቤት ሀገራት አድልቷል። በርሀብና ችግር የተጠቁ ወገኖቹን ትቶ እነሱን አጉርሷል። እነዚያን ሀገራት የጠቀመውን ያህል ለሀገሩ ሊሆን አልተቻለውም ነበር።

ከመኖር ብዛት ሳይሆን ከስራው ጥልቀት ታይቶ አንቱ የሚባልበት ጊዜ ደረሰ። ከዘመናት ሳይጠቅሙ ኑሮ በኋላ ግን መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ቀን ወጣለት። ግንባታው ከተጀመረም 13 መጋቢቶች አልፈው ዘንድሮ 13ኛው ላይ እንገኛለን። ጅማሮው ለኢትዮጵያውያኑ የክፍለዘመኑ ትልቁ ዜና ነበር። አሁን ትልቋን ኢትዮጵያን ያለ ዓባይ ማሰብ የማይቻልበት ዘመን ተወልዷል። ብዙ ህልሞች በእርሱ ትራስነት ታልመዋል።

ጭስ ያሞጨሞጨው አይናቸው በግድቡ እንደሚታከም ተስፋ የጣሉ እናቶች ብዙ ናቸው። እንደ ኢትዮጵያ ላሉቱ ሀገራት እንደ ዓባይ ያለ ትልቅ ተቋም አንድምታው ሰፊ ነው። የዓባይ ግድብ በራስ አቅም በሁለት እግር የመቆም ምልክት ነው። ግድቡ የአልበገር ባይነት ምሳሌ ዳግማዊ ዓድዋ ሆኗል።

ዓባይ የዘመናት የቁጭት ውላጅ ነው። ጥርሱን ነክሶ የሀገርን በሀገር ባዩ በዛ። ገንቢዎቹ 24 ሰዓታትን ሳይታክቱ ሲገነቡ ይውላሉ። መድከም በእነሱ ዘንድ አይታሰብም። ባለሀብቱ በገንዘቡ ድሀ አደጉ በጉልበቱ ተሰማራ። እልፍ መቀነቶች ተፈቱለት። ገንዘብ ሀብት ንብረቱን ያለመሰሰት የሰጠው ብዙ ነው።

የየካ ክፍለ ከተማ እናቶችም በዚህ ጉዳይ ላይ ባለገድል ናቸው። የክፍለ ከተማው ሰራተኞች በበጎ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል። ለመስጠት መሰጠት እንደሚያስፈልገው ሕያው ምስክር ናቸው። ከሚሰጣቸው ሶፍትና ሳሙና ላይም ለተጎዱ ሴቶችም እጃቸው ይዘረጋል።

የመልካምነት እጃቸው ወደ ግድቡም ተዘርግቷል። ከዓመታት በፊት ነበር፤ በቢሮ ፅዳት ስራ የሚተዳደሩት ከ90 የሚልቁ ሰራተኞች ለግድቡ አለን አሉ። ደሞዛቸው ከእጅ ወደአፍ ነው፤ ግን አልሳሱላትም፤ ከዛሬ ችግራቸው ለነገው ትውልድ መልካም መሆን ላይ በረቱ።

ለግድቡ ይዘው የሚሄዱት እጅ መንሻ ባይኖራቸውም ማድረግ አልችልም ብለው ግን የፈለጉትን ከማድረግ ወደኋላ አላሉም። እናም መስጠት የሻተ ልባቸው አርፎ ሊቀመጥ አልተቻለውም። ሰራተኞቹ በዓመት አንዴ የሚሰጣቸውን ሁለት ጥንድ ጫማ ለበጎ ተግባር አሰቧት። በጥቅማ ጥቅም መልክ የሚሰጣቸው ጫማ ላይ ታሪክ ጻፉበት። እነዚህ ቆራጦች ለእግራችን አንዱ ጥንድ ይበቃናል አሉ። የሌላኛውን ሂሳብ ግን ለዓባይ ግድብ ስጦታ አበረከቱ።

ከዚህ ታሪክ ተጋሪዎች መካከል አንዷ ወይዘሮ ታደሰች ሞገስ ይባላሉ። በክፍለ ከተማው የሕንፃ አስተዳደር ባለሙያ ናቸው። ለልጆቻቸው የተሻለ ነገር ማውረስ ይሻሉና ለግድቡ አደረጉት።

ለሳቸው ይህን አደረግኩ ተብሎ የማይወራ ትንሽ ነገር ነው። ካላቸው ሳይሰስቱ ሰጥተዋልና አልነፈጉም። በስራቸው ትውልዱን ዋጅተዋል። ቀጣይ ስለሚመጣው በማሰብ የዛሬ ችግራቸውን ዘንግተዋል። ሀገር ከዛሬ የተሻለ ነገ እንዲኖራት የራሳቸውን ጠጠር ወርውረዋል። ባልጠቀማቸው ገቢ ታሪክ መፃፍ በልጠዋቸዋል። ከእለት እንጀራቸው ይልቅ የመረጡት ለልጅ ልጆቻቸው መልካም ታሪክ ለማቆየት መሆኑን ይጠቅሳሉ። የሀሳቡም አስተባባሪ ናቸው። ሀሳባቸውንም መሰረት በማድረግ ከዘጠና የሚልቁ ሠራተኞች ተጋርተዋቸዋል።



ዓባይ በወይዘሮዋ ቤት ውስጥ ባለትልቅ ስም ነው። ወይዘሮዋ በግድቡ ተስፋቸው ሙሉ ነው። ሲጠናቀቅ ሕይወት የተሻለ መልክ እንደሚኖራት ያምናሉ። ለዚያም ነው የራሳቸውን አሻራ ለማሳረፍ ደፋ ብለው ያቀኑት። እኛ ዋጋ ከፍለን ቀጣይ ትውልድ የተሻለ ሕይወት ሊኖሩ ይገባቸዋል ባይ ናቸው።

እንደ እናትነታቸው ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። የኢትዮጵያኑ ርብርብ ታሪክ መስራቱን ቀጥሏል። ስጦታውን የሰጡት ከልጆቻቸው ጉርስ ነጥለው ነው። በየልጆቻቸው ትምህርት ቤት ውስጥ የቦንድ መዋጮም ያዋጣሉ።

ሌላኛዋ የድጋፉ አስተባባሪ ሕይወት መኮንን ትባላለች። የወር ገቢዋ ከአንድ ሺህ ትንሽ ፈቀቅ ያለ ነው። ታዲያ ይህ ገንዘብ ፍላጎቶቿን ለማሟላት ይሰንፋል። ቢሆንም እሷም ከጫማ ጥቅማጥቅሟ ገሚሱን ለግድቡ ለግሳለች። ባላት በጥቂቷ ገቢዋ ለሀገሯ ያላትን ፍቅርና ታማኝነት አስመስክራለች።

የተሻለ ኢትዮጵያን ለማምጣት ግድቡ የማይተካ ሚና እንደሚኖረው ታምናለች። ዓባይ ለትውልድ የምናስረክበው ተስፋ በሌለበት ተስፋን ያሰነቀን ነው ትላለች። ግድቡ ገጠር ላሉ እህቶች ትልቅ ተስፋ ነው። በርካታ እህቶችን በኩበት ጭስ ከመሰቃየት ይታደጋል፤ እየታደገም ነው።

እነ ሕይወት ለግድቡ አበርክቶ ቀጣይነት ያለው መሆኑንም አስረድተዋል። ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅም ቦታው ተገኝቶ የመጎብኘት ትልም አላቸው።

## "የግድቡ መጠናቀቅ በኃይል እጥረት ወደኋላ የቀሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያንሰራሩ ያደርጋል"

**- አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ**
**የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ**

**ስምስም መንግስቱ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ በኃይል አቅርቦት ላይ ያለውን ችግር በመፍታት ወደኋላ የቀሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያንሰራሩና እንዲጠናከሩ እንደሚያደርግ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። የኃይል አቅርቦት ውስንነት ከፍተኛ የሰው ኃይል መያዝ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ዕድል እንዳይፈጥሩ ሲያደርግ መቆየቱም ተገልጿል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፣ አምራች ኢንዱስትሪው ተግዳሮቶቹ የተለያዩ ቢሆኑም በቂ የሆነ የኃይል አቅርቦት አለመኖር፣ የኃይል መቆራረጥና መዋዠቅ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፡፡ እነዚህ ችግሮች ደግሞ ኢንዱስትሪዎቹ በበቂ ሁኔታ ማምረት እንዳይችሉ አድርጓቸዋል፤ አሁን ላይ የግድቡ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ መድረስ ግን ችግሮቹን ለመፍታት ትልቅ አቅም ነው፡፡

በቂና አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት ቢያገኙ የማስፋፋት ሥራ በመሥራት ምርታቸውን በእጥፍ ለማሳደግ የተዘጋጁ አምራች ኢንዱስትሪዎች አሉ ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ የኃይል አቅርቦት ውስንነት ከፍተኛ የሰው ኃይል መያዝ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ዕድል እንዳይፈጥሩ ሲያደርግ ቆይቷል ብለዋል፡፡

የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ በኃይል አቅርቦት ላይ ያለውን ችግር ፈትቶ ወደኋላ የቀሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያንሰራሩና እንዲጠናከሩ፣ ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

"ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የአምራችነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት



ይፈልጋሉ፡፡ ከፍተኛ ኃይል ከመጠቀም አንጻር ለምሳሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ እራሱን የቻለ ኃይል ያስፈልገዋል፡፡ ይህ መሆኑ ረዘም ያለ የሥራ ጊዜ እንዲኖራቸው ያስችላል" ብለዋል፡፡

እንደ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ያሉት ደግሞ በትልልቅ አምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚመደቡ በመሆናቸው ከፍተኛ ኃይል ይጠቀማሉ የሚሉት አቶ ታረቀኝ፤ የኃይል አቅርቦት ምቹ ሲሆን፣ በተጨማሪ ትላልቅ የሚባሉ ኢንዱስትሪዎች እየመጡ መሆኑንም አብራርተዋል።

እንደ ሀገር 15ሺ የሚደርሱ በአነስተኛና መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በሥራ ላይ ይገኛሉ ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች አስተማማኝ የሆነ የኃይል አቅርቦት ባቀረብንላቸው ልክ የማምረት አቅማቸው ስለሚጨምርና በርካታ የሰው ኃይልንም ስለሚይዙልን ሁኔታውን ይበልጥ ምቹ ለማድረግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ድርጅት ጋር በጋራ እየሰራ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

## "ሕብረታችን በሌሎችም የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የኃይል ማመንጫ ግንባታዎች ላይ መደገም አለበት"

**- አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር)**
**የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፅሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር**

**ምሕረት ሞገስ**

አዲስ አበባ፡- በዓባይ ግድብ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳየውን ሕብረት በሌሎችም የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የኃይል ማመንጫ ግንባታዎች ላይ መድገም እንዳለበት የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፅሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ የዓባይ ግድብ በሕዝብ ቁጭት ተገንብቶ አፈፃፀሙም 95 በመቶ ደርሷል፡፡ በቀጣይም በሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ላይ በተመሳሳይ መልኩ ሕብረቱን አጠናክረን ልንቀጥል ይገባል፡፡

ለጊዜው ግድቡ ሙሉ ለሙሉ እስኪያልቅ እና መቶ በመቶ ኃይል ማመንጨት እስከሚጀምር፤ የሕዝቡ ድጋፍ በተጀመረበት መንፈስ መቀጠል አለበት ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ግድቡን ማነፅ ቢያልቅም፤ ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች መኖራቸውን አስታውሰዋል፡፡ አካባቢውን በአረንጓዴ ልማት መሸፈን እና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ጊዜ የሚሠጠው ጉዳይ እንዳልሆነም ጠቁመዋል፡፡

አረንጓዴ ልማት ላይ በስፋት ካልተሠራ ውሃው አፈሩን እየጠረገ ወደ ግድቡ በመግባት የግድቡን እድሜ የሚያሳጥረው መሆኑን ጠቁመው፤ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የአካባቢ ጥበቃ ሥራው ላይ ጠንክሮ መሳተፍ የግድ መሆኑን አመልክተዋል፡፡



በቀጣይም በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ላይ የሚገነቡ የኃይል ማመንጫዎች እንደ ዓባይ ግድብ ተጀምረው እንዲጠናቀቁ ሕዝቡ ሕብረቱን መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል፡፡



የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት

ልዩ እትም

ዜና



## “የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያን መልማት የማይፈልጉ አካላትን ሃሳብ የቀለበሰ ነው”

- ኢንጂነር ጥላሁን ኤርዱኖ (ዶ/ር)

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያን መልማት የማይፈልጉ አካላትን ሃሳብ በመቀልበስ ልማትን ማረጋገጥ የቻለ ሀገራዊ ፕሮጀክት ነው ሲሉ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር ጥላሁን ኤርዱኖ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሰርቬይንግና ካርታ ኢንጂነሪንግ መምህር ጥላሁን ኤርዱኖ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያን መልማት የማይፈልጉ አካላት ሃሳብ የቀለበሰ ነው፡፡

ግድቡ ኢትዮጵያ በሰላም መቀጠል ከቻለችና አንድነቷ ከጠነከረ ልማት ታስባለች በሚል የተዛባ አመለካከት የኢትዮጵያን ልማት ሲያደናቅፉ የቆዩ ሀገራትን እሳቤ ማምከን ችሏል ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የነበሩበትን በርካታ ጫናዎች እንዲሁም ፈተና ተቋቁሞ ለዚህ ደረጃ መድረሱ በተባበበረ ክንድ የትኛውንም አይነት ዓላማ ከግብ ማድረስ እንደሚቻል በተግባር የተገለጸበት ነው ሲሉም አብራርተዋል፡፡

ለወደፊት ለሚቀረጹ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች መሳካት መንገድ የሚከፍት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ዶክተር ጥላሁን አክለውም፤ የግድቡ እውን መሆን ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ጎን ለጎን የሀገርን ደህንነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር የሚረዳ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ጥላሁን ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ረገድ የዓባይ ወንዝን በጋራ ለመጠቀም እየሄደች ያለው ርቀት ትክክለኛና ሕግን የተከተለ ነው፡፡ ውሃን በብቸኝነት የመጠቀም አባዜ ያለባቸው ሀገራት ከስምምነት ላለመድረስ ለተፋሰሱ ሀገራት ስጋት ይሆናል ቢሉም ምንም ዓይነት የሚፈጥረው ጫና የለም፡፡

የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለማንም ድጋፍ በራሱ አቅም የገነባው ትልቅ ፕሮጀክት ነው ያሉት ዶክተር ጥላሁን፤ ለዚህ ደረጃ ለመድረስም በርካታ ፈተናዎች መታለፉን አስረድተዋል፡፡

ግድቡ ለኢትዮጵያ ለተለያዩ ልማቶች መሰረት ከመሆን በተጨማሪ ለተፋሰሱ ሀገራት የጎርፍ አደጋ ለመቀነስ የሚረዳ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያ ሌሎች የውሃ ሀብቶቿን በአግባቡ እንድትጠቀም ያስችላል ያሉት ዶክተር ጥላሁን፤ በሀገሪቱ ያሉ የውሃ ሀብቶች ማልማት ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር የሰላም ዋስትና ማረጋገጫ ነውም ብለዋል፡፡


ኢትዮጵያ በቀጣናው ያሉ የውሃ ሀብቶች በጋራ አልምታ የመጠቀም እሳቤ ቢኖራትም አንዳንድ ሀገራት በግል የማግበስበስ ፍላጎት የተነሳ አሻጥር ሲሰሩ ይታያሉም ብለዋል፡፡

ዶክተር ጥላሁን፤ ከኢትዮጵያ የሚወጡ ወንዞች ላይ ልማት ሲጀመር የተፋሰሱ ሀገራት ቅሬታ ሲያቀርቡ ይስተዋላል፡፡ ይህንንም ለመቀልበስ ወደ ውጭ የሚፈሱ ወንዞችን ቀድሞ ማልማት እንደሚያስፈልግ ምክረ-ሃሳባቸውን ለግሰዋል፡፡

በተጨማሪም የተፋሰሱ ሀገራትን ስጋት ለመቀነስ፣ አስተማማኝ ሁለንተናዊ ልማት በኢትዮጵያ ለማረጋገጥ፣ የውስጥና የውጭ ፖለቲካዊ ጫናን ለመቀነስ እንዲሁም ግድቡ በአጭር ጊዜ ደለል እንዳይሞለው ለማድረግ ሌሎች ግድቦችን መገንባት አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

# የዓባይ ግድብ ዕውነታዎች

ማርቆስ በላይ



ከ13 ዓመት በፊት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ነበር የተጀመረው። የኢትዮጵያዊያን አንድነትና የይቻላል መንፈስ የታየበት ሀገራዊ ፕሮጀክትም ነው። በተለይ ለመጪው ትውልድም የይቻላል መንፈስን ሲያንጸባርቅ የሚኖር ፕሮጀክት ነው - የዓባይ ግድብ።

ግድቡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጉባ ወረዳ ላይ እየተገነባ ይገኛል። የግንባታው ፕሮጀክት ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ሁሉም ዜጋ የአቅሙን አስተዋጽኦ በማድረግ መጠናቀቁን በጉጉት እየተጠባበቀ ነው።

ታዲያ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ኢትዮጵያዊያን ትንሹም ትልቁ እንጉርጉሮን በማስቀረት ዓባይን ወደ ህዳሴ ጉዞ አስጀምረዋል። የዚህ ሀገራዊ ፕሮጀክት የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠበት 13ኛ ዓመት በተለያዩ ሁነቶች እየተከበረ ነው።

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክር አቶ ኃይሉ አብርሃም ለአፐድ እንደገለጹት፤ 13ኛ ዓመቱን የያዘው የዓባይ ግድብ አጠቃላይ ግንባታ በአማካኝ 95 በመቶ ደርሷል።

የግድቡ ከፍታ 145 ሜትር ሲሆን፤ ዋናው ግድብ አንድ ሺህ 780 ሜትር ርዝመት አለው። የዋናው ግድብ ከስር ውፍረቱ 130 ሜትር ሲሆን ግድቡ ሲያልቅ ከላይ አስራ አንድ ሜትር እንደሚሆን ይናገራሉ።

በአሁኑ ወቅት የሲቪል ስራ 98 ነጥብ 9 በመቶ መድረሱን የሚገልጹት አቶ ኃይሉ፤ የኤሌክትሮ መካኒካል ስራው 76 በመቶ የተሰራ ሲሆን የውሃ ማስተላለፊያ ብረታ ብረት ስራዎች 87 ነጥብ አንድ በመቶ ደርሷል።

አሁን ላይ ግድቡ 42 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ የውሃ መጠን መያዙን ገልጸው፤ ውሃው ከዋናው ግድብ ወደ ኋላ 160 ኪሎ ሜትር መተኛቱን ገልጸዋል።

ግድቡ ሲጠናቀቅ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ አጠቃላይ ውሃ መጠን እንደሚይዝ ጠቁመው፤ ዋናው ግድብ ሲጠናቀቅ 256 ኪሎ ሜትር ወደ ኋላ ውሃ እንደሚያስተኛ ይገልጻሉ።

የዓባይ ግድብ በአሁኑ ወቅት በሁለት ተርባይኖች 540 ሜጋ ዋት በማመንጨት ላይ ነው። ግድቡ ሲጠናቀቅ አምስት ሺህ 150 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረት አቅም አለው ብለዋል።

ግድቡ ሲጠናቀቅ በ13 ተርባይኖች 5 ሺህ 150 ሜጋ ዋት የሚያመነጭ መሆኑን ገልጸው፤ 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ በመያዝ ትልቁ ሰው ሰራሽ ሀይቅ ይሆናል ተብሎም እንደሚጠበቅ አመላክተዋል።

የኮርቻ ግድብ አምስት ነጥብ ሁለት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን 50 ሜትር ከፍታ እንዲኖረው ተደርጎ ተገንብቷል። የኮርቻ ግድብ ሃይል ለማመንጨት የተጠራቀመውን ውሃ አቅፎ የሚይዝ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

የሲቪል ስራውን የሚያከናውነው የጣሊያኑ ሳሊኒ የሥራ ተቋራጭ ሲሆን ቀሪ ሥራዎችን አምስት የተለያዩ ተቋማት በግንባታው ላይ እየተሳተፉ ይገኛል። ግድቡ ሲጠናቀቅ 78 ደሴቶች ይፈጠራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ደሴቶቹን ለተለያዩ የሪዞርትና መዝናኛ አገልግሎት ማዋል እንደሚያስችል ጠቅሰው፤ በግድቡ ሐይቅ በዓመት ከ10 ሺህ ቶን በላይ አሳ ማምረት የሚያስችል እንደሚሆን ጠቁመዋል።

የዓባይ ግድብ በኤሌክትሪክ ኃይልን በማመንጨት ከአፍሪካ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። በተለይም ለቀጠናው ህዝቦች ትስስር፣ ለገጽታ ግንባታ፣ ለአፍሪካ ሀገራት ተሞክሮ ቁልፍ ሚና እንዳለው ተመላክቷል።

ግንባታው ሲጠናቀቅ ለውጪ ከሚቀርብ የኤሌክትሪክ ሽያጭ በዓመት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ ይገኝበታል ተብሎ ይገመታል። የሀገር ውስጥ የኤሌክትሪክ ሽፋኑን 75 በመቶ ለማዳረስ ያግዛል ተብሎ እንደሚጠበቅም ገልጸዋል።

ለግድቡ እስካሁን ከ19 ቢሊዮን ብር በላይ ከሕዝብ መሰብሰቡን የገለጹት አቶ ኃይሉ፤ በዘንድሮው ስምንት ወራት ብቻ 931 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ ተችሏል ብለዋል።

# “ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ኩራት፣ የይቻላል ተምሳሌት ነው”

- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ታላቁ የሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ኩራት፣ የይቻላል ተምሳሌት ነው ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበትን 13ኛ ዓመትን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ እንደገለጸው፤ የግድቡ መሠረት የተጀመረበት 13ኛ ዓመቱ “በኅብረት ችለናል!” በሚል መሪ ሃሳብ የሚከበረው ከጅምሩ እስከዛሬ ሕዝባችን ላደረገው ያልተቋረጠ ሁለንተናዊ ድጋፍ ምስጋና ለማቅረብ ነው ሲል ገልጿል።

መግለጫው እንዳተተው፤ መጋቢት 24 ቀን በ2003 ዓ.ም የተጀመረው የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ተሳክቶ ከመገባደጃው ጫፍ ደርሷል። ግድቡ ከዚህ ስኬት ሲደርስ እልፍ አእላፍ ችግሮችንና የሴራ ወጥመዶችን አልፎ ነው።

የግድቡ መሠረት የተጀመረበት 13ኛ ዓመቱ “በኅብረት ችለናል!” በሚል መሪ መልእክት የሚከበረው ከጅምሩ እስከዛሬ ሕዝባችን ላደረገው ያልተቋረጠ ሁለንተናዊ ድጋፍ ምስጋና ለማቅረብ ነው ሲል አስታውቋል።

ግድቡን ለመገንባት ስናቅድና ስንጀምር ጫጫታና ጫናው ቀላል አልነበረም ያለው መግለጫው፤ የኢትዮጵያውያን ሕልምና ተስፋ ከጅምሩ እንዲጨናገፍ አንዳንድ ሀገራት በጋራ አድመው አሲረውብናል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድንገለልና እንድንነጠል ከፍተኛ ዘመቻ ተከፍቶብናል። ባልፈረምነው የቅኝ ገዥዎች ውል ሊያስገድዱንና ውጥኑ ከመነሻው እንዲጨናገፍ ሞክረዋል። አንዳንዶቹም “ይጀምሩታል እንጂ አይጨርሱትም!” እያሉ የብድር አማራጮችን ሁሉ ሲያመክኑብን ቆይተዋል ብሏል።

ሁሉን አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁመን ግድቡን ወደ ማገባደጃ ምዕራፍ ስናሸጋግርም ዘመቻውን ዳግም በመክፈትና ኃይል በማስተባበር የፀጥታው ምክር ቤት ልማትን እንደጦርነት እንዲመክርበት ተደርጓል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን በጋራ የጀመርነውና አስፈላጊውን መሥዋዕትነት ሁሉ የምንከፍልለት የኩራታችንና አንድነታችን መገለጫ ፕሮጀክት ነበርና ከዚህ አድርሰነዋል ብሏል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

በመግለጫው።

እንደመግለጫው፤ ግድቡን የምንገድበው ማንንም ለመጉዳት አይደለም፣ መነሻችን ሕዝባችንን ከጨለማ ኑሮ ለማላቀቅ ብቻ ነው። በዚህ መሻታችን ደግሞ የሚጎዳም፣ የተጎዳም አካል የለም፣ አይኖርምም። በራሳችን ወንዝና በራሳችን ሀገር፣ በራሳችን አቅም እንዳንለማ ሲፍጨረጨሩ የነበሩ ሁሉ ብድር ለማስከልከል፣ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንዳያደርጉ ለመወትወትና ልዩ ልዩ ማሰናከያዎችን ለመደርደር በእጅጉ ደክመዋል።

ኢትዮጵያውያን ግን የተንኮል መረቦችን በጋራ እየበጣጠሱ፣ ተማሪዎች ከዕለት ጉርሳቸው፣ የመንግሥት ሠራተኞች ከደመወዛቸው፣ ነጋዴዎች ከወረታቸው፣ ጡሮተኞች ከአነስተኛ አበላቸው፣ የጉልበት ሠራተኞች ከዕለት ምንዳቸው፣ የፀጥታ ኃይሎችና የመከላከያ ሠራዊት አባላት ከሬሽናቸው፣ በስደት ያሉ ኢትዮጵያውያን ከአነስተኛ ገቢያቸው፣ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በላባቸው ካፈሩት ፍሬ እየቀነሱ ግድቡን ከማጠናቀቂያ ምዕራፉ አድርሰውታል።

ኢትዮጵያውያን ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ አስተዋጽኦ ያደረጉት ገንዘባቸውን ብቻ አልነበረም፤ ደስታቸውን፣ ኀዘናቸውን ሁሉ ጭምር እንጂ ያለው የአገልግሎቱ መግለጫ፤ የሠርጋቸውን ወጪ ቀንሰው ሙሽሮች ለግድቡ ሰጥተዋል፤ የሟች ቤተሰቦቻቸውን የሙት ዓመት መታሰቢያ ለሕዳሴ ግድብ አበርክተዋል። በአጠቃላይ ታላቁ የሕዳሴ ግድባችን ልክ እንደ ዓድዋ ድል መላው ኢትዮጵያውያን የተረባረቡበት የወል ድል ነው፤ በጋራ ጀምረን የማንጨርሰው ጉዳይ እንደሌለ ማሳያም ነው ብሏል።

የኃይል አቅርቦት ዓለም አቀፍ ችግር ነው፤ በተለይ ደግሞ ታዳሽ ኃይል ማመንጨት ዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚያስገኝ ተግባር ነበር። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ግን በራሳችን ወንዝ፣ በራሳችን አቅም፣ በራሳችን ሀገር ታዳሽ ኃይል እንዳናመነጭ በርካቶች ተረባረቡብን። ነገር ግን ሊያዘገዩን እንጂ ከሕልማችን መዳረሻ ሊያስቆሙን አልቻሉም፤ ምክንያቱም በጋራ ቆመናልና ሲል አስፍሯል።

አሁን ላይ በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ስኬት ፕሮጀክቶችን በራስ አቅም ጀምሮ የመጨረስ አቅም እንዳለን አሳይተናል። አጠቃላይ ሥራው በመጠናቀቅ ላይ የደረሰው ግድባችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል፤ ለቀሪ ሥራዎቹም ኢትዮጵያውያን የመጨረሻዎቹን ሴኮንዶች ማርሽ ቀይረው ጭምር ማስደመም ይችላሉና። ከ18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ አዋጥተው ግድቡን በማገባደጃ ምዕራፍ ላይ ያደረሱ ኢትዮጵያውያን ለቀሪው የማንንም ድጋፍ አይጠብቁምና ብሏል።

መንግሥት ዘንድሮ የግድቡን ግንባታ የጅማሮ 13ኛ ዓመት ሲያከብር እንደከዚህ ቀደሙ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እየጠየቀ ብቻ አይደለም ያለው መግለጫው፤ በጋራ ተሳትፎ ከዚህ ስላደረሱት እያመሰገነ ጭምር እንደሆነ ጠቁሟል።

አገልግሎቱ እንደገለጸው፤ እንደ ሕዳሴ ግድብ ሕዝብ በነቂስ የተሳተፈበት ፕሮጀክት በዓለም ስለመኖሩ ያጠራጥራል፤ እንደ ሕዳሴ ግድብ በዓለም አቀፍ መድረክ እየተፈተነ ከዚህ ደረጃ የደረሰ የታዳሽ ኃይል ማመንጫ ግድብም እምብዛም አይታወቅም። ሆኖም ግን ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት የተሳካው በመላው ኢትዮጵያውያን የእንችላለን መንፈስና የጋራ ጥረት ነው። ታላቁ የሕዳሴ ግድባችንም የኢትዮጵያን ሁሉ የጋራ ድልና የይቻላል መንፈስ ተምሳሌት ሆኖ ይቀጥላል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት



ልዩ እትም

# ለ13 ዓመታት ቦንድ የገዙት ጡረተኛ

**መዓዛ ማሞ**

የሀገር ፍቅርን ከቃላት አልፎ በተግባር መግለጽ ሲቻል የሚፈጥረው ደስታ ወደር የለውም፡፡ ብዙዎች ለሀገራቸው ባላቸው ፍቅር የሀገር ሉዓላዊነትን ለማስከበር ጦር ሜዳ በመዝለቅ ህይወታቸውን ሰጥተው ስማቸውን ከመቃብር በላይ አውለዋል፡፡

ሌሎች በዓለም አደባባይ በመገኘት የእናት ሀገራቸውን ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ አድርገዋል፡፡ የታደሉት ደግሞ በማምሻ እድሜያቸውና በጡረታ ዘመናቸዉ ላይ ሆነዉ ለልጆቻቸዉ የሚያስረክቧትን ሀገር መገንባት ችለዋል፡፡

የደብረማርቆስ ከተማ ነዋሪ የሆኑት የ74 ዓመቱ የእድሜ ባለጸጋ አቶ ፋንታ መስተሳህል ከታደሉት መካከል አንዱ ናቸው፡፡ አቶ ፋንታ በቀድሞ አውራ ጎዳና በአሁኑ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የአንደኛ ደረጃ የመንገድ ስራ ኃላፊ በመሆን ለ37 ዓመታት ሀገራቸውን አገልግለው በ2002 ዓ.ም በጡረታ በክብር ተገልለዋል፡፡

የሶስት ሴቶች እና የአንድ ወንድ ልጅ አባት የሆኑት አቶ ፋንታ፤ መጀመሪያ ጡረታ እንደወጡ በወር 1600 ብር ይከፈላቸው እንደነበር ይናገራሉ፡፡ በ2003 የዓባይ ግድብ ግንባታ በመጀመሩ እጅግ መደሰታቸውን የሚገልጹት እኚሁ አባት በወቅቱ የመንግሥት ሰራተኞች ከደሞዛቸው ቦንድ ሲገዙ እሳቸውም ከሚያገኙት የጡረታ ገንዘብ ላይ ግድቡ እስከሚጠናቀቅ በየወሩ ያለማቋረጥ የ1000 ብር ቦንድ ለመግዛት ለራሳቸው ቃል ገብተው ጀመሩ፡፡

ለ13 ዓመታት በየወሩ ያለማቋረጥ ቦንድ ሲገዙ የቤተሰቦቼ ድጋፍ አልተለየኝም የሚሉት ጡረተኛው፤ በተለይ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ከሚያገኙት የጡረታ ክፍያ ከ62 በመቶ በላይ የሚሆነውን ለቦንድ ግዢ ያውሉ እንደነበር ይገልጻሉ፡፡

ዛሬ ላይ ፈጣሪ እድሜ ሰጥቷቸው የግድቡን መጨረሻ ለማየት በመቃረባቸው እድለኛ መሆናቸውን የሚገልጹት አቶ ፋንታ፤ አያድርገውና ክፉው ሞት ቀድሟቸው የነበረ ቢሆን እንኳን ለልጆቻቸው "ከሞትኩ ግድቡ እስከሚጠናቀቅ በስሜ የቦንድ ግዢው እንዳይቋረጥ"በማለት አደራ ብለው እንደነበር ይናገራሉ፡፡

"አቅም በነበረኝ ጊዜ በየጫካው እና በየዱሩ እየዞርኩ ለሀገሬ አገልግያለሁ" የሚሉት አቶ ፋንታ በጡረታ ከተገለሉ በኋላም በህይወት እስካሉ ድረስ ለሀገራቸው አስተዋጾ ማድረጉን እንደሚቀጥሉበት በኩራት ይናገራሉ፡፡

ወጣቱ ትውልድ ከሳቸው ህይወት በመማር ለሀገር ልማትና ግንባታ በሚደረጉ ስራዎች ሁሉ ጉልበቱንና ገንዘቡን ሳይሰስት በመስጠት ሀገርን ለማሳደግ ሁሉም መተባበር እንዳለበትም ይመክራሉ፡፡

ጡረተኛው በየወሩ የሚገዙት የአንድ ሺህ ብር ቦንድ ዛሬ በ13ኛ ዓመቱ ላይ 156 ሺ ብር ደርሷል፡፡ ግድቡም ወደ መጠናቀቁ ተቃርቧል፡፡

የዓባይ ግድብ ኃይል ከማመንጨት ባሻገር ለቱሪዝም እድገቱም ወሳኝ ነው የሚሉት አቶ ፋንታ ለዚህ ታላቅ ግድብ አስተዋጾ አለማድረግ በህይወት እንዳለመኖር ይቆጠራል ይላሉ፡፡

# "ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁማ አላማዋን ማሳካት እንደምትችል በዓባይ ፕሮጀክት አሳይታለች"

**- አቶ ሞቱማ መቃሳ**
**የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር አማካሪ**

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁማ አላማዋን ማሳካት እንደምትችል በዓባይ ግድብ ፕሮጀክት አማካኝነት በግልጽ አሳይታለች ሲሉ በሚኒስትር ዴኤታ ማዕረግ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ አማካሪ አቶ ሞቱማ መቃሳ ተናገሩ።

አቶ ሞቱማ መቃሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በዓባይ ግድብ ፕሮጀክት የተነሳ ኢትዮጵያ እስከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት የደረሰ ክስ ቢቀርብባትም ግንባታውን ሳታቆም ከማገባደጃው ማድረሷ ማንኛውም ጫና ቢደርስባት ከግቧ ሊያስቆማት የሚችል ኃይል እንደሌለ ማሳያ ነው።

ግብጽ በዋናነት የግድቡ ግንባታ እንዳይከናወን የተለያዩ ሴራዎችን ስታከናውን መቆየቷን አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ በበኩሏ በውሃ ሃብቷ የመጠቀምና የመልሟት ፍላጎቷን እንዳታሳካ የተደረጉ ጥረቶችን በሙሉ በማክሸፍ ግንባታውን ወደማጠናቀቂያው ማሸጋገሯ ለትውልዱም ጽናትን የሚያጎናጽፍ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በግድቡ ጉዳይ ኢትዮጵያ በተዘዋዋሪ መንገድ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንዲሁም በአሜሪካ በኩል ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲቀርብባት እንደነበር ጠቁመው፤ በፕሮጀክቱ ሂደት ላይ በአፍሪካ ኅብረት በኩልም በርካታ ታዛቢዎች የተሳተፉባቸው ድርድሮች ሲካሄዱ መቆየታቸውን አመላክተዋል።

በዋናነት በዓባይ ግድብ ጉዳይ የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት ሱዳንና ግብጽ ከኢትዮጵያ ጋር መስማማት የሚችሉባቸው ሰፊ አማራጮች ቢኖሩም ጉዳዩን ዓለም አቀፋዊ ስጋት ለማድረግ የጸጥታው ምክር ቤት ድረስ የተሄደበት መንገድ ተገቢ አለመሆኑን አመላክተዋል።

አቶ ሞቱማ እንዳስታወቁት፤ ቀድሞ በዓባይ ወንዝ ላይ ግድብ አትገነቡም ሲባል የነበረው ተቀይሮ ውሃ መያዝ አትችሉም የሚል ጥያቄ ነበር ከግብጽ የሚነሳው። አሁን ደግሞ ውሃውም ተሞልቶ ኤሌክትሪክም እያመነጨ በመሆኑ ግብጾች የማጠናቀቂያ ስራውን ከማየት ውጪ የተለየ ጫና መፍጠር እንደማይችሉ ይረዱታል ብለዋል።

በዚህ አግባብ ፈተና ቢበዛም አላማ ላይ ማተኮርና መብትን መጠቀም ከተቻለ የማይታለፍ ችግር እንደማይኖር መገንዘብ ይገባል ሲሉ አማካሪው አስረድተዋል።

ጫናው በተለያዩ ስራዎች አማካኝነት እየታለፈ ቢመጣም በሂደት የታየው ጣልቃ ገብነትና ክስ ግን ለሌሎች ግዙፍ የልማት ስራዎችም አቅም የሚሰጥ ልምድ የተገኘበት መሆኑን ገልጸዋል።

የታችኞቹን የተፋሰስ ሀገራትን በማይጎዳ መልኩ በጥንቃቄ እየተገነባ የሚገኘው የዓባይ ግድብ የመላው ኢትዮጵያውያን የአንድነት ተምሳሌት መሆኑን ጠቁመው፤ ፕሮጀክቱ ምንም አይነት ጫና ቢበረታብን አላማችንን መሳት እንደሌለብን ያስተማረ በመሆኑ ድጋፋችንን አጠናክረን ልንቀጥል ይገባል ብለዋል።

የመልማት መብታችንን ተጠቅመን ለምንሰራቸው ማናቸውም ፕሮጀክቶች ዓለም አቀፍ ሕጎችን ከተከተልንና በአንድነት ድጋፍ ካደረግን ማሳካት የማንችለው የልማት ስራ እንደማይኖር ዓባይ ምስክር መሆኑን አስታውቀዋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ የተጀመረበት 13ኛ ዓመት ሲከበርም "በኅብረት ችለናል" በሚል መሪ ሀሳብ መሆኑ ጫናዎች ቢበረቱ እንኳን አንድነት ካለን ግባችንን ማሳካት እንደምንችል አመላካች ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ልክ ለግድቡ እንደተደረገው ርብርብ በሌሎች የልማት ስራዎች ላይ ተመሳሳይ ድጋፎችን በማድረግ ሀገራችንን ወደተሻለ ሁኔታ ማሸጋገር ይገባል ሲሉም አቶ ሞቱማ መቃሳ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# ዳያስፖራው ለዓባይ ግድብ ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወደ ኢትዮጵያ ልኳል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አቶ ወንደሰን ግርማ

አዲስ አበባ፡- የዳያስፖራው ማህበረሰብ የዓባይ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን በቦንድ ግዢና በስጦታ ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወደ ኢትዮጵያ መላኩን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደሰን ግርማ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የዳያስፖራው ማህበረሰብ ባለፉት አሥራ ሶስት ዓመታት ማለትም የዓባይ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ዘርፈ ብዙ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል።

የዲያስፖራው ማህበረሰብ ከሚሰራቸው ሥራዎች አንዱ ሀብት ማሰባሰብ ሥራ ተጠቃሽ ነው ያሉት አቶ ወንደሰን፤በዚህም የዳያስፖራው ማህበረሰብ በቦንድ ግዢና በስጦታ ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ አሰባስቦ ወደ ኢትዮጵያ ልኳል ብለዋል።

የዳያስፖራው ማህበረሰብ አባላት ኢትዮጵያ በተፈተነችበት ወቅት በዓለም አደባባይ ለሀገራቸው ብሄራዊ ጥቅም መከበር ሲሉ ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ያላቸውን ሁሉ ሰጥተዋል ያሉት አቶ ወንደሰን፤ በተለይ የዓባይ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጫና ነበር። በተለይም ግድቡ ውሃ መያዝ ከጀመረ ጊዜ በኋላ የነበሩት ጫናዎች በእጥፍ ጨምረው ነበር ያሉት አቶ ወንደሰን፤ የዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት ግን በዚህ ሁሉ ጊዜ ለሀገራቸው ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበር ጠቁመዋል፡፡

የዓባይ ግድብ ጉዳይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት አጀንዳ በነበረበት ወቅት መንግሥት ከሚያደርጋቸው የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ሥራዎች በተጨማሪ የዳያስፖራው ማህበረሰብ ሰላማዊ ሰልፎችና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶችን አድርጓል ነው ያሉት።

እንደ አቶ ወንደሰን ገለፃ፤ ዳያስፖራው በግድቡና በኢትዮጵያ ላይ የነበረው የውጭ ተጽዕኖ እንዲቀንስ ከፍተኛ ሥራዎችን ሰርቷል። ይህም የኢትዮጵያውያን አንድነት የታየበት ነው። አሁን ከዓባይ ግድብ ጋር በተያያዘ በርካታ ድርድሮች እየተካሄዱ ነው።

በድርድሩም የዳያስፖራው ማህበረሰብ በርካታ ጠቃሚ ግብዓቶችን እያቀረበ ይገኛል ያሉት አቶ ወንደሰን፤ ከዚህ ባለፈ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ግድቡን በሚመለከት የኢትዮጵያን እውነታ እና ትክክለኛነት እንዲረዳ የተለያዩ ሥራዎችን ሰርቷል። ይህም በሰላማዊ ሰልፍ፣ በመጽሔትና በማህበራዊ ሚዲያዎች ተግባራዊ ተደርጓል ብለዋል።

ስለዚህ የዳያስፖራው ማህበረሰብ ባለፉት አሥራ ሶስት ዓመታት ከዓባይ ግድብ ጋር በተያያዘ የሠራቸው ሥራዎች ዘርፈ ብዙ መሆኑንም ገልጸዋል።

# ለዓባይ የተዘረጉ ለጋስ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በጉባ ወረዳ ሰማይ ስር የግንባታው የመሰረት ድንጋይ ተቀመጠ።

እነሆ በአሁኑ ወቅት ታዲያ የዓባይ ግድብ ግንባታ በልጆቹ ብርቱ ክንድ እየተገነባ 13 ዓመታትን ተሻግሯል። የኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ ሀሩር ከበረታባቸው የጉባ ተራሮች ግርጌ ታላቅ ጀብዱ ፈፅሟል። ዓባይ ግስጋሴውን ገታ አድርጎ ወደ ውስጥ በአትኩሮት እንዲያጤን ተደርጓል፤ በሀገር እጅ ለሀገር ልጅ እንዲሆንም ተደርጓል።

ጉዞው ከተገታና በቤቱ ማደር ከጀመረም ዓመታትን አስቆጠሯል፤ በኢትዮጵያውያን የድጋፍ ማዕበል ታጅቦ፣ በጠላት ዓይን እየተገለመጠ፣ በርካታ ተግዳሮቶችን በመሻገር የተስፋ ፍሬውን ለልጆቹ ማቅመስ ከጀመረም ሰነባብቷል።

ግድቡን ከዳር ለማድረስ እናቶች በመቀነታቸው ከቋጠሯት ገንዘብ ለግሰዋል። ከዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እስከ ባለሀብት በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በጉልበትና በቴክኒካል ጉዳዮች ድጋፍ አድርገዋል። ከልጅ እስከ አረጋውያን በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለግድቡ ያለማቋረጥ አለኝታነታቸውን አረጋግጠዋል።

በርካታ ተቋማት ከተቋቋሙበት ተግባርና ኃላፊነት ጎን ለጎን ቦንድ በመግዛት፣ ቴክኒካል ድጋፍ በማድረግና ሰራተኞችን በማስተባበር አሻራቸውን እንዲያሳርፉ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት፣ የበላይነህ ክንዴ ግሩፕ፣ መድን ሰጪ ኩባንያዎች እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ድጋፍ ካደረጉ ተቋማት መካከል ናቸው። ተቋማቱም ለዝግጅት ክፍላችን ይህንን ብለዋል።

ደረሰ በላይነህ ይባላሉ። በኢትዮጵያ መድን ድርጅት የፕሮሞሽንና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር ናቸው። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለዓባይ ግድብ ግንባታ የተለያዩ አስተዋጽኦዎችን አበርክቷል። በ2013 ዓ.ም የ50 ሚሊዮን ብር፣ በ2014 ዓ.ም የ100 ሚሊዮን ብር፣ በ2015 ዓ.ም የ155 ሚሊዮን 310 ሺህ ብር በ2016 ዓ.ም 173 ሚሊዮን 350 ሺህ ብር ቦንድ በመግዛት የድርሻውን ተወጥቷል።

በአጠቃላይ ድርጅቱ ለዓባይ ግድብ የ478 ሚሊዮን 660 ሺህ ብር ቦንድ በመግዛት ድጋፍ ማድረጉን የሚናገሩት አቶ ደረሰ፤ ድርጅቱ መድን ሰጪ ተቋም እንደመሆኑ መጠን በዓባይ ግድቡ ምንም ዓይነት አደጋ ቢደርስበት መቋቋም እንዲችል የመድን ሽፋን ተሰጥቶታል ብለዋል። የተቋሙ ሰራተኞች ለግድቡ የራሳቸውን አሻራ እንዲያሳርፉ በሁለት ዙር ቦንድ እንዲገዙ የማስተባበር ስራም ተሰርቷል ብለዋል።

ታላቁ ህዳሴ ግድብ ለፍጻሜ ደርሶ ኢትዮጵያ በስራ እድል ፈጠራ፣ በኃይል አቅርቦት፣ በመስኖ ልማትና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ተጠቃሚ እንድትሆን ድርጅቱና ሰራተኞቹ የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉም ተናግረዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም ለዓባይ ግድቡ እጃቸውን ከዘረጉ ተቋማት አንዱ ነው። በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ከ2013 ጀምሮ 389 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉን የሚናገሩት የኢትዮ ቴሌኮም ኮሚኒኬሽን ኦፊሰር አቶ መሳይ ውብሸት ናቸው። ድጋፉ የተደረገው በ8100፣ በቴሌ ብር፣ በቦንድ ግዢ፣ በኤስኤምኤስ እና በሌሎች አማራጮች መሆኑን ይናገራሉ።

የበላነህ ክንዴ ግሩፕ የዓባይ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ጀምሮ በዓይነትም በገንዘብም አስተዋጽኦ አበርክቷል የሚሉት የድርጅቱ ኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰጠኝ እንግዳ ናቸው። ድርጅቱ ቦንድ በመግዛትና ግንባታውን የሚያከናውኑ ሰራተኞችን ለማበረታታት የቁም እንስሳትን ጭምር በስጦታ አበርክቷል።

ድርጅቱ በዓይነትና ቦንድ በመግዛት ያደረገው ድጋፍ 36 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ነው። 33 ሚሊየን ብሩ ለቦንድ ግዢ ቀሪው ደግሞ ግድቡን ለሚያከናውኑ ሰራተኞች የዓይነት ድጋፍ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የዓባይ ግድቡ እውን መሆን ለድርጅቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚሉት አቶ ሰጠኝ፤ በአምራች ዘርፍ የተሰማራ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የኃይል አቅርቦት መቆራረጥን ችግር በዘላቂነት ይፈታል የሚል እምነት እንዳላቸውም አብራርተዋል።

"ድርጅቱ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ለዓባይ ግድብ ከሚያደርገው ድጋፍ በተጨማሪም በሀገር ደረጃ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲያጋጥሙ ድጋፍ የማድረግ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን የመገንባት ስራ ያከናውናል። በቀጣይም ለህዳሴ ግድቡ ድጋፍ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ድጋፉን ያደርጋል" ብለዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ዋቄ በበኩላቸው፤ ባንኩ ከመጀመሪያው ጀምሮ ታሪካዊ የሆነ ታላቅ ኃላፊነት ተሰጥቶት ሲሰራ መቆየቱን ጠቁመው፤ በተለይ በፋይናንስ በኩል ቦንድ ከህትመት ጀምሮ እስከ ስርጭት ያለውን ስራ እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት ሲወጣ የቆየ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለግድቡ ግንባታ ፕሮጀክት የተለያዩ እገዛዎችን ከማድረጉም ባለፈ ለዓባይ ግድብ ተግባር ማስፈፀሚያ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ያግዝ ዘንድ ሁለት ተሽከርካሪዎችን በስጦታ አበርክቷል። ቦንዶችን ከ25 ብር ጀምሮ በማሳተም ለህብረተሰቡ የማሰራጨት ስራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የኢትዮጵያ መድን ሰጪዎች ማህበር አባል የሆኑ 18 መድን ሰጪ ኩባንያዎችም ለዓባይ ግድብ አስተዋጿቸውን አበርክተዋል። ግድቡ ከተጀመረ ጀምሮ አንድ ቢሊዮን 563 ሚሊዮን 893 ሺህ ብር ቦንድ በመግዛትና በጥሬ ገንዘብ በመስጠት የድርሻቸውን መወጣታቸውን ማህበሩ አስታውቋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ ከተጀመረበት መጋቢት 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ከሀገር ውስጥ ቦንድ ግዢና ስጦታ፣ ከዲያስፖራ ቦንድ ግዢና ስጦታ፣ ከ8100 A፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ገቢ እና ከደረት ፒን ሽያጭ በአጠቃላይ ከ19 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡንም ከማስተባበሪያው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በአመስጋኝነት ቅኝት፣ በስኬታማነትም መንገድ ነጋችንን እናልቃለን!

ሁሉም ነገር መነሻ አለው፤ ሁሉም ጉዳይ ፈጻሚ አለው፤ ሁሉም ጅምር የሚጠናቀቅበት ጊዜና የሚያጠናቅቀው ኃይል አለው። ትናንት ለዛሬ፣ ዛሬም ለነገ መነሻ እንደሆነው ሁሉ፤ ቀደምቶች ለአሁኑ፣ የአሁኖቹም ለመጪዎቹ ትውልዶች የታሪክም የግብርም መሰናሰል መሠረቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያንም ከትናንት እስከ ዛሬ በታሪክ ጅረት ውስጥ የሚገለጥ፤ የትውልዶች የተግባርም፣ የታሪክም፣ የባህልና እሴትም፣... ቅብብሎሽና መሰናሰሎች የተሳሰሩ ማንነት ያላቸው ሀገርና ሕዝቦች ናቸው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ስንል የሚታየን የገናን ታሪክ ባለቤትነቷ፤ የነፃነትና ብዝሀነት ገጿ ከዚሁ እውነት የተቀዳ ነው።

ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ የደመቀ ታሪክ ባለቤትነታቸው፤ የብዝሀ ማንነት ስሪታቸው የዚሁ የትውልዶች ከትናንት እስከ ዛሬ የዘለቀው የማህበራዊም፣ የኢኮኖሚያዊም፣ የሥነ ልቡናዊም ውቅር ውጤት ነው። የተናበበ ሃሳባቸው፤ የተሰናሰለ ተግባራቸው፤ ያልተቆራረጠ ገድላቸውም የዚህ የጠነከረ የወል ጉዳያቸው ስሪት ነው።

በዚህም ረገድ በሺህ ዘመናት የሚለካ ታሪክን ሰርተዋል፤ ያልተቆራረጠ ሥርዓተ መንግሥትን አኑረዋል፤ የሕዝቦች አብሮነትና መተሳሰብን አጽንተዋል። ዓድዋን የመሳሰሉ ከራስ አልፎ ለመላው ዓለም የነፃነት ችቦን በደማቁ ያበራ ድል የተገኘው በዚሁ መንገድ ነው። የዓባይ ግድብን ያህል ታላቅ ፕሮጀክት አስቦ ለመጀመር፣ ጀምሮም ለመፈጸም ከጫፍ ማድረስ የተቻለውም በዚሁ ልዕልና ነው።

ከ128ኛው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ማግስት፣ 13ኛ ዓመት ልደቱ የሚከበርለት ይሄ ግድብ ታዲያ፤ የትናንት አባቶች የመሠረቷትን ነፃ ሀገር ወደ ሙሉ ነፃነቷ ለማሸጋገር አቅም የሚሆን ነው። ምክንያቱም የዓድዋ ድል ለዓባይ ግድብ ዛሬ ላይ ለዚህ መድረስ አቅምም፣ የሞራል ስንቅም ሆኗል።

ከዚህ ባሻገር ደግሞ፣ የዓድዋ ዘመን ትውልዶች ለዛሬው የዓባይ ዘመን ትውልድ የመቻል ሰብዕና፤ የመፈጸም ልዕልናን፤ የነፃነትንም ከፍ ያለ ዋጋ በልኩ እንዲገነዘብ የሚሆን የመንፈስ ጥንካሬን እንዲላበስ አርአያ ሆነውታል። እናም የትናንቱ ድል ለዛሬው ፕሮጀክት ስንቅ፤ የትናንቶቹ ባለ ድሎች ለዛሬዎቹ ታሪክ አስቀጣዮች አብነት ሆነዋቸዋል።

ይሄ የታሪክ መሰናሰል፤ የትውልድ ቅብብሎች፤ የግብር ምግግቦሽ ታዲያ፤ ለቀደሞት ክብርን፣ ለጀመሩትም ምስጋናን በመቸር ውስጥ የሚራመድ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም የቀደሙትን ያከበረ ትውልድ፣ ለራሱም ይከበራል። የሰሩትን የሚያመሰግን ትውልድ ተመስጋኝነትን ይጎናጸፋል።

የዓባይ ግድብ ጉዳይ ሲነሳም እውነቱ ይሄው ነው። ቀደምቶቹ አሰቡት፤ ሃሳባቸውን በንድፍ አኖሩት፤ ግን ለመፈጸም አቅሙም ወቅቱም አልፈቀደላቸውም፤ እናም ለትውልድ በአደራም በኃላፊነትም ሰጡት። ይሄ የቀደምቶች ምኞት፤ የትናንት ሕልም ነበር።

ዛሬ ያ ምኞት እውነት ሊሆን፤ ሕልሙም ሊፈታ ቀኑ ደረሰ፤ የአደራ ተቀባዩ ትውልድ ምኞቱን ወደ ተጨባጭ እውነት፤ ሕልሙንም በተግባር ፈታው። እናም የዓባይ ግድብ የዛሬ 13 ዓመት የሚታይ እና የሚዳሰስ እውነት ሆነ። ዘመን ለዘመን ሥፍራውን ሲለቅቅ፤ ትውልድ ለትውልድ አደራውን ሰጥቶ ሲያልፍ፤ የማያልፈው እውነት፣ የማይደበዝዘው ተግባር ቦታውን ያዘ።

ለዚህም ነው ቀደምቶችን ማክበር፤ ለተግባር የሚተጉትን ሁሉ ማመስገን የሚገባው። ይሄ በማክበርና በማመስገን የተቃኘ ትውልድና ማንነት ደግሞ፤ መንገዱ ያማረ፣ ተግባሩም የቀና ይሆናል። አመስግኗልና የሚመሰገንበትን ለመሥራት፤ አክብሯልና የሚከበርበትን ዐሻራ ለማኖር የሚያግደው አንዳችም ሁኔታ አይኖርም።

ዛሬ ላይ የዓባይ ግድብ ተጨባጭ እውነት የሚገልጠውም ይሄው ነው፤ በማክበርና በማመስገን የተጀመረ ፕሮጀክት ምንም እንኳን ፈተናው የበዛ ቢሆንም ከችግሩ ባሻገር ለመገለጥ ያገደው ነገር አልነበረም። ዓባይ ከባይተዋርነት ወደ ቤተኝነት ተደምሮ ለሕዝቡ ብርሃንን ማቀበል መጀመሩም የዚሁ ቅኝት ውጤት ነው።

ይሄን መሰሉ የአመስጋኝነት ቅኝት የወለደው ውጤት ደግሞ፣ ዛሬ ላይ በርቶ የሚጨልም አልያም የሚደበዝዝ አይደለም። ይልቁንም የዛሬው ስኬትና ውጤት እንደ ትናንቱ ሁሉ ለነገው አቅምም፣ ስንቅም የሚሆንን ሰብዕና የሚያላብስ ነው። ምክንያቱም ስኬት ጫፍ የለውም። ስኬት በቃኝ የሚል እሳቤም አይቀበልም።

ስኬት እያመሰገኑ መሥራትና ለውጤት መብቃትን ይጠይቃል። ስኬት ዛሬን የተሻለ ሰርቶ ለነገዎቹ በኃላፊነት የሚወጡትን አደራ ማኖርን አብዝቶ ይሻል። ዓባይም እንዲሁ ነው። ትናንቶች አሰቡት፤ ዛሬ ላይ ያሉ ጀምረው ከፍጻሜው አደረሱት። ዓባይ ግን አንድ ብቻ አይደለም። ዓባይ መልከ ብዙ ነው። እናም በዚሁ የበዛ መልኩ የሚገባቸውን እያከበርንና እያመሰገንን፤ የተገኘውን ውጤትም እያላቅን መጓዝ፤ ነጋችንን በዚሁ ልዕልና ቃኝነት የላቀ ማድረግ የተገባ ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት

ልዩ እትም



# ዓባይ-የኢትዮጵያውያን ብርሃን

አስናቀ ፀጋዬ

ብዙ የተባለለትና ብዙ የተወራለት የዓባይ ግድብ ከብዙ ውጣውረድና መሰናክል በኋላ ዘንድሮ አስራ ሶስተኛ ዓመቱን ደፍኖ እነሆ ሊጠናቀቅ ጥቂት ወራቶች ብቻ ይቀሩታል። ያኔ በቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስቴር አቶ መለስ ዜናዊ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጉባና ሰዳል ወረዳ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠለት የዓባይ ግድብ ገና ከመነሻው ነበር ከታችኛው የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት በተለይም ከግብፅና ሱዳን ተቃውሞ የገጠመው። ሁለቱ ሀገራት በተለይም ግብፅ የቀድሞ የቅኝ ግዛት ሕጎችን በማምጣትና በኢትዮጵያ ላይ ዓለም አቀፍ ጫና እንዲበረታ በማድረግ የግድቡን ግንባታ እንዳይከናወን በብርቱ ጥራለች። እንዲያም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ በቁርጥ ቀን ልጆቿ የዲፕሎማሲ ጥረት ፈተናዎችን ተጋፍጣና አልፋ የግድቡን ግንባታ አስጀምራለች።

የዓባይ ግድብ ግንባታ ገና ሃሳቡ ሲፀነስ ነበር መላው ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከዳር ድጋፋቸውን የገለፁት። ግድቡ በሕዝብ ትብብር የሚገነባ እንደመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ነበሩ የግድቡን ግንባታ ዳር ለማድረስ በሚችሉት ሁሉ ድጋፋቸውን ለመቸር ቃል የገቡት። ግድቡ የነገ ኢትዮጵያውያን ብርሃንና ተስፋ ነበርና በጊዜው ኢትዮጵያውን ለግድቡ ግንባታ የሰጡት የትብብርና ድጋፍ ምላሽ ድንቅ ነበር። ኢትዮጵያውያን ለጋራ ጠላቶቻቸው ብቻ ሳይሆን ለጋራ ልማት «ሆ» ብለው እንደሚነሱ ያሳየም ጭምር ነበር የዓባይ ግድብ።

ብረት እንደጋለ ነውና ነገሩ ኢትዮጵያውያን ወዲያው ነበር የግድቡን ግንባታ ያስጀመሩት። የግድቡ ግንባታ ሲጀመር ኢትዮጵያውን የገንዘብና የዓይነት መዋጮ፣ የጉልበት አስተዋፅኦ፣ የሙያና እውቀት አበርክቶ አድርገዋል። እናት ከመቀነቷ ፈታ ለግድቡ አዋጥታለች። ተማሪዎችም አምስትም አስር ሳንቲም ቆጥበው ለግሰዋል። የመንግሥት ሠራተኛውም ቢሆን ቦንድ ገዝቶ የአንድ ዓመት ደሞዙን እንካችሁ ብሏል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማትም ለግድቡ ያልተቋረጠ ድጋፍ አድርገዋል። ባለሀብቶችም እንደዛው።

መላው ኢትዮጵያውያንን ባስተባበረና ባሳተፈ መልኩ የተጀመረው የዓባይ ግድብ ግንባታ ከታችኛው የወንዙ ተፋሰስ ሀገራት የገጠመውን ጫና እየተቋቋመ፣ ለግድቡ ግንባታ አስፈላጊ የሆነውን የብድር ገንዘብ ለማግኘት ተዘዋዋሪ ክልከላና ጫና እየተደረገበት ግንባታው መቀጠሉ አልቀረም። ቀንና ሌሊት ያለእረፍት የሚከናወነው የዓባይ ግድብ ግንባታ እለት በእለት ለውጥ ይታይበት ጀመር። ሕዝቡም የግንባታውን ሂደት በንቃት ነበር የሚከታተለው። የግድቡ መጠናቀቅ ሊያመጣ የሚችለውን ትሩፋት አስቀድሞ የተገነዘበው ሕዝቡ ግድቡ የዓይኑ ማረፊያውም ጭምር ነበር ማለት ይቻላል።

በእንዲህ ሂደት የቀጠለውና እለት በእለት ለውጥ እያሳየ የመጣው የዓባይ ግድብ ግንባታ በመሃል ግን ችግር ገጠመው። በተለይ የብረትና ኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራውን የያዘው የቀድሞው ሜቴክ ድርጅት ሥራውን በአግባቡ ባለመወጣቱ በግድቡ ግንባታ ሂደት ላይ መስተጓጎል ፈጥሯል። የሚጠበቅበትን ሥራ በጊዜው ባለማከናወኑ የግንባታ ሥራ ተቋራጭ የሆነው ሳሊኒ ያለሥራ ቁጭ እንዲል አድርጎታል፤ ለኪሳራም ዳርጎታል። በዚህም ኩባንያው ለደረሰበት ኪሳራ ካሳም እስከመጠየቅ ደርሷል። በዚህ መሃል ታሪካዊ ጠላቶች ጮቤ እስከ መርገጥ ደርሰው ነበር። አጋጣሚውን ተጠቅመው የግድቡን ግንባታ ለማስቆም በብርቱ ጥረዋል።

በአዲስ አበባ ዙሪያና በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ብሎም በአማራ ክልል በተለይ ጎንደር የተቀጣጠለው አመፅ ጫናው አይሎ የኢህአዴግን መንግሥት አስወግዷል። በተለይ ኢህአዴግን ከሥልጣን በማውረድ ረገድ ከኦሮሞ ወጣት እንቅስቃሴ በተጨማሪ በራሱ በኢህአዴግ ውስጥ የነበሩ የኦህዴድና የብአዴን ፖለቲከኞች ትልቅ ታሪካዊ ሥራ ሰርተዋል። በዚህም በኢትዮጵያ አዲስ የለውጥ መንግሥት መጥቷል።

የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ የዓባይ ጉዳይ ለጊዜው የተረሳ ቢመስልም የለውጡ መንግሥት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የፖለቲካ ጉዳዮች ከቋጨ በኋላ በቀጥታ ፊቱን ያማተረው ወደ ዓባይ ግድብ ነበር። በመጀመሪያ መንግሥት የዓባይ ግድብ የገጠመውን ችግር ለመፈተሽ ቁጭ ብሎ ገመገመ። ቀስ በቀስ ግደቡ ለገጠመው ችግር መፍትሔ በማምጣት ግንባታው ካቆመበት እንዲጀምር አደረገ። አሁንም የዓባይ ግድብ ሕዝቡ ሀብት ነውና ሕዝቡ አዲሱ የለውጥ መንግሥት ከመጣም በኋላ ለግድቡ ግንባታ የሚያደርገውን አስተዋፅኦ አላቋረጠም።

መንግሥትም ቢሆን ሊጠፋ የነበረውን የኢትዮጵያውያን ብርሃን የሆነውን የዓባይ ግድብ ነፍስ ዘርቶበት ሥራውን ባስጀመረ በመጀመሪያው ዓመት የመጀመሪያውን የውሃ ሙሌት አጠናቆ ለሕዝቡ አበሰረ። በዚሁ ዓመት የዓባይ ግድብ ሁለት ዩኒቶች ኃይል ማመንጨት መጀመራቸውንም ተናገረ። ሕዝቡም ይህን ብስራት ሲሰማ ለለውጡ መንግሥት ያለው አመኔታ ጨመረ። ወትሮም ቢሆን ለዓባይ ግድብ ግንባታ ሕይወቱንም ጭምር ለመስጠት የማይሳሳው ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሥራቱን ሲሰማ ከዚህ ቀደሙ በበለጠ ለግድቡ የሚያደርገውን ድጋፍ እንደሚያጠናክር ቃል በመግባት ጭምር አረጋገጠ። መንግሥትም የግድቡን ሥራ ማፋጠን ቀጠለ።

አንድ ብሎ የጀመረው የዓባይ ግድብ የውሃ ሙሌት ሁለት ሶስት እያለ አምና ክረምት አራተኛውና የመጨረሻው ሙሌት መከናወኑ በክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተበስሯል። ከሰባት ወር በኋላ ደግሞ የዓባይ ግድብ ሙሉ እንደሚጠናቀቅና ኃይል እንደሚያመነጭ ተነግሯል። ይህም የሕዝቡን መፃኢ ተስፋ ያፈካ ነው። የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ በብዙ መልኩ የኢትዮጵያውያንን ሕይወት የሚለውጥ ነው። ከኢትዮጵያውያንም አልፎ ለሌሎች የጎረቤት ሀገራት የሚተርፍ ነው። የታችኛው የወንዙ ተፋሰስ ሀገራትንም ከተደጋጋሚ ጎርፍና የደለል ሙላት የሚታደግ ነው።

በዚህ የዓባይ ግድብ ግንባታ ኢትዮጵያውያን አንጡራ ሀብታቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን ሁሉ አፍሰዋል። ግድቡ የነገ ተስፋና ብርሃናቸው ነውና የአቅማቸውን ሁሉ ለግድቡ ግንባታ አድርገዋል። ዛሬም ቢሆን የኢትዮጵያውን ለግድቡ ያላቸው አስተዋፅኦ አልቀነሰም። ይልቁንም ጨምሯል። ዛሬም የኢትዮጵያውያን ለግድቡ ግንባታ ያላቸው ድጋፍ ቀጥሏል። ነገም ይቀጥላል።

በእያንዳንዱ ኢትዮጵያውን አበርክቶ እየተገነባ ያለው የዓባይ ግድብ በቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስቴር አቶ መለሰ ዜናዊ የመሠረት ድንጋይ ተቀምጦ በጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ግንባታው ሊጠናቀቅ ከጫፍ ደርሷል። ባጠቃላይ 13 ተርባይኖችን የያዘው የዓባይ ግድብ 145 ሜትር ቁመትና 1 ሺ 780 ሜትር ርዝማኔ አለው። ከ 6 ሺ ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚያመነጭም ይነገርለታል። በእያንዳንዱ ዩኒቶች ወይም ተርባይኖች የሚያመነጨው የኃይል መጠን ደግሞ ከ375 እስከ 400 ሜጋ ዋት መሆኑም ታውቋል።

ግድቡ 74 ቢሊዮን ሜትሪክ ቲዩብ መጠን ያለው ውሃም የሚይዝ ሲሆን ግንባታው ሲጠናቀቅ ግደቡን ከአፍሪካ አንደኛ ከዓለም ደግሞ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጠዋል። ይህም ለመላው ኢትዮጵያውያን ድርብ ድል ነው። ከግድቡ የሚመነጨው 2 ሺ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለጎረቤት ሀገራት በሽያጭ እንደሚቀርብም ይገመታል። ግድቡ በአጠቃላይ የሚይዘው የቦታ ስፋትም 1 ሺ 686 ካሬ ሜትር ነው። ግድቡ ከተገነባ በኋላ ውሃ የሚተኛበት ቦታ ርዝመት ወደኋላ 240 ኪሎ ሜትር እንደሚሆን ተገምቷል።

እንዲህ ብዙ የተወራለትና በብዙ ትግልና ሕዝብ የነቃ ተሳትፎ እየተገነባ ያለው የዓባይ ግድብ ወደ መጠናቀቂያ ምዕራፉ እየተጠጋ ነው። በለውጡ መንግሥት ቁርጠኝነትና በሰፊው ሕዝብ ተሳትፎና ያላሰለሰ ጥረት የግድቡ ግንባታ ሊጠናቀቅ እነሆ ሰባት ወራት ብቻ እንደቀሩት ተነግሯል።ሕዝቡም የኔ ነው ብሎ የሚጠራው የዓባይ ግድብ ተጠናቆ ብርሃኑን ለማየት በጉጉት እየተጠባበቀ ይገኛል። ዓባይም የዘመናት የሕዝብ ቁጭትን አስረስቶ መላው ኢትዮጵያውያንን ሊክስና ብርሃን ሊሰጥ ተዘጋጅቷል።

ታዲያ በቀሩት የሰባት ወራት ጊዚያት ውስጥ መንግሥት ከዚህ በፊት ያሳየውን ቁርጠኝነት በመድገም ግድቡ በተባለው ጊዜ ግንባታው እንዲጠናቀቅ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። የግድቡን ግንባታ ከግብ በማድረስ ሕዝቡ በጉጉት የሚጠብቀውን የልማት በረከት እንካችሁ ማለትና ማስደሰት ይጠበቅበታል። በተለይ አሁንም ያላባራውንና ከግብፅና ከሱዳን በኩል የግድቡን ሥራ ለማስተጓጎል እየተሸረበ ያለውን ሴራ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ማክሸፍ ይኖርበታል። ለግድቡ ግንባታ የተመደበውን ገንዘብም በአግባቡ ማዋል ይጠበቅበታል።

ሕዝቡም ቢሆን የዓባይ ግድብ ገና የመሠረት ድንጋይ ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ በገንዘቡ፣ በጉልበቱ፣ በሞራሉ፣ በእውቀቱ ወዘተ ድጋፉን በማሳየት ባለውለታነቱን አሳይቷል። ምን ያህል በጋራ የመልማት ፍላጎት እንዳለውም አስመስክሯል። የግድቡን ግንባታ ሥራም እዚህ ደረጃ ያደረሰው ይኸው ከእለት ጉርሱ ላይ ቀንሶ አስተዋፅኦ ያደረገው ድንቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ዛሬም የግድቡ ሥራ ተጠናቆ ከግድቡ የሚጠብቀውን በረከት ለማግኘት አሁንም በሁለንተናዊ መልኩ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ግድቡ ሊጠናቀቅ ጥቂት ጊዚያት ብቻ ናቸውና የቀሩት ወገቡን ጠበቅ አድርጎ ለግድቡ ሥራ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል።


የግድቡ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ዓባይ የኢትዮጵያውያን ብርሃን ይሆናል። ዓባይ ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አቅም፣ ጉልበት፣ ችሎታና ገንዘብ እንዲህ ዓይነት ግዙፍ ፕሮጀክቶችን መገንባትና ለዓለም ማሳየት እንደሚችሉ ቋሚ ምስክር ይሆናል። ዓባይ ኢትዮጵያውያንን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ዓባይ ኢትዮጵያውያን በሌሎችም ወንዞቻቸው ላይ አልምተው መጠቀም እንዲችሉ መንደርደሪያ ይሆናል። ዓባይ ኢትዮጵያውያን መጪው ጊዚያቸው የፈካ ብርሃን እንዲሆንም ብርሃን ይሆናቸዋል። እውነትም ዓባይ ብርሃን ነው!!





# “የሕዳሴ ግድባችን ታዳሽ ኃይል በመሆኑ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገት መሠረት ነው”

ብርሃኑ ደኑ (ዶ/ር)
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በንግድ ሥራ ኮሌጅ የኢኮኖሚክስ መምህር



አስቴር ኤልያስ

ዛሬ የመሠረተ ድንጋይ ከተቀመጠለት 13ኛ ዓመቱን ደፍኗል - ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ፈተናን በመጋፈጥ የዘለቀ ቢሆንም፤ በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፎ ወደ ፍጻሜው መቃረብ ችሏል። ይህ የሆነው ግን በኢትዮጵያውያኑ ብርታትና ጥንካሬ እንዲሁም መንግሥት አይተኬ ሚናውን በአግባቡ መወጣት በመቻሉ ነው። የኢትዮጵያውያኑ ማንነት እና ታሪክ የሆነው የሕዳሴ ግድብ፣ ሲጠናቀቅ የወራት ያህል ጊዜ ብቻ ቀርተውታል። በቅርቡ የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት እንዳስታወቀውም የግድቡ ግንባታ አፈጻጸም በአማካይ 95 በመቶ ደርሷል። የግድቡ አጠቃላይ የሲቪል ሥራው ደግሞ 98 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ መከናወኑም ተጠቅሷል።

ይህ ወደ ፍጻሜው የተንደረደረው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፣ እዚህ ደረጃ ላይ ስለመድረሱ የኢትዮጵያን መንግሥት እና የዜጎቿን ቁርጠኝነት የሚያመላክት ነው። ግብጽን ጨምሮ ምዕራባውያኑም ሆኑ ሌሎች አካላትም ሆኑ ተቋማት በዚህ ግድብ ያልወረወሩት የተንኮል ጠጠር አልነበረም። ከማስፈራራት እስከ ማስጠንቀቂያ፤ ከማሸማቀቅ እስከ ማጭበርበር ድረስ ትልልቅ ናቸው የሚባሉ ሀገራት ጭምር በኢትዮጵያ ላይ ያደረሱት ደባ ታሪክ ሆኖ በትውልድ አዕምሮ ተመዝግቧል።

ይሁንና ኢትዮጵያ በዚህ የሕዳሴ ግድብ ያስመዘገበችው ድል በብዙ ጉዳዮቿ ላይ ጨክና መጨረስን ብቻ ሳይሆን በቀጣይም ተመሳሳይ ቁርጠኝነትን ማሳየት የምትችል መሆኗንም ጭምር ነው።

ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ምንም እንኳ ኢትዮጵያ በፈለገቻቸው በቁርጥ ቀን አብረዋት ስመሆን ፈጣኖች ባይሆኑም ከኢትዮጵያ ጥንካሬ እና የ—ይቻላል“ መንፈስ ብዙ የሚማሩበት ዕድል እንደሆነ ይታወቃል። የግድቡ መጠናቀቅ ስኬቱ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የእነርሱም ጭምር እንደሆነም የተረዱ ይመስላል።

አዲስ ዘመንም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠለትን 13ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ የሚኖረው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ምንድን ነው? ሲል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በንግድ ሥራ ኮሌጅ የኢኮኖሚክስ መምህር ከሆኑት ከብርሃኑ ደኑ (ዶ/ር) ጋር ልዩ እትሙን አስመልክቶ ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቦታል። መልካም ንባብ ተመኘንላችሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በሰባት ወር ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተገልጿል፤ ይህን እንዴት ያዩታል? ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውስ እንደምን ይገለጻል?**

**ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ብዙ ውጣ ውረድን አልፎ የተጋረጡበትንም ፈተናዎች ተሻግሮ ወደ ምረቃ ምዕራፍ መሸጋገር መቻሉ ከምንም በላይ ትልቅ ስኬት ነው። ብዙዎች ይህ ግድብ እውን እንዳይሆን በብዙ ጥረው የነበረ መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም።

ይህ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለምረቃ መቃረቡ አንድ ትልቅ ስኬት ሆኖ ሳለ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እና ያንን በአግባቡ መጠቀም መቻል ደግሞ ለኢኮኖሚው ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው ነው። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምናያቸው የበለጸጉ ሀገሮች ሁሉ በከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል የተደራጁ ናቸው። ምርቶቻቸውንም በዚሁ ባላቸው የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመርቱና ለተደራሻቸውም የሚከፋፍሉ ናቸው።

በርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የተለያየ የኃይል ምንጭ ነው። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የሚመረጠውና እና ለብክለትም የማያጋልጥ ከውሃ የሚገኝ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዓይነት ሲሆን፣ ጠቀሜታውም ዘርፈ ብዙ ነው። ከዚህ አንጻር አንደኛው ለኢኮኖሚ የሚጠቅመውን የአካባቢ ጥበቃ የሚመለከት ነው። እንዲህም ሲባል አየሩንም ከብክለት የሚከላከል እና ነፃ የሚያደርግ መሆኑ ነው።

ሁለተኛው ደግሞ እንደሚታወቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ታዳሽ ነው። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይል አቅርቦቱ ታዳሽ ኃይል እንዲሆን የሚበረታታበት ጊዜ ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የሚፈልገው ውሃ ነው፤ ውሃ ደግሞ ከዝናብ ይገኛል፤ ሁሌም ቢሆን ዝናብ ይዘንባል። ግድቡ ያለምንም ችግር መልሶ መሙላት ይችላልና ታዳሽነቱ በዚሁ መልኩ የሚቀጥል ይሆናል።

ስለዚህ እንደሌሎች ለምሳሌ እንደ ነዳጅ ማውጣት ዓይነት የኃይል አማራጭን ብንመለከት በሂደት እያለቀ የሚሄድ የኃይል ምንጭ ነው። ከዚህ የተነሳ ሀብቱ የሚያልቅ በመሆኑ ወደፊት ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ትልቅ ጥያቄ የሚያስነሳም ጭምር ነው። ይህ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዓይነት ታዳሽ ኃይል ለወደፊቱ የኢኮኖሚ ቀጣይነት ዓይነተኛ የኃይል ምንጭ ነው። በአጭሩ የሕዳሴ ግድባችን ታዳሽ ኃይል በመሆኑ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገት መሠረት ነው።

ይህ ብቻም ሳይሆን የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽልና ቀጣይነት እንዲኖረው ከማድረግ አንጻር አስተዋጽኦው ከፍ ያለ ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያውያኑ ጥንካሬ የተገነባው እና ሊጠናቀቅ ጫፍ ላይ የደረሰው የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ለዘመናት ወደኋላ ቀርቶ የነበረውን የኢኮኖሚ እድገት እና ግስጋሴ ወደፊት ለማስፈንጠር ሚናው የጎላ ነው። ሀገሪቷ ልታድግ የምትችልበትን፣ ምርታማነት የሚጨምርበትን፣ በከፍተኛ ደረጃ የሥራ እድል የሚከፈትበትንም እድል የሚፈጠር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሲጠናቀቅ አንዱ ጠቀሜታው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ነው፤ ከዚህ አንጻር የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል የሚቻለው እንዴት ነው?**

**ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** የኢኮኖሚ እድገት እና ጠቀሜታ ማለት አንደኛ የሕዝብን ኑሮ የሚያሻሽል እንደ ማለት ነው፡። የሕዝብ ኑሮ ማሻሻል ሲባል ደግሞ የሥራ እድልን መክፈት ነው። የሥራ እድል ተከፈተ ማለት ደግሞ የገቢ ምንጭ ተገኘ እንደማለት ነው። ገቢን ከፍ ለማድረግ ዋነኛው መሠረት የሆነው ምርታማነትን መጨመር እና ማበራከት ነው።

በኢኮኖሚ ሴክተሮች ወይም በሁሉም ክፍለ ኢኮኖሚዎች ማለትም በአገልግሎት መስጫ፣ በኢንዱስትሪ እና በግብርናው ዘርፍ ላይ ሁሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ዛሬ ዛሬ በከፍተኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው። ዘርፎቹም በተሳለጠ ሁኔታ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ኃይል ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው ነው።


ከዚህ ጎን ለጎን ቀጣይነት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት መቻል ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸውን የምርት ዓይነቶች በተገቢው መንገድ ማምረት እንዲችሉ ያደርጋል። በየኢንዱስትሪው እና በየፋብሪካው ያሉ ማሽኖች የምንጠቀምባቸው በኤሌክትሪክ ኃይል ነው። ስለዚህም እነዚህ ሁሉ ቀጣይነት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገኙ ማለት በጣም ከፍተኛ የሆነ ምርታማነትን ማምጣት ያስችላቸዋል።

**ሕ**ዳሴ ግድብ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ለዘመናት ወደኋላ ቀርቶ የነበረውን የኢኮኖሚ እድገት እና ግስጋሴ ወደፊት ለማስፈንጠር ሚናው የጎላ ነው። ሀገሪቷ ልታድግ የምትችልበትን፣ ምርታማነት የሚጨምርበትን፣ በከፍተኛ ደረጃ የሥራ እድል የሚከፈትበትንም እድል የሚፈጠር ነው

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ ብዙ የሥራ ዕድል ያገኛሉ። እንዲህም ሲባል ኢኮኖሚው እያደገ ሲሄድ በርካታ ሰዎች ሥራ አጥ ተብለው ከተፈረጁበት ቋት ውስጥ መውጣት ይችላሉ። የተፈጠረው የኢኮኖሚ መስክ በራሱ በርካታ ሰዎችን ፈላጊ ይሆናል።

ይህ ማለት ተምረው ሥራ አጥተው የተቀመጡ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል





# “የሕዳሴ ግድባችን ታዳሽ ኃይል በመሆኑ ቀጣይነት. . .

**ከ6ኛው ገጽ የዞረ**

ዜጎችን ወደ ሥራው መስክ እንዲገቡ የሚያደርግ ይሆናል። በርካቶች በሥራ መስክ ተሰማሩ ማለት ገቢ አደገ እንደ ማለት ነው። የግለሰብ ገቢ ሲያድግ የራሱ የግለሰቡን ገቢ ከማሻሻል አልፎ በሀገር ደረጃ የመንግሥት ገቢ ከፍ ለማድረግ የራሱ አስተዋጽኦ አለው። ምክንያቱም ዜጎች ሥራ አግኝተው መሥራት ሲጀምሩ ታክስ ከፋይ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ለመንግሥት ገቢ የሚያበረክተው የራሱ የሆነ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። ዜጋውም ሀገርም ተጠቃሚ ሆኑ ማለት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ የተያያዘ እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሥራ እድል ማስገኘት በተጨማሪ በሌላ በኩል ያለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውስ እንዴት ይገለጻል?**

**ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** ጠቀሜታው ከሥራ ማስገኘት ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም፤ ምርት ማትረፍረፍ ወይም ምርት ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ፋይዳዎችም አሉት። እንደሚታወቀው ደግሞ በአሁኑ ወቅት የግብይትም ሆነ የሽያጭ ሥርዓታችን እንደቀደመው ዘመን ሆኖ የሚዘልቅ አይደለም። ዛሬ የምንጠቀምባቸው የግብይት ሥርዓቶች ለምሳሌ ዲጂታል (Digital) ገበያ እና ክፍያ ኤሌክትሪክ ከሌለ ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም። ከኤሌክትሪክ ኃይል ውጭ ምንም ማድረግ አይቻልም።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በከፍተኛ ደረጃ ኤሌክትሪክን ሳይቆራረጥ እና በተሳካ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውል ኃይል ማምረቱ እና ማመንጨት መቻሉ ከፍተኛ የሆነ የግብይቱንም ሥርዓት ዘመናዊ የሚያደርግ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የክፍያ ሥርዓታችንንም የሚያዘምን ነው። በባንኮች ደረጃ የሒሳብ አያያዝ እና አገባብ ሪፖርት የማድረጉን ተግባር በተቀላጠፈ መንገድ እንዲካሔድ ያሉንን የዲጂታል (Digital) መስመሮችን ሁሉ ሳይቆራረጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ነው ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ በኢኮኖሚው መስክ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በየጊዜው እየተቆራረጠ የሚያስቸግረውን የኤሌክትሪክ ኃይል ቀጣይነት እንዲኖረው ስለሚያደርግ በተለያየ የሥራ መስክ የተሰማራውን ሴክተር ሁሉ እፎይታ የሚሰጥ ይሆናል። ለምሳሌ በትምህርት ቤት አካባቢ እና በጤና ተቋማት አካባቢ በርካታ ማሽኖች ይኖራሉ። እነዚህ ሁሉ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሹና በዚያው ኃይል የሚንቀሳቀሱ ናቸው። እነዚህ ትልልቅ እና በጤናውም፤ በትምህርቱም ዘርፍ ሰፊ አገልግሎት የሚሰጡ ሴክተሮችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለውን የኤሌክትሪክ ኃይል ለማግኘት የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ተጠናቅቆ ወደሥራ መግባት እጅግ አስፈላጊው ጉዳይ ነው።

የአንድ ሀገር ዜጋ ጤና ተጠበቀ ማለት በኢኮኖሚው ዘርፍ ለሚሰራው ሥራም ሆነ ለኢኮኖሚው ደኅንነት ጠቃሚ ነው። ከዚህ አንጻር ኢኮኖሚው ከሁሉም ጋር የተያያዘ በመሆኑ የኢኮኖሚው ደኅንነት ተጠበቀ ማለት የብዙዎች ደኅንነት ተጠበቀ እንደማለትም ነው። ምክንያቱም ኢኮኖሚው ከትምህርት ሴክተሩም ጋር የተያያዘ ነው።

በቂ እና እጅግ በጣም የሚጠቅም የትምህርት ሥርዓትንም ለማካሔድ የኤሌክትሪክ ኃይል በስፋት መገኘት እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። ለዚህ ሁሉ መሠረት የሚሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ እና ለምረቃ መብቃት እጅግ በጣም በጉጉት የሚጠበቅ ነው። በተለይም እንደ ምጣኔ ሀብት መምህርነቴ ሳጤነው ለኢትዮጵያ አንድ ትልቅ የታሪክ ምዕራፍ ሆኖ ሊቆጠር የሚገባው ነው።

ምክንያቱም ባለፉት ዓመታት ለረጅም ዘመናት ይህን ዓይነት እድል ማግኘትም ሆነ ይህንን ዓይነት ሥራ ማሳካት አልተቻለም ነበር። ያለፈው ታሪካችን ይህንን ማሳካት አልቻለም።

የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ ትራንስፖርት ላይ ከፍተኛ የሆነ በጎ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ለነዳጅ የምናወጣውን ወጪ ልንቀንስ የምንችለው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም ስንችል ነው። ለዚህ ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል የግድ ነው። የሚጠናቀቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እንደዚህ ዓይነቱ ኃይል የሚሻ መኪናን ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት እንድንጠቀም የሚያግዝ ነው።

**በአሁኑ ወቅት በየጊዜው እየተቆራረጠ የሚያስቸግረውን የኤሌክትሪክ ኃይል ቀጣይነት እንዲኖረው ስለሚያደርግ በተለያየ የሥራ መስክ የተሰማራውን ሴክተር ሁሉ እፎይታ የሚሰጥ ይሆናል**

ኢኮኖሚው ደግሞ ሁሉንም ሴክተር የሚነካ ነው። ኢኮኖሚው ፖለቲካውንም ሆነ አመለካከታችንንም ጭምር የሚነካ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ወደመጠናቀቁ መቅረብ መቻሉ በቀላሉ ታይቶ የሚታለፍ አይደለም። በተለይ ደግሞ የዚህ ታላቅ ግድብ መጠናቀቅ፣ ለመጪው ትውልድ ከፍተኛ የሆነ የታሪክ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

እንዲያውም ይህ ታላቅ ግድብ የታሪክ ማርሽ ቀያሪ ነው ማለት ይቻላል። የአሁኑ ትውልድ በርከት ያለ ፈተና እና ተግዳሮትን አልፎ የሠራው ሲሆን፣ በዚህ ሥራው ደግሞ በሌላ ሌላውም ተጠቃሚ መሆኑ እንዳለ ሆኖ በኢኮኖሚው መስክ የበለጠ ተጠቃሚ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ መጪው ትውልድ ሊናገርለት የሚችለው ትልቅ ታሪክም ጭምር ነው። በመሆኑም በቀጣይ እየተወሳ የሚዘልቅ ግድብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እውን ሆኖ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚው ዘርፍ ተጠቃሚ እንዳትሆን የነበረው ፈተና በዋናነት ስምን ይመስልዎታል?**

**ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** ምክንያቱም እንዳናድግ ስለሚፈልጉ ነው፤ ብዙዎቹ እኛ ኢትዮጵያውያን የምናገኘውን የኢኮኖሚ እድገት እና እሱን ተከትሎ የሚመጣ አቅም እንዳይኖር መፈለጋቸው ነው። እንዲሁም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እንዳይሳካ በብዙ ሲጥሩ የነበረው እንደ ሀገር የሚገኝ ተሰሚነት እንዳናገኝ ስለሚፈልጉ ነበር። በርግጥ ይህ ታላቅ ግድብ የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠለት ጀምሮ እስካሁኗ ሰዓት ድረስ በብዙ ሲታትሩ እንደነበር የሚታወቅ ነው።

ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ደግሞ ‘ሀገሩ የእኔም ጭምር ነው፤ የሀገሬ እድገት እኔንም ይመለከተኛል። ሀገሬ አደገች ማለት የነገው ትውልድም ሆነ የልጅ ልጆቼም እድገት ነውና የእኔም የትውልድም ታሪክ ነው’ ብሎ የሚያስብ ማንኛውም ሰው በጉጉት የሚጠበቀው ግድብ ነው። ከዚህ የተነሳ አስፈላጊውን ድጋፍም የሚያደርግለት ነው።

ይህ ታላቅ ግድብ ደግሞ ክፉ ነገር እንዳይደርስበት ሌት ተቀን መጠበቅ የግድ ይላል። ተግተው ከሚጠብቁት የኢትዮጵያ ልጆች፣ ከሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ ከአካባቢው ሕዝብ እና ሚሊሻም እንዲሁም ከመንግሥትም ጋር በመሆን እንደ ራስ ንብረት እና እንደ ራስ ሕይወት መከታተል እና ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ የሚጠበቅብን ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያውያን እና መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥተውት የገነቡት ግድብ ነው፤ ቀጣዩን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ያለ ሕዳሴ ግድብ ብናስብ ምን ዓይነት ኢኮኖሚ ይኖራታል ብለው ያስባሉ?**

**ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** ኢትዮጵያን ያለ ሕዳሴ ግድብ ብናስባት በትክክል የምንደግመው ያለፈውን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ ኋላቀርነትን ነው። በኢኮኖሚ ኋላቀርነት ማለት ለልመና ራስን መዳረግ እንደማለት ነው። ልመና ማለት ደግሞ እንደ ሀገር ሲሆን ከባድ ነው። ከዚህም በላይ ራስን በሌላ ሀገር እጅ ላይ እንደመጣል የሚቆጠር ነው። መለመን ማለት በሌሎች ድጋፍ ተመርኩዞ መንቀሳቀስ ማለት ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያን ያለ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ማሰብ በጥቅሉ ያለፈውን በኢኮኖሚው በኩል የነበረውን ደካማ ታሪካችንን መድገም ነው። ርግጥ ነው ከዚህ ውጭ የሆኑ ጥሩ ጥሩ የሆኑ ታሪኮች እንዳሉን የሚታወቅ ነው፤ በብዙዎችም ዘንድ ሲነገር ይደመጣል። ነገር ግን እሱ ዓይነት ታሪክ ስላለን ብቻ ኋላቀር ከሆነው ኢኮኖሚያዊ ድኅነት ሊያላቅቀን አልቻለም።

አንዱ እና ትልቁ ነገር ከኋላቀርነታችን ሊያላቅቀን ያልቻለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማጣታችን ጭምር ነው። ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል የምንጠቀምባቸው የምርት መገልገያ መሳሪያዎችን ማንቀሳቀስ አንችልም። ፈጥነን በማምረት ተወዳዳሪነትን ማሳየት አንችልም። በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪነትን አሳይተን እና ገበያዎችን ሰብረን ገብተን የምናመርታቸውን እቃዎቻችንን በተሻለ ሁኔታ መሸጥ እና መገበያየት አንችልም።

በአሁኑ ወቅት ዓለም እየፈጠነ በመሄድ ላይ የሚገኘው አንዱ ትልቁ ነገር የተለያየ የኃይል ምንጭን በመጠቀሙ ነው፤ እንዲህም ሲባል ከፀሐይ፣ ከነፋስ፣ ከእንፋሎት እንዲሁም ከሃይድሮ ኤሌክትሪክ የሚገኘውን የኃይል ምንጭ በመጠቀም በመቻሉ ነው፡። በአሁኑ ወቅት በሀገራችንም ከተለያዩ የኃይል ምንጮች ኃይልን ለማግኘት እየተሠራ እንደሆነ ይታወቃል። ከፀሐይ የኃይል ምንጭ በማግኘት በኩል በይበልጥ እየተሠራ ያለ ሂደት አለ። በተመሳሳይ ከነፋስ ኃይልም በስፋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማግኘት እየተሠራ ይገኛል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከከርሰ ምድር በሚወጣ እንፋሎትም የኤሌክትሪክ ኃይል የማግኘቱ ሥራ እንዲሁ እየተሠራበት ያለ እንቅስቃሴ ሆኗል።

ከእነዚህ ሁሉ የምንጠቀመው የኤሌክትሪክ ኃይል አለ። ነገር ግን በአብዛኛው ከፍተኛ እና ጥሩ ነው ተብሎ የሚገመተው እና የሚታመንበት ከውሃ የሚገኝ ሃይድሮ ኤሌክትሪከ ኃይል ነው። ይህ ማለት ደግሞ በቅርቡ ፍጻሜውን አግኝቶ ይመረቃል ተብሎ የሚጠበቀው እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዓይነቱ ነው። ይህ የሕዳሴ ግድብ ደግሞ የሚመነጨው ኃይል ከፍ ያለ በመሆኑ ሊሰሩ የታቀዱ በርካታ ሥራዎችን በአግባቡ ማሳለጥ የሚያስችል አቅም ያለው ነው። ኢኮኖሚው እያደገ እና እየዳበረ ሲሄድ በሕዳሴ ግድብ ብቻ ተወስነን የምንቀር አይደለንም፤ ወደፊት የተለያዩ ግድቦችን ከመሥራት ባለፈ ኢኮኖሚያችንም እያደገ የሚመጣበት ጊዜ ይሆናል።

በርግጥ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጨዋታውን የሚቀየር (Game Changer) ግድብ ነው። ኢትዮጵያውያኑ የሠሩት ይህን ዓይነት ግድብ ነው። ስለሆነም ይህን ታላቅ ግድብ በሚገባው መጠን መጠቀም የሚጠበቅብን ነው። ግድቡ ኃይልን የሚያመነጭ ብቻ ሳይሆን አብሮ ጎን ለጎን መታሰብ ያለበት የኃይል ማስተላለፊያውን (Transmission) እና የሥርጭቱን (distribution) ጉዳይ በሚገባ ከተገኘው እና ከመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በማገናኘት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋሉ ተገቢ ነው።

ዋናው ነገር ማመንጨት ብቻ መሆን የለበትም። የተገኘውን የኤሌክትሪክ ኃይል አስፈላጊው ጥቅም ላይ በማዋል ውጤታማ መሆን መቻል ነው። ይህን ስናደርግ በትክክለኛው መንገድ መሆን አለበት። እንዲህ ማድረግ ስንችል ተበጣጥሶ የሚመጣን እና ተቆራርጦ የሚደርስን የኃይል ችግር ማስወገድ እንችላለን።

እንደዚያ ማድረግ ከቻልን ደግሞ ከእሱ ጎን ለጎን የኃይል ማስተላለፍ ዘዴዎችንን (transmission mechanism) እንዲሁም የማስተላለፊያ መስመሮችን ዘመናዊ ማድረግ የግድ ይለናል። በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀማችንንም እንዲሁ ልናዘምን ይገባናል፡

እንደሚታወቀው የኤሌክትሪክ ኃይልን በተመለከተ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት (Ethiopian Electric Utility) ነው። ይህ የአገልግሎት ጉዳይ አሁንም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ ድክመት እና ችግር ያለበት ነው። ስለሆነም ይህንን ድክመት በግልጽ አውጥቶ መናገር እና ማስተካከልን የሚጠይቅ ነው።

ይህ ተቋም የመነጨውን የኤሌክትሪክ ኃይል ሥራ ላይ እንዲውል አደረገ የሚባለው በየቤታችን፣ በየፋብሪካችን፣ በየኢንዱስትሪዎቻችን እና በተፈላጊ ቦታ ሁሉ ደርሶ ጥቅም ሲሰጥ ነው። ስለሆነም የዚህ አገልግሎት አጠቃቀም ሁኔታ መስተካከል አለበት ባይ ነኝ። ዋናው ጉዳይ ኃይል ማመንጨት ብቻ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። ርግጥ የሕዳሴ ግድቡን ገድበን ኃይል ለማመንጨት የሚያስችል ደረጃ ላይ መገኘት በራሱ በጣም በጎ ተግባር ነው፤ ኃይል በራስ አቅም ማመንጨት መቻል እጅግ በጣም ታሪካዊ ነገር ነው። በጣምም ትልቅ ስኬት ነው። አሁን ላለው ትውልድ እና በአሁኑ ሰዓት ላለው አመራር ሁሉ እጅግ በጣም ትልቅ ድል ነው። ይበልም የሚያሰኝ ነው። ነገር ግን ከዚህ ጎን ለጎን የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀሙ ላይ መሻሻል የሚገባቸው በሰው ኃይል ደረጃም ቢሆን በሌላ ሌላ አመራርም ቢሆን መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ መጠቀስ ያለበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ብርሃኑ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት



ልዩ እትም

# ‹‹ የዓባይ ግድብ -የአምራች ኢንዱስትሪው መድኅን ››

አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ



ስምስም መንግሥቱ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በመለስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ላይ የተሠማሩ ወደ 15 ሺ የሚሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች ይገኛሉ። አምራች ኢንዱስትሪዎቹ ለውጭና ለሀገር ውስጥ የሚቀርቡ ምርትና አገልግሎቶችን ሲያቀርቡ የነበረው በበቂ ሁኔታ ባልተሟላ የኃይል መሠረተ ልማት እንደሆነ አይዘነጋም።

በኃይል መቆራረጥና መሰል ችግሮች የማምረት ሥራቸው እየተስተጓጎለባቸው፣ ምርት መበላሸትም እያጋጠማቸው እንደሚቸገሩ በተደጋጋሚ ያነሱ እንደነበር ይታወቃል። ምንም እንኳን መንግሥት በተለያዩ አማራጮች አምራች ኢንዱስትሪው እንዲበረታታ በሚችለው ሁሉ ለመደገፍ ጥረት ቢያደረግም ሆኖም ያለው የኃይል አቅርቦትና የኢንዱስትሪው ፍላጎት ለማመጣጠን ሳይቻለው ቆይቷል።

በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብም ሆነ ኢንዱስትሪ መር የሆነ የምጣኔ ሀብት እድገት ለማስመዝገብ አስተማማኝ የሆነ የኃይል አቅርቦት ደግሞ ወሳኝ ነው። በሥራ ላይ ያለው አምራች ኢንዱስትሪ በኃይል አቅርቦት ያሳለፈው ተግዳሮት ታሪክ ሲሆን፤ በዘርፉ አዲስ ኢንቨስትመንትም ለመሳብ በኢትዮጵያ ምቹ ጊዜ ላይ ተደርሷል።

ለመጠናቀቅ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ የሚገኘው የህዳሴ ግድብ ለአምራች ኢንዱስትሪው ትልቅ እፎይታን እንደሚሰጥ ይጠበቃል። በሕዝብ ተሳትፎ ግንባታው ከዳር የደረሰው ታላቁ የህዳሴ ግድብ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፎ እንደሆነ አይዘነጋም። በተለይም ግብፅ የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠበት ጊዜ ጀምሮ በግንባታው የ13 ዓመታት ጉዞ ለማስተጓጎል ያልፈነቀለችው ድንጋይ የለም ማለት ይቻላል። ዓለምአቀፉን ማኅበረሰብ በማስተባበር ጭምር ኢትዮጵያ የገንዘብም ሆነ የተለያየ ድጋፍ እንዳታገኝ፣ ግንባታውንም ለማስቆም ብዙ ርቀት ተጉዛለች።

ኢትዮጵያ የማንንም ሉዓላዊ ሀገር መብት ሳትጋፋ፣ በጋራ የመጠቀም መብቷን ለማስጠበቅ፣ የዲፕሎማሲ ጥረቷን በአሸናፊነት ተወጥታለች። ኢትዮጵያ ይዛ የተነሳችውን የፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርሕ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ መልማት ለጎረቤት ሀገሮችም የሚተርፍ እንደሆነ በዲፕሎማሲ ሥራዋ አጠናክራ ቀጥላለች።

የዓባይ ግድብ ግንባታ የተጀመረበት 13ኛ ዓመት እና ለመጠናቀቅ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ መድረስ አስመልክቶ በተለይም የግድቡ መጠናቀቅ ያልተቆራረጠ አስተማማኝ የኃይል መሠረተ ልማት አቅርቦት ለሚያስፈልገው በተለያዩ ዘርፍ ላይ ለተሠማራው አምራች ኢንዱስትሪ የሚሰጠውን እፎይታ፣ አጠቃላይ የአምራች ኢንዱስትሪውን እንቅስቃሴ በተመለከተ ከኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን ፦ የዓባይ ግድብ ግንባታ ሲጠናቀቅ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ይገኛል፤ ይህንኑ በተመለከተ የተሰማዎትን ስሜት አስቀድመው ቢገልጹልን?**

**አቶ ታረቀኝ ፦** በቅድሚያ የዓባይ ግድብ ግንባታ ሊጠናቀቅ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ በመድረሱ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ደስ አላችሁ። እንኳን ደስ አለን! ለማለት እፈልጋለሁ። የግድቡ ግንባታ ከፍተኛ ድል የተገኘበት ወይንም ውጤት የተመዘገበበት ነው። ግንባታው እውን ወደመሆን መቃረቡ፤ ደስታውና ኩራቱ ከፍ ያለ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ከተባበርንና አንድ ከሆንን አዲስ ነገር መሥራት እንደምንችል በተምሳሌነት የሚጠቀስ ግድብ ነው።

የሁላችንም ኢትዮጵያውያን ዐሻራ የታየበት፣ የሁላችንም ስኬት ነው። ለልጆቻችን፣ ለልጅልጆቻችን ትልቅ የሆነ ሐውልት ማስቀመጥ ችለናል። ከዚህ የተገኘው ልምድ ደግሞ እንደሀገር፣ እንደዜጋ፣ ታላላቅ የሆኑ ነገሮችን መሥራት እንደሚቻል ያሳያል። ስለ ዓባይ ብዙ ተብሏል። በተለያዩ የሙዚቃ ባለሙያዎችም ተዘፍኖለታል። ግን እንደሀገር ሳንጠቀምበት ቆይተናል።

ታሪክን ወደኋላ መለስ ብለን ብናስታውስ፤ ኢትዮጵያ የዓባይ መገኛ ሆና እያለ፤ እንዳትጠቀም በሕግ ለመገደብ ጥረት ተደርጓል። ግብፅ እና በተወሰነም ሱዳን ውሃውን ለሁለት በመክፈል የራስ የማድረግ ሁኔታ ነው የነበረው። ይህን ኢ-ፍትሐዊነት ሰብሮ ለመውጣት የተለያዩ ተግዳሮቶች ነበሩ። የአቅም ውስንነቱም ሌላው ፈተና ነበር። ኢትዮጵያ ከሌሎች የገንዘብ ብድር አግኝታ የራስዋ የሆነውን የውሃ ሀብት ለልማት እንዳታውል በተለይም ግብፅና የግብፅ ወዳጆች ከፍተኛ ጫና ለማሳደር ተንቀሳቅሰዋል።

ጫናው ግን ኢትዮጵያ ግድቡን ለመገንባት ያደረገችውን መነሳሳትና መነቃቃት ወደኋላ አላስቀረውም። ብድርም ሆነ ድጋፍ ለማግኘት የማንንም ደጅ መጥናት ሳያስፈልጋት ዜጎችን በማስተባበር በራስ አቅም መሥራት መቻሏን አሳይታለች።

ዜጎች በቂ ገቢ ሳይኖራቸው፣ መንግሥት ሠራተኛውም የተሻለ ክፍያ ሳይኖረው፣ በተለያየ የዓለም ሀገር የሚኖረው ትውልደ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊ ለግድቡ ቅድሚያ በመስጠት በጋራ ተረባርቦ ከዳር ያደረሰው ነው። ይሄ ትርጉሙ ለእኛ ኩራት ሊሆን ይችላል። ግድቡን እንዳንገነባና እንዳንጠቀም ጥረት ሲያደርጉ ለነበሩ ኀዘን ነው።

**አዲስ ዘመን፦ የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ ሀገራዊ አቅምን በመፍጠር በኩል ያለው ድርሻና አያይዘውም የግድብ ግንባታው እንደ ሀገር የወደብ ባለቤት ለመሆን እየተደረገ ሳለው ጥረት የሚፈጥረውን አቅም ቢገልጹልን?**

**አቶ ታረቀኝ ፦** ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛትም ሆነ ወደ ኢኮኖሚ ሊለወጥ የሚችል ሀብት ባለቤት ሆና ወደብ የሌላት በዓለም ላይ የመጀመሪያ ሀገር ናት። የግድቡ መጠናቀቅ ደግሞ ሀገራዊ አቅማችንን ያሳድግልናል። በተለይም በጂዲፒ ያለንን ድርሻ ከፍ ያደርግልናል። እንደ ኅብረተሰብ ደግሞ አብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ያስችላል።

ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብን የገነባችው ሌላውን ለመጉዳት ሳይሆን የኃይል አቅርቦት ክፍተቷን ለመሙላት ወይንም በውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጭቶ ለመጠቀም ነው። የወደብ ባለቤት ለመሆን ከሶማሊላንድ ጋር በሰጥቶ መቀበል ስምምነት ስትፈራረም እንዲሁ ሌላውን ለመጉዳት አይደለም። የወደብ አማራጮችን በማየትና የዓለም አቀፍ ሕግንም መሠረት በማድረግ ለመጠቀም እየተንቀሳቀሰች ነው ።

ኢትዮጵያ ለወደብ የምትከፍለው ክፍያ ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ የክፍያ ሁኔታ በየጊዜው መቀያየሩ የወጭ ምርትና የገቢ ምርት ተገማች እንዳይሆን እያደረገው ነው። የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያ እንዲጨምር ያደርጋል። የዋጋ መለዋወጥ ኢንቨስትመንትን በማዳከም ጉዳት ያስከትላል። አሁን ባለው አሠራር ለመጓጓዣ የሚወጣው ወጪ፣ ተጓጉዘው የመጡት እቃዎች ወደብ ላይ ለሚቆዩበት የሚከፈለው ክፍያና ተያያዥ የሆኑ ነገሮች የዋጋ ንረት (ኢንፍሌሽን) እያስከተሉ ነው። ስለዚህ በኑሮ ውድነት ውስጥ የራሱ ድርሻ አለው። በዚህም ተጎጂ የሚሆነው ተጠቃሚው ነው።

የራስ የሆነ የወደብ አገልግሎት መኖር የኑሮ ውድነትን በመቀነስ፣ የራስን ወጪና ገቢ ምርት ለመቆጣጠርና ግምታዊ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ ለማውጣት ከማስቻሉ በተጨማሪ፤ የሀገር ሉዓላዊነትንም ለማስጠበቅ የራሱ ድርሻ አለው። በሌላ ሀገር ወደብ ተጠቅመን የምናስገባው ዕቃ በሙሉ ስለሚፈተሽ (ስክሪን ስለሚደረግ) እንደሀገር በምስጢር ልንጠብቀው የምንፈልገው ነገር እንኳን ቢኖር አንችልም። ይሄ ደግሞ የሀገር ሉዓላዊነትን ይዳፈራል። የሀገር ደኅንነትን ስጋት ላይ ይጥላል። ከዚህ አንጻር ነው የወደብ ባለቤት መሆን ጥቅሙ የትየለሌ ነው።

የወደቡ አስፈላጊነት ከኢንዱስትሪው አንጻርም ሲቃኝ፤ ምንም እንኳን ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪ የሚያደርገው የኃይል አቅርቦት ቢሆንም፤ ወደቡም ምርትና አገልግሎትን ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ ወደሀገር ለማስገባት ወሳኝ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፦ አምራች ኢንዱስትሪው ለዓባይ ግድብ ግንባታ የነበረው አበርክቶ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ታረቀኝ፦** ለግድቡ ግንባታ የኢትዮጵያ ባለሀብት ቦንድ በመግዛት፣ በስጦታም በማበርከት ያደረገው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው። ትልቅ ምስጋናም ያስፈልገዋል።

**አዲስ ዘመን፦ የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱን ታሳቢ በማድረግ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የተያዘ እቅድ አለ?**

**አቶ ታረቀኝ፦** እንደ ሀገር ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ ኢንዱስትሪ ነው። እንደ አንድ ዘርፍም ሲታይ ፋይዳዎች አሉት። ከፋይዳዎቹ አንዱ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ነው። በአነስተኛ መሬት ላይ የተቋቋመ ኢንዱስትሪ ብዙ የሰው ኃይል የሚይዝ በመሆኑ ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጠራል።

የተመረተውን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ ሁለተኛው ፋይዳ ነው። ተኪ ምርት በማምረት ከውጭ የሚገባውን በማስቀረት በከፍተኛ ሁኔታ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማዳንም ሌላው ነው። ለሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (ጂዲፒው)ም ድርሻ አለው። የኋላ ታሪካችን እንደሚያሳየው ከነዳጅና የተለያዩ ማዕድናት ከሚገኝ ገቢ ካልሆነ በስተቀር አብዛኞቹ ሀገሮች በኢኮኖሚ ያደጉበት መሠረታቸው ኢንዱስትሪ ነው። ኢትዮጵያ በጂዲፒ ያላት ድርሻ በኢንዱስትሪ ዝቅተኛ ነው። ከሰባት በመቶ በታች ነው። አብዛኛው በግብርና ነው። ከዚህ ካለፈም በአገልግሎት ነው። ስለዚህ ለሀገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (ጂዲፒ) ድርሻ ኢንዱስትሪው በጣም ማደግ ይኖርበታል። ማደግ ካለበት ደግሞ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ኢንዱስትሪው ላይ ይጠበቃል። አሁን ባለው የውጭ ምንዛሪ እየተገኘ ያለው የመጀመሪያ ከሚባለው የግብርና ምርት ነው። ምርቱ የሚቀርብላቸው እሴት ጨምረው በእጥፍ ዋጋ እያገኙበት ነው። በራሳችን እሴት ጨምረን ማቅረብ ብንችል ተጠቃሚ እንሆናለን። ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም ጥቅሙ ይጨምራል።

መንግሥት አምራች ኢንዱስትሪው እንዲያድግ ቁርጠኛ ሆኖ እየሠራ ነው። በአሁኑ ጊዜም በገበያ የሚመራ ኢንዱስትሪ እንዲኖር ግልጽ የሆነ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ አዘጋጅቷል። በገበያ የሚመራ ኢንዱስትሪ ማለት የተገልጋዩን ወይንም የሸማቹን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ምርት እንዲያመርት ማለት ነው። ምክንያቱም ኢንዱስትሪው ካመረተ በኋላ ገዥ ከሌለው፣ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ቴክኖሎጂ ማሻሻል ካለበት ያሻሽላል። ምርት መቀየር ካለበትም ይቀይራል። ሁልጊዜም ገበያው

ወደ ገጽ 9 ዞሯል



# « የዓባይ ግድብ -የአምራች. . .

**ከ8ኛው ገጽ የዞረ**

የሚመራው መሆን ይኖርበታል።

ሌላው ኢንዱስትሪን ከግብ የሚያደርሰው የግሉ ዘርፍ (ፕራይቬት ኦርየንትድ) መሆን አለበት። ምክንያቱም መንግሥት ግልጽ ሚና ይኖረዋል እንጂ ኢንዱስትሪ ውስጥ እራሱ ገብቶ ሊያሳካ አይችልም። ስለዚህ መንግሥት ብሔራዊ ወይንም ሀገራዊ ባለሀብት ላይ ትኩረት አድርጎ የመደገፍ ሚና ነው የሚወጣው። ኢንደዱስትሪው የሚፈልገውን ነገር ማሻሻል፣ በተለይም ከባቢያዊ ሁኔታ የሚፈጥረውን ምቹ ሁኔታ መጠቀም ይገባል።

ይሄ ማለት የፋይናንስ፣ የኃይል፣ የመሬት፣ የግብዓት የሠለጠነ የሰው ኃይል ኢንዱስትሪው በሚፈልገው ጊዜ ማቅረብ ማለት ነው። አሁን ላይ የፋይናንስ አቅርቦቱ ወደ ግል እየሄደ ነው። ይሄ ጥሩ ነው። ፖሊሲውም ያበረታታል።

አምራች ኢንዱስትሪው በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ መደገፍ ይኖርበታል። ጥናትና ምርምርም ማካሄድ ይጠበቅበታል። ትላልቅ የሚባሉት ኢንዱስትሪዎች የራሳቸው ጥናትና ምርምር ማዕከል አላቸው። የራሳቸው የሆነ የምርት ፎርሙላ አላቸው። ለአብነት የኮካኮላ አምራች ኢንዱስትሪን ብንወስድ በጥናትና ምርምር ያገኘው የራሱ የሆነ ፎርሙላ አለው። ለማንም አይሰጥም። የመንግሥት ተቋማት የሚያደርጉት ጥናትና ምርምር ቢኖርም ኢንዱስትሪዎቹ በራሳቸው የሚያከናውኑት ጥናትና ምርምር አላቸው። ስለዚህ ኢንዱስትሪዎቹ ጊዜው ከሚጠይቀው ጋር የሚራመድ ቴክኖሎጂ እንዲኖራቸው፣ አዲስ ስልተምርቶችን መከተል እንዲችሉ የመደገፍ ሥራ መሥራትም ይጠበቃል።

የኢንዱስትሪ እድገቱ አንዴ ከፍ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ ማለት የለበትም። ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለው፣ አካታች የሆነ የኢንዱስትሪ እድገት ነው መኖር ያለበት። ስለዚህ አዲስ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል። ይህን መነሻ ያደረገ ስትራቴጂም ተዘጋጅቷል። ከስትራቴጂው አንዱ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ነው። ተኪ ምርት ከውጭ ሀገር የሚገቡ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር በማምረት መጠቀም ማለት ነው። መጠቀም ብቻ ሳይሆን፣ በሀገራችን ምርትም መኩራት ያስፈልጋል። ስትራቴጂው ስኬታማ እንዲሆን መሥራት ይጠበቅብናል።

ኢንዱስትሪዎቹ በጥራት፣ በዋጋ፣ በጊዜ ተወዳዳሪ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህ ረገድ አበረታች የሆኑ ለውጦች እየታዩ ነው። ጅምሩን እየሰፋ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል። መንግሥት በስትራቴጂ መደገፍ፣ መሻሻል ያለበትን ሕግና አሠራርንም ያሻሽላል። ሰሞኑን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያስቀመጠው አቅጣጫ ለኢንዱስትሪ ዘርፉ ትልቅ መነቃቃትን የሚፈጥር ነው።

አቅጣጫው የመንግሥት ግዥዎች ከሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲፈጸም የሚል ነው። አብዛኛውን ግዥ የሚፈጽሙት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ናቸው። ስለዚህ ግዥውን ከሀገር ውስጥ አምራቾች ሲፈጽሙ፣ኢንዱስትሪዎቹ በተሻለ ጥራትና አቅርቦት ለመወዳደር ያስችላቸዋል። ውሳኔው ለአምራች ኢንዱስትሪው ትልቅ ዕድል ነው ።

ለሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ ይሰጥ ማለት ጥራት የሌለውንም መንግሥት ይወስዳል ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። ዕድሉ የተሻለ ጥራትና ዋጋ ላላቸው፣ በጊዜው ማቅረብ ለሚችሉ ነው። አሁን የተፈጠረው ምቹ ሁኔታ የአምራች ኢንዱስትሪው ለረጅም ጊዜ ሲያቀርበው የነበረው ጥያቄ ነው። የአምራች ኢንዱስትሪውን ቅሬታንም ይፈታል።

**አዲስ ዘመን፦ አምራች ኢንዱስትሪውን እየፈተኑት ያሉት ወይንም እያጋጠመው ያለው ተግዳሮት በዋናነት ምንድነው? ከፍተኛ ኃይል የሚፈልገው የኢንዱስትሪ ዘርፍስ ተለይቷል? አምራች ኢንዱስትሪውስ ምን ያህል ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፤** አምራች ኢንዱስትሪው ተግዳሮቶቹ የተለያዩ ናቸው። ከዚያ ውስጥ የኃይል አጠቃቀም አንዱ ነው። የኃይል አጠቃቀምን ከሚገድቡት ደግሞ በቂ የሆነ የኃይል አቅርቦት አለመኖር፣ መቆራረጥና መዋዠቅ ነው። ይህ ሲሆን በበቂ ሁኔታ ማምረት አለመቻል ያጋጥማል። በበቂ ሁኔታና አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት ቢያገኙ የማስፋፋት ሥራ በመሥራት ምርታቸውን በእጥፍ ለማሳደግ የተዘጋጁ አምራች ኢንዱስትሪዎች አሉ።

በኃይል አቅርቦት ውስንነት ከፍተኛ የሰው ኃይል መያዝ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች የሥራ ዕድል እንዳይፈጥሩ

> **የዓባይ ግድቡ መጠናቀቅ በኃይል እጥረት ምክንያት ወደኋላ የቀሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያንሠራሩና እንዲጠናከሩ ከማድረጉም በላይ ተጨማሪ ኢንቨስትመንትንም ለመሳብ ፋይዳው የጎላ ነው**

አድርጓል። የዓባይ ግድቡ መጠናቀቅ በኃይል እጥረት ምክንያት ወደኃላ የቀሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲያንሠራሩና እንዲጠናከሩ ከማድረጉም በላይ ተጨማሪ ኢንቨስትመንትንም ለመሳብ ፋይዳው የጎላ ነው።

ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የአምራች ደረጃ የሚገኙ አምራች ኢንዱስትሪዎች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ይፈልጋሉ። ከፍተኛ ኃይል ከመጠቀም አንጻር ለምሳሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ እራሱን የቻለ ኃይል ይፈልጋል። ይህ መሆኑ ረዘም ያለ የሥራ ጊዜ እንዲኖራቸው ያስችላል። እንደ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ያሉ በትልልቅ አምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚመደቡ በመሆናቸው ከፍተኛ ኃይል ይጠቀማሉ። በቂ የሆነ የኃይል አቅርቦት ምቹ ሲሆን፣ በተጨማሪ ትላልቅ የሚባሉ ኢንዱስትሪዎች ይመጣሉ። አሁንም ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መምጣት ጀምረዋል።

ኢንዱስትሪዎቹ ምን ያህል ናቸው ለሚለው። ኢንዱስትሪ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ በሚል ይከፈላሉ። አጠቃላይ ያለውን የኢንዱስትሪ ብዛት እያጠናን ቢሆንም፤ እንደሀገር ወደ 15ሺ ኢንዱስትሪዎች በሥራ ላይ ይገኛሉ። አብዛኞቹም በአነስተኛና መካከለኛ ደረጃ የሚገኙ ናቸው።

እነዚህ በሥራ ላይ የሚገኙት ኢንዱስትሪዎች አስተማማኝ የሆነ የኃይል አቅርቦት ማግኘት ከቻሉ የማምረት አቅማቸው ይጨምራል። የበጀት ዓመቱ የስድስት ወር ግምገማ እንደሚያሳየው ለኢንዱስትሪ የሚቀርበው ኃይል ቀደም ሲል ከነበረበት አድጓል። አቅርቦቱን የበለጠ ለማሻሻል ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ድርጅት ጋር በጋራ ለመሥራት ኮሚቴ አዋቅሮ እየሠራ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን ፦ አምራች ኢንዱስትሪው የኃይል አቅርቦቱ ብቻ ሳይሆን ለምርት የሚያውለው ጥሬ እቃም በየጊዜው ዋጋ መናርና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ተወዳዳሪነቱ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ያነሳል። እዚህ ላይ ምላሽዎ ምንድነው?**

**አቶ ታረቀኝ፤** እውነት ነው አምራች ኢንዱስትሪው የግብዓት ችግር ያነሳል። አብዛኞቹ ግብዓቶች ከውጭ በግዥ የሚገቡ ናቸው። አሁን ባለው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ላይ እንደተቀመጠው አንድ ኢንዱስትሪ ከሀገር ውስጥ የሚጠቀመው ግብዓት ምንያህል ነው የሚለው ይታያል። ወይንም ይለያል። በሚሠራው የልየታ ሥራ መቶ በመቶ ከሀገር ውስጥ ግብዓት የሚጠቀም ኢንዱስትሪ ይበረታታል። ምክንያቱም ኢንዱስትሪዎች የውጭ ሀገር የግብዓት ጥገኛ እንዲሆኑ አይፈለግም። የወደፊት አቅጣጫም የሀገር ውስጥ ግብዓት ጥቅም ላይ እንዲውል ማስቻል ነው።

የግብዓት አቅርቦት ክፍተት ካለ ደግሞ የግብዓት ልማት ላይ መሥራት ነው። በዚሁ መሠረትም ለተኪ ምርት ዝግጅት ስናደርግ ያለንን ቴክኖሎጂ፣ የሰው ኃይል፣ አሁን ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙት የግብዓት አይነት፣ በስንት ጊዜ ልናሳካው እንችላለን የሚለውን ለማወቅ ከግብዓት በመነሳት ሥራዎች ሠርተናል። ኢንዱስትሪዎቹ ግብዓትን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉ ከሆነ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ልናሳካ እንችላለን ብለን ነው በእቅድ የያዝነው።

የሰው ኃይል ላይ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል ያልነውን ደግሞ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስኬት ማስመዝገብ ይቻላል በሚል ነው። ነገር ግን አሁንም ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ማምጣት አለብን ብለን ያስቀመጥነው በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው።

አሁን ላይ የግብዓት አቅርቦት ችግርን ለመፍታት እየተሠራ ነው። ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል። ከፍላጎት አንጻር በቂ ባይሆንም ሀገሪቱ ከምታመነጨው የውጭ ምንዛሪ ትኩረት ሰጥታ ዘርፉን እየደገፈች ነው። የውጭ ምንዛሪ ሳይፈልጉ የራሳቸውን ግብዓት ከውጭ የሚያስመጡ ኢንዱስትሪዎች አሉ። ከግብር (ታክስ) ነፃ ናቸው። ያመረቱትን ምርትም ለውጭ ገበያ ነው የሚያቀርቡት። ግብዓት የሚያስመጡትም አብዛኞቹ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡

በተለያየ ምክንያት ማምረት አቁመው የነበሩና በከፊል ያመርቱ የነበሩ ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ወደ 390 ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፤ - የኢንዱስትሪዎቹ አንዱ የመወዳደሪያ መስፈርት ጥራት ነው። ማነው ክትትልና ቁጥጥሩን የሚያከናውነው? ተጠያቂነታቸውስ?**

**አቶ ታረቀኝ፤** የቁጥጥር ሥራን የሚሠሩ የተለያዩ ተቋማት አሉ። አንዱ የኢትዮጵያ ጥራት ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ነው። ለምርቱ ደረጃ ያወጣል። በወጣው ደረጃ መሠረት ምርቱ መመረቱ በቤተሙከራ ውስጥ የምርት ምርመራ ወይንም ፍተሻ ይለያል። ደረጃዎቹ ሁለት አይነት ናቸው። አንዱ አስገዳጅ ሲሆን ሌላው ደግሞ አስገዳጅ ያልሆነ ነው።

ለምሳሌ ከምግብና ከመጠጥ ጋር የተገናኘ ከሆነ ምርቱ የተመረተበትና የሚያበቃበት ጊዜ፣ ምርቱ የተመረተበት ግብዓት፣ አጠቃላይ መረጃ የያዘ መግለጫ ሊኖረው ይገባል። ይሄ አስገዳጅ ደረጃ ነው። ስለዚህ በዚህ በኩል ደረጃ የሚያወጣና ደረጃ የሚቆጣጠር አለ። በተለይም ከምግብና መጠጥ ጋር የተያያዘውን የኢትዮጵያ መድኃኒትና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቁጥጥርና ክትትል ኃላፊነቱን የሚወጣው።

የጥራት ጉዳይ ድርድር ውስጥ አይገባም። የጥራት ጉዳይ በቸልታ የሚታለፍ ከሆነ የኢንዱስትሪ ዕድገት አይታሰብም። የኢንዱስትሪ ማደግ ብቻ ሳይሆን፤ የተጠቃሚውም ፍላጎት መሟላት አለበት። ስለዚህ ለኢንዱስትሪ እድገት ወሳኙ ሸማች ነው። ከዚያ ውጭ የኢንዱስትሪዎች ዘላቂነት ጉዳይ ነው። አንዱ ከኃይል አቅርቦት ጋር ይያያዛል።

ለምሳሌ አንድ ኢንዱስትሪ የሚጠቀመው የኃይል አይነት አረንጓዴ ኃይል(ግሪን ኢነርጂ)፣ ኒኩሌየር ኃይል፣ የዲዝል (ጋዝ) ኃይል ነው የሚለው መታወቅ አለበት። ኢንዱስትሪው እንደሚጠቀመው የኃይል ሁኔታ ገበያ ላይ የሚያወጣው ምርት ዋጋ ይለያያል። ግሪን ኢነርጂ ተጠቅሞ ከሆነ የተሻለ ዋጋ ያገኛል። ይሄ በአብዛኛው ለውጭ ገበያ በሚቀርበው ምርት ላይ የሚስተዋል የገበያ ሁኔታ ነው። በአካባቢ ላይ በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ኃይል አጠቃቀምም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተመራጭ አይደለም።

አካታች አለመሆንም እንዲሁ ተመራጭ አያደርገውም። ለምሳሌ አሁን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ርካሽ የሆነ የሰው ኃይል ስለመኖሩ ነው የሚነገረው። ይሄ ግን ወደፊት የሚቀጥል አይሆንም። ሰው በሠራው ልክ ክፍያ ማግኘት አለበት። ከሰው ጉልበት ብዝበዛ ጋር ነው የሚያያዘው። ሌላው አሳታፊነት ውስጥ መካተት ያለበት ሴቶችና ወንዶች፣ አካል ጉዳተኞች ኢንዱስትሪ ውስጥ መኖር ያለባቸው መስፈርቶች ናቸው። እነዚህ ሁሉ የኢንዱስትሪው የምርት ማረጋገጫዎች ናቸው። ኢንዱስትሪዎች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትም በየጊዜው ይሰጣቸዋል።

**አዲስ ዘመን ፦ወቅታዊው የሀገር ሠላምና ኢንዱስትሪው እንዴት ይታያል?**

**አቶ ታረቀኝ፦** ሠላም አለመኖር መጀመሪያ የሚጎዳው ኢንዱስትሪውን ነው። ሠላም ከሌለ ነባር ኢንቨስትመንቶች የመቀጠል እድላቸው አነስተኛ ነው። ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን መሳብ አይቻልም። በአሁኑ ጊዜ በግጭቱ ሥራቸው ተስተጓጉሎ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እየተመለሱ ነው። ኤክስፖርት የጀመሩም አሉ።

በቀጣይ መሻሻል ያለበት ለኢንቨስመንት ያለን አተያይ ነው። የፀጥታ ችግር በሌለበትም ኢንቨስትመንት የሥራ ዕድል፣ ቴክኖሎጂ ይዞ እንደሚመጣና ለሀገር እድገት አስፈላጊ እንደሆነ አለመገንዘብና በመልካም ያለመቀበል ሁኔታ ይስተዋላል። የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ያስፈልጋል። የፖለቲካ ተቃውሞ ሲነሳ ኢንቨስትመንትን ማዕከል የማድረግ ሁኔታም መስተካከል አለበት።

**አዲስ ዘመን ፦የዓባይ ግድብ ተጠናቅቆ የኃይል አቅርቦት ችግሩ ከተፈታ ከአምራች ኢንዱስትሪው ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ታረቀኝ፦** አምራች ኢንዱስትሪዎች የኃይል አቅርቦት ችግራቸው ከተቃለላቸው በኋላ የማምረት አቅማቸው ማደጉን ማረጋገጥ አለባቸው። ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት የበለጠ ለመሥራት መነሳሳት ይኖርባቸዋል። እንደመንግሥትም ደግሞ በቂ የሆነ ኃይል መኖሩንና በዋጋም ርካሽ እንደሆነ ማስተዋወቅ ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን፦ ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ታረቀኝ፦** እኔም አመሰግናለሁ።

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት



ልዩ እትም

# ታላቁ የሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያውያን ሁሉ ኩራት፣ የይቻላል ተምሳሌት!

መጋቢት 24 ቀን በ2003 ዓ.ም የተጀመረው የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ተሳክቶ ከመገባደጃው ጫፍ ደርሷል። ግድቡ ከዚህ ስኬት ሲደርስ እልፍ አእላፍ ችግሮችንና የሴራ ወጥመዶችን አልፎ ነው።

የግድቡ መሠረት የተጀመረበት 13ኛ ዓመቱ "በኅብረት ችለናል!" በሚል መሪ መልእክት የሚከበረው ከጅምሩ እስከዛሬ ሕዝባችን ላደረገው ያልተቋረጠ ሁለንተናዊ ድጋፍ ምስጋና ለማቅረብ ነው።

ግድቡን ለመገንባት ስናቅድና ስንጀምር ጫጫታና ጫናው ቀላል አልነበረም። የኢትዮጵያውያን ሕልምና ተስፋ ከጅምሩ እንዲጨናገፍ አንዳንድ ሀገራት በጋራ አድመው አሲረውብናል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድንገለልና እንድንነጠል ከፍተኛ ዘመቻ ተከፍቶብናል። ባልፈረምነው የቅኝ ገዥዎች ውል ሊያስገድዱንና ውጥኑ ከመነሻው እንዲጨናገፍ ሞክረዋል። አንዳንዶቹም "ይጀምሩታል እንጂ አይጨርሱትም!" እያሉ የብድር አማራጮችን ሁሉ ሲያመክኑብን ቆይተዋል።

ሁሉን አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁመን ግድቡን ወደ ማገባደጃ ምዕራፍ ስንሸጋገርም ዘመቻውን ዳግም በመከፈትና ኃይል በማስተባበር የፀጥታው ምክር ቤት ልማትን እንደጦርነት እንዲመክርበት ተደርጓል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን በጋራ የጀመርነውና አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ የምንከፍልለት የኩራታችንና አንድነታችን መገለጫ ፕሮጀክት ነበርና ከዚህ አድርሰነዋል።

ግድቡን የምንገድበው ማንንም ለመጉዳት አይደለም፣ መነሻችን ሕዝባችንን ከጨለማ ኑሮ ለማላቀቅ ብቻ ነው። በዚህ መሻታችን ደግሞ የሚጎዳም፣ የተጎዳም አካል የለም፣ አይኖርምም። በራሳችን ወንዝና በራሳችን ሀገር፣ በራሳችን አቅም እንዳንለማ ሲፍጨረጨሩ የነበሩ ሁሉ ብድር ለማስከልከል፣ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንዳያደርጉ ለመወትወትና ልዩ ልዩ ማሰናከያዎችን ለመደርደር በእጅጉ ደክመዋል። ኢትዮጵያውያን ግን የተንኮል መረቦችን በጋራ

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

እየበጣጠሱ፣ ተማሪዎች ከዕለት ጉርሳቸው፣ የመንግሥት ሠራተኞች ከደመወዛቸው፣ ነጋዴዎች ከወረታቸው፣ ጡሮተኞች ከአነስተኛ አበላቸው፣ የጉልበት ሠራተኞች ከዕለት ምንዳቸው፣ የፀጥታ ኃይሎችና የመከላከያ ሠራዊት አባላት ከሬሽናቸው፣ በስደት ያሉ ኢትዮጵያውያን ከአነስተኛ ገቢያቸው፣ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በላባቸው ካፈሩት ፍሬ እየቀነሱ ግድቡን ከማጠናቀቂያ ምዕራፉ አድርሰውታል።

ኢትዮጵያውያን ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ አስተዋጽኦ ያደረጉት ገንዘባቸውን ብቻ አልነበረም፤ ደስታቸውን፣ ኀዘናቸውን ሁሉ ጭምር እንጂ። የሠርጋቸውን ወጪ ቀንሰው ሙሽሮች ለግድቡ ሰጥተዋል፤ የሟች ቤተሰቦቻቸውን የሙት ዓመት መታሰቢያ ለሕዳሴ ግድብ አበርክተዋል። በአጠቃላይ ታላቁ የሕዳሴ ግድባችን ልክ እንደ ዓድዋ ድል መላው ኢትዮጵያውያን የተረባረቡበት የወል ድል ነው፤ በጋራ ጀምረን የማንጨርሰው ጉዳይ እንደሌለ ማሳያም ነው።

የኃይል አቅርቦት ዓለም አቀፍ ችግር ነው፤ በተለይ ደግሞ ታዳሽ ኃይል ማመንጨት ዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚያስገኝ ተግባር ነበር። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ግን በራሳችን ወንዝ፣ በራሳችን አቅም፣ በራሳችን ሀገር ታዳሽ ኃይል እንዳናመነጭ በርካቶች ተረባረቡብን። ነገር ግን ሊያዘገዩን እንጂ ከሕልማችን መዳረሻ ሊያስቆሙን አልቻሉም፤ ምክንያቱም በጋራ ቆመናልና።

አሁን ላይ በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ስኬት ፕሮጀክቶችን በራስ አቅም ጀምሮ የመጨረስ አቅም እንዳለን አሳይተናል። አጠቃላይ ሥራው በመጠናቀቅ ላይ የደረሰው ግድባችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል፤ ለቀሪ ሥራዎቹም ኢትዮጵያውያን የመጨረሻዎቹን ሴኮንዶች ማርሽ ቀይረው ጭምር ማስደመም ይችላሉና። ከ18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ አዋጥተው ግድቡን በማገባደጃ ምዕራፍ ላይ ያደረሱ ኢትዮያውያን ለቀሪው የማንንም ድጋፍ አይጠብቁምና።

መንግሥት ዘንድሮ የግድቡን ግንባታ የጅማሮ 13ኛ ዓመት ሲያከብር እንደከዚህ ቀደሙ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እየጠየቀ ብቻ አይደለም፤ በጋራ ተሳትፎ ከዚህ ስላደረሱት እያመሰገነ እንጂ። እንደ ሕዳሴ ግድብ ሕዝብ በነቂስ የተሳተፈበት ፕሮጀክት በዓለም ስለመኖሩ እንጠራጠራለን፤ እንደ ሕዳሴ ግድብ በዓለም አቀፍ መድረክ እየተፈተነ ከዚህ ደረጃ የደረሰ የታዳሽ ኃይል ማመንጫ ግድብም እምብዛም አይታወቅም። ሆኖም ግን ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት የተሳካው በመላው ኢትዮጵያውያን የእንችላለን መንፈስና የጋራ ጥረት ነው። ታላቁ የሕዳሴ ግድባችንም የኢትዮጵያን ሁሉ የጋራ ድልና የይቻላል መንፈስ ተምሳሌት ሆኖ ይቀጥላል።

በኢትዮጵያውያን ኅብረት ግድቡ ይጠናቀቃል፣ ሁለንተናዊ ብልጽግናችን ይረጋገጣል!

# ዓባይ ግድብን እየተቃወሙ በዓባይ ግድብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅኝ ገዢዎች የዓባይ ተፋሰስን ጠቅልለው ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ ከሽፏል። ይህ በ20ኛውና 21ኛው ክፍለ ዘመንም መልኩን እየቀያየረ ቀጣይነት ያለው ሙከራ ሆኖ ቀጥሏል።

የዓባይ ንጉሶች ሚዲያ ባለቤትና የዓባይ ጉዳይ የኢትዮጵያ ተሚጋች ዑስታዝ ጀማል በሽር እንደሚሉት፤ ግብጽ የዓባይ ወንዝን በባህር መልኩ በመስህብነት ደረጃ ከፍ ያለ ቦታ እንዲኖረው አድርጋ ናይል ሲባል ግብጽ እንዲባል፤ ግብጽ ሲባል ናይል እንዲባል ማድረግ የሚያስችል የቱሪዝም መስህብ ሰርታ ለዓለም አሳይታለች። ይህንን ከማስቀጠል አኳያ የዓባይን ውሃ በመጠቀም አሁንም በዓለም አንደኛ ሊባል የሚችል ሰው ሰራሽ ወንዝ እየሰራች ነው።

እንደ ዑስታዝ ጀማል ማብራሪያ፤ አስገራሚው ነገር ለግብጽ አብዛኛው የውሃ መጠን የሚሄድላት ከኢትዮጵያ ሲሆን፤ 86 ነጥብ አምስት በመቶው ከኢትዮጵያ የሚሄድ ውሃ ላይ ተንተርሶ የሚሰራ ወንዝ ግን ኢትዮጵያን ያማከለ፣ ኢትዮጵያን ያላማካረ መሆን ነበረበት። ይህንን ሥራ ሊያስቀጥሉም ሆነ ላያስቀጥሉ የሚችሉ ነገሮች ይፈጠራሉ ወይ ተብለው ከኢትዮጵያ ጋር ቢያንስ ተወያይቶ ተደጋግፎ መሥራት ተገቢ ነበር። ነገር ግን የግብጽ የሁልጊዜ አካሄድ "ይህንን ውሃ በምንም መልኩ አላጣውም። የራሴም ነው። ምክንያቱም ናይል የኔ ስጦታ ነው። ግብጽ ራሱ የናይል ስጦታ ናት" ብላ ስለምታስብ ኢትዮጵያን በታሳቢነት የምታስቀምጥበት ሁኔታ የላትም።

ግብጽ ዓባይን በመጀመሪያ ከምንጩ የመቆጣጠር አባዜ አለባት የሚሉት ዑስታዝ ጀማል፤ በዚህም እስከ ጉንደት ጦርነት ውስጥ እንዲገቡ ማድረጉም የዚህ ማሳያ እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ስላልተሳካ ከዛ በኋላ በተለያዩ ዘዴዎች ይህንን ውሃ ማንም ሳይነካው ወደ ግብጽ ኮለል ብሎ እንዲፈስ የሚያደርጉ የተለያዩ ውሎችን ለማስፈረም ሙከራ ማድረጋቸውንም ያነሳሉ።

አሁንም በዚህ አይነት እሳቤ ውስጥ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በማስፈራራትም ይሁን በተለያዩ የፖለቲካ ሴራ እንዲሁም በተለያዩ ጫናዎች የዓባይን ወንዝ ማንም አይነካብንም ብለው ስለሚያስቡ ኢትዮጵያን ሂሳብ ውስጥ እየከተቷት አይደለም ነው ያሉት።

ዑስታዝ ጀማል እንደሚሉት፤ ይሄ ጉዳይ መቀጠል የለበትም። የዓባይን ውሃ ተንተርሶ በግብጽ የሚሰሩ ማናቸውም ትላልቅ ፕሮጀክቶች በማንኛውም ሁኔታ ነገ ኢትዮጵያ በምትሰራቸው ሥራዎች ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም እነሱ በሚሰሩት የውሃ ልማት ላይ ትንሽም እክል ገጠማቸው በሚባልበት ወቅት ኢትዮጵያ ከምትሰራው የመስኖ ስራ ጋር ሊያያይዙ ይችላሉ። በአጋጣሚ በተወሰነ ደረጃ እንኳን ውሃው ቢቀንስ እንደምክንያት የሚያስቀምጡት አሁንም ኢትዮጵያን ነው። ስለዚህ እንዲህ አይነት ትላልቅ ፕሮጀክቶች ሲሰሩ ኢትዮጵያን ማማከር ይገባል።

"ኢትዮጵያ ውሃ አመንጪ ሀገር ሆና ግድብ ስትሰራ እኛን ሳታማክሩ አትሰሩም እያሉን፤ እነርሱ ደግሞ የታችኛው ተፋሰስ ሆነው ምንም ነገር ሳያማክሩን ሊሰሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። ተቃርኖ ያለው አካሄድ ነው እየሄዱ ያሉት" በማለት ነው ዑስታዝ ጀማል የሚናገሩት።

ግብጽ አዲስ ለምትገነባው ግዙፉ ሰው ሰራሽ ወንዝ እንደ ምንጭነት ከምትጠቀማቸው መካከል አንዱ የዓባይ ወንዝ እንደመሆኑ የዓባይ ግድብ ላይ የምታንጸባርቃቸው ክርክሮችና ጫናዎች የራሷን ጥቅም ብቻ ከማየት የመጣ መሆኑን ዑስታዝ ጀማል ይናገራሉ። "ግብጾች ትልቅ ወንዝ ለመስራት ከዩጋንዳ ብቻ የሚሄድላቸው ውሃ በቂ እንዳልሆነ ያውቁታል። ምክንያቱም 15 በመቶ ብቻ ነው ከዛ የሚሄደው። የተረፈው ውኃ በሙሉ የሚሄደው ከኢትዮጵያ ነው። ስለዚህ እዛ ላይ ተንተርሰው ይህን ያክል ትልቅ ወንዝ ሲሰሩ ኢትዮጵያን አለማማከር ተገቢ አይደለም" በማለት ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያን ማማከር ቀርቶ በተቃራኒው ኢትዮጵያ ይሄን ውኃ እንዳትጠቀም እየሞገቱ መሆናቸውንም ዑስታዝ ጀማል ያነሳሉ። "ሌሎች ፕሮጀክቶቻችን የምንሰራው ኢትዮጵያን ሳናማክር፤ ሳንጠይቃት ነው" የሚል እሳቤ ውስጥ ስላሉ ምን ያህል ራስ ወዳድ እንደሆኑና የራሳቸውን ጥቅም ብቻ እያዩ የሚሰሩ መሆኑን በግልጽ ያሳያል ብለዋል።

እንደ ዑስታዝ ጀማል ገለጻ፤ ከኢትዮጵያ የሚመነጨው ውሃ ላይ ኢትዮጵያ ግድብ ስትሰራ እኛን ልታማክረን ይገባል፤ ለኤሌክትሪክ ማመንጫነት በቋሚነት ሊያገለግል የሚችለውንና ወደ ግብጽ የሚፈሰውን ውሃ እንኳን የሚያዝበትን አግባብ እኛ ነን መወሰን ያለብን፤ በ10፣ በ20 ዓመት ይለቀቅ የሚለውን የግድቡን ሂደት ራሱ እኛ ነን መወሰን ያለብን የሚሉበት አግባብ አለ። እነርሱ ግን አስዋን ግድብን ሲገድቡ ኢትዮጵያን አላማከሩም፤ አሁንም ደግሞ ይሄንን የሚያክል ትላልቅ ወንዞችና ሌሎችንም ነገሮች በሚሰሩበት ወቅት እያማከሩን አይደለም። ይሄ ምን ያህል በራስ ወዳድነት ዓለም ውስጥ ያሉ እንደሆነና የኢትዮጵያንም ሀቅ በደንብ የሚያሳይ ነው።

የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪው ዶክተር ያዕቆብ አርሳኖ በበኩላቸው፤ ግብጽ የአስዋንን ግድብ ጨምሮ መሠረታቸው በዓባይ ውሃ ላይ የሆኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በራሳቸው በረሃማ ግዛት ላይ መስራቷን ይጠቅሳሉ። አሁንም በዚሁ መልክ የራሷን ወንዝ መገንባቷን ቀጥላለች ብለዋል።

ግብጽ አሁንም የወሰን ተሻጋሪ የውሃ ባህሪያትን በትክክል አልተረዳችም የሚሉት ተመራማሪው፤ ግብፅ በነፃ በምታገኘው ውሃ ተጨማሪ ግድቦችን ሰርታ ውሃ ማቆየት እንደምትሻው ሌሎች ህዝቦችና ሀገራትም ውሃቸውን እንዳይጠቀሙ ማድረግ እንደሌለባት ይመክራሉ። በወሰን ተሻጋሪ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ኢትዮጵያ፤ ግብጽና ሌሎች የተቀሩ ሀገራት ተሰብስበው የጋራ ጥቅምን ሊያስጠበቅ የሚችል ፖሊሲ ቀርፀው መስራት እንዳለባቸውም ያመላክታሉ።

የወሰን ተሻጋሪ ውሃዎች የኢትዮጵያ ልማት ግብፅን ለመደገፍ፣ የግብፅ ልማት ደግሞ ኢትዮጵያን ለመደገፍ ዓላማ መዋል አለባቸው። ይህ በግብፅ ውስጥም ሆነ በኢትዮጵያ ያለው የተሻለ ነገር ምን እንደሆነ ለመለየትና በጎ ተግባራትን እርስበርስ ለመመጋገብ ያስችላል ነው ያሉት። ግብጽ በእንዲህ መልኩ ተረድታ መስራት አለባት ሲሉም ገልጸዋል።

ግብጽ ወንዙን ለመስራት ኢትዮጵያን እስካላስፈቀደች ድረስ፤ ኢትዮጵያ ደግሞ በራሷ ሀብት ላይ ግድብም ሆነ ሌላ ነገር ለመስራት የታችኛውንም ሆነ የላይኛውን ተፋሰስ ሀገራት ፍቃድ ማግኘት የለባትም የሚለውን ነገር እያጎላው መሆኑን ያሳያል ያሉት ደግሞ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ናቸው።

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም ግብጽ በዓባይ ውሃ ስትጠቀም ቆይታለች። በርካታ የልማት ሥራዎችን መስራት ችላለች። ይህ የሆነው ከኢትዮጵያና የላይኛው ተፋሰስ ሀገራት በተገኘ ፍቃድ አይደለም። ያለ ፈቃድ የራሷን ወንዝ እስከገነባች ድረስ በዛው ልክ ኢትዮጵያንም በዓባይ ግድብ ጉዳይ መቃወምና መከራከሯ ተገቢ አይደለም።

ዑስታዝ ጀማል በበኩላቸው፤ "ግብጽ በኢትዮጵያ ላይ የምታሳየው አቋም ትክክል አይደለም። የራሷን ግዙፍ ልማት ባካሄደች ቁጥር በዚያው ልክ ያንን ሊያግዝ ይችላል ብላ የምታምናቸው ኢትዮጵያ ላይ የሚደረጉ ብዙ የልማት አቅጣጫዎችንም ልትደግፍና ልታግዝ ይገባል" ብለዋል።

ግብጽ የዓባይን ውሃ በመጠቀም ለራሷ ግዙፍ ልማት እያከናወነች ኢትዮጵያ ላይ የምታሳየው አቋም ትክክል አይደለም የሚሉት ዑስታዝ ጀማል፤ በእርግጥም ግብጽ የፈለገችውን የልማት አይነት እንድትሰራ ኢትዮጵያ ፈጽሞ እንቅፋት ሆናባት እንደማታውቅ፤ የአስዋን ግድብ ሲገደብ ለምን የሚል ጥያቄ ያቀረበችበት ሁኔታ እንደሌለ፤ በተለያዩ የግብጽ የልማት ሂደቶች ውስጥ ኢትዮጵያ ምንም ቦታ ላይ ጣልቃ ገብታ ስትናገር እንደማትታይ ያብራራሉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ልማት፤ የኢትዮጵያ መጠቀምና በውሃው ላይ የተለያዩ ልማቶችን መስራት ግብጾቹን ሊያስደስታቸው ይገባል ነው ያሉት። ግብጾች በተባበረ አካሄድ ከኢትዮጵያ ጋር የሚሰሩ ከሆነ እንዲያውም ካሰቡት በላይ ውሃውን የበለጠ ማጎልበት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች እንዳሉም ነው የገለጹት።

ዑስታዝ ጀማል እንደሚያብራሩት፤ ግብጾች በኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ ላይ ምንም አይነት አሻራቸውን አላሳዩም። የኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ ላይ የምትሰራው ስራ ግን በውኃው ላይ በጎ የሆነ ተጽዕኖ አለው። ምክንያቱም ዛፎች በበዙ ቁጥር የአየር መስተካከል ይመጣል። የአየር መስተካከል ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የዝናብ ምንጭ ይሆናል። ስለዚህ ዝናብ በመጣ ቁጥር አሁንም የሚሄደው ወደ ግብጽ ከመሆኑ አንጻር በተዘዋዋሪ ግብጽ ተጠቃሚ ናት። ስለዚህ በእንደዚህና መሰል የሆኑ የልማት ሂደቶች ውስጥ ግብጽ ብትሳተፍ ውሃዋን የበለጠ ጥሩ ሆኖ እንዲሄድላት የማድረግ ሁኔታ ይፈጠራል።

በውሃ ፖለቲካ ላይ የሚጽፉ ምሁራን እንደሚገልጹት፤ ከሆነ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የውሃ ሀብቶችን ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር በጋራ ከመጠቀም አኳያ ወደ ትብብርም ሆነ ወደ ግጭት ሊገቡ ይችላሉ። የተለያዩ የህግ ስምምነቶች ላይ በመድረስና ፖለቲካዊ መፍትሄ በማምጣት ሀገራት ወደ ስምምነቱና በጋራ ወደ መስራቱ መምጣት አለባቸው።



# ታላቅ ተስፋ ለሴቶች የሰነቀው የዓባይ ግድብ

**አስመረት ብስራት**



ምዕራብ ጎጃም ደጋ ደሞት ወረዳ ተወልዳ እንዳደገች ትናገራለች ምንታምር ተመስገን። ምንታምር በነፋሻዋማ የገጠር ወረዳ ተወልዳ ያደገች ሲሆን እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ ነበር ከመኖሪያ ቀዬዋ በእግር ከአንድ ሰዓት በላይ የሚያስጉዝ ትምህርት ቤት የገባችው።

ቤታቸው ውስጥ ሶስት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆች የነበሩ ሲሆን የመጀመሪያዋ እህታቸው በሕፃንነቷ ተድራ የቤት እመቤት በመሆኗ ምክንያት የትምህርት ቤትን ደጃፍ የማየት እድል አላገኘችም ነበር። የተቀሩት አራቱ ልጆች ግን ማልደው በመነሳት ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት መጀመሪያ ውሃ ቀድተው ነበር ረጅሙን ጉዞ የሚጀምሩት።

ልጆቹ ሩቅ ተጓዥ በመሆናቸው ሰዓት ለመቆጠብ ሲሉ እህል ቢጤ አፋቸው ላይ ጣል የሚያደረጉትም እንኳን መንገድ ላይ እንደነበር ታስታውሳለች። ቀን ትምህርቱና መንገዱ አድክሞ ቤት ሲያደርሳቸው ቤት የተገኘቸውን ቀማምሰው ወንዶቹ ልጆች ደብተራቸውን ይዘው ለእረኝነት ሲወጡ ሴቶቹ ደግሞ ማጀት ገብተው እናታቸውን የማገዝ ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር። ምንታምር እንደምትለው ከትምህርት ቤት በኋላ የቤት ሥራውንም ለመሥራት ቀን የተማሩትንም መለስ ብሎ ለማየት ኩራዝ ትልቁ አጋዣቸው ነበር።

እንደዚህም ሆኖ በትምህርታቸው ወጤታማ የነበሩት ልጆች ዛሬ የደረሱበት ለመድረስ በርካታ ውጣ ውረዶችን ማለፋቸውን ታስታውሳለች። አንድ ቀን ለዓመቱ ማጠቃለያ ፈተና በቂ ጥናት አለማድረጓ ስጋት የሆነባት ምንታምር ሌሊት ሙሉ ስታነብ ለማደር ኩራዙን ላንባ ሞልታ ለኩሳ ማንበብ ጀመረች። ሌሊቱ እየተጋመሰ ሲሄድ ድካም የበረታባት ልጅ ደብተሯን እንደገለጠች አጠገቧ የነበረው ኩራዝ ላይ እንቅልፍ ጥሏት ትወድቃለች። ኩራዙ ላይ በመውደቋ የተነሳ እሳቱ ጠፍቶ፤ ግማሽ ሌሊት የነደደው ላንባ መጠኑ ቀንሶ የከፋ ጉዳት ባያደርስም ይህ ሁሉ የመብራት ኃይል አለመኖሩ ውጤት እንደሆነ ታስታውሳለች።

በወቅቱ ለዓመታት ውጤታማ ለመሆን የነበረውን መፍጨርጨረ ስታስብ እንዲህ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሀገር ውስጥ እየኖሩ መቸገራቸው እንደሚያስገርማት ታስረዳለች። ውሃ ዳር ተኝቶ ውሃ መጠማት፤ ሀብት ላይ ቆሞ ለምፅዋት እጅን መዘርጋት የሀገሪቱ ሕዝቦች እጣ ፈንታ መሆኑ የሚያሰቆጭ መሆኑን ታብራራለች።

ምንታምር ቁጭት አጠንክሯት ዛሬ ተምራ ከፍ ባለ ደመወዝ ከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ብትሆንም አሁንም ድረስ በተወለደችበት አካባቢ በቂ የኃይል አቅርቦት ባለመኖሩ የተነሳ ሴቶቹ ላይ ከፍተኛ ጫና መኖሩን ትናገራለች። ምንም እንኳን በእጅ የሚሰራ ድካምን የሚያቀል ወፍጮ ቢመጣም፤ በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ መብራቶች ቢኖሩም ሙሉ ለሙሉ የኃይል አቅርቦቱ ተሟልቶ ሴቶችን ሊያሳርፍ አለመቻሉን ታስረዳለች።

የታላቁ ሕዳሴ ግድቡ መጠናቀቅ በትንሹም ቢሆን የተጀመሩ ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎች አድገው የገጠሯን ሴት ሕይወት ይቀይሩታል ብላ እንደምታስብ ታስረዳለች። የኃይል አቅርቦት የሴቶችን ድካም ከመቀነሱም ባሻገር በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይም የማይናቅ አስተዋፅኦ ይኖራዋል ብላለች።

ሌላዋ ባለታሪካችን ወይዘሮ ይታይሽ አስማማው ይባላሉ። እሳቸውም ምዕራብ ጎጃም ይልማና ዴንሳ ወረዳ ውስጥ ገጠር ቀበሌ ነዋሪ ናት። ወይዘሮ ይታይሽ የሚኖሩባትን እና መብራት አይታ የማታውቀውን የገጠር ጎጆ በብርሃን ለመሙላት፤ ገበያ ወርዶ ላንባ መግዛት የሴቷን ጉልበት ይጠይቃል። የቤቱን ሙቀት ለመጠበቅም ምድጃ የሚፈለገውን እንጨት ለማምጣትም ጫካ ገብታ እንጨት ለቅማ ተሸክማ መምጣት አለባት። ጠላ ለመጥመቅ ለሰባት ቀናት የተዘፈዘፈውን ደረቆት ለመቁላትም የሚሆኑ ወፋፍራም እንጨቶችን አዘጋጅታ ሌሊት ተነሰታ ያን ሁሉ ቆልታ ታደራለች። ማልዳ ለቤተሰቡ ያሰናዳችውን ቁርስና ቡና ከአፍ ካደረሰች በኋላ ደግሞ ከሴት ልጇቿ ጋር በመተባበር የተቆላውን ደረቆት ሙሉ ቀን በእጇ ስትፈጭ ትውላለች።

ጠዋት ልጆች ወደ ትምህርት እንደሄዱ ባሏን እህል አቅምሳ ወደ እርሻ ትሸኛለች፤ ከዛም የከብት በረቱን ማፅዳት እና ቤቱን የማሰናዳት ኃላፊነቷን ተወጥታ ደግሞ ባልዋን ከተል ብላ እርሻ ለማገዝ ትሄዳች። እርሻው ላይ ምሳ ሰዓት እስኪደርስ ደፋ ቀና ስትል ቆይታ ደግሞ ምሳ ለመሰናዳት ወደ ቤቷ እንደምትመለስ ትናገራለች። ከዛም ቤት ያፈራውን አስናድታ ተሸከማ፤ ጠላውን ምሳውን ውሃውን አዝላ ወደ እርሻ ትወርዳለች። ምሳ አብልታ ባልየው እጥላው አረፍ ሲል አረምና ጉልጋሎ ስትራዳ ቆይታ ወደ ቤት እንደምትመለስ ትናገራለች።

ቤት ገብታ ጋገራው፤ ወጥ ሥራሁ ስትል፤ ላይ ታች ስትሮጥ ማምሸቷ አነሷት ባሏ ሲገባ ነፍሰጡር ብትሆንም እንኳን አጎንብሳ እግር ታጥባለች። ይህን ሁሉ ኃላፊነት በሰዓቱ ለመጨረስ ደግሞ ከፀሐይዋ ጋር እሽቅድድም እንደሚገቡ ትናገራለች። ትግሉ ድካሙ ሁሉንም ለማቅለል መብራትን የሚያህል ረዳት ከየትም አይገኝም ትለናለች።

ወይዘሮ ይታይሽ እንደምትለው ለድግሱም ፤ ለማህበሩም፤ ለደቦውም ብቻ ባጠቃላይ ለሚያስፈልግ ድግስ በሙሉ እንጨት ከመልቀም አንስቶ ምግቡም መጠጡም ተሰናደቶ ሰው አፍ እስኪደርስ ድረስ የሴቷ ሙሉ አቅም ፈሶ ዓይኗ በጭስ ተጨናብሶ ወገቧ ጎብጦ ያለ እድሜዋ አርጅታ እንድታለፍ ትሆናለች። ከጉልበት ጠያቂው ሥራ በተጨማሪም አርግዞ መውለድ፤ ልጅ ማሳደግም አሁንም የሴቷን ሙሉ አቅም የሚፈልግ ተግባር ነው።

ይህ ሰቆቃ በኔ ይብቃ ያለች እናትም ልጆቿን ትምህርት ቤት ብትልክም ልጆቿ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት በሌሊት ተነስተው ውሃ ቀድተው ነው ጉዞን የሚጀምሩት። ልጆችም ትምህርት ቤት እንዳይረፍድባቸው እህል ቢጤ አፋቸው ላይ ጣል የሚያደረጉትም መንገድ ላይ ነው። ቀን ትምህርቱና መንገዱ አድክሟቸው ቤት ሲያደርሳቸው ቤት የተገኘቸውን ቀማምሰው ወንድ ልጆች ደብተራቸውን ይዘው ለእረኝነት ሲወጡ ሴቶቹ ልጆች ቤት ማጀት ውስጥ እናታቸውን ሲያግዙ ያመሻሉ።

ሥራው ሲያበቃ ምሽቱን የቤት ሥራ ለመሥራትም ሆነ የተማሩትን ለመመልከት ኩራዝ አብርተው የሚያመሹ ሲሆን ጭሱ አፈንጫቸውን ሞልቶ ለተለያዩ ችግሮች ያጋልጣቸዋል። ላንባ መግዣው ሳንቲም ሲያጥርም ሆነ በተለያየ ምክንያት ሲጠፋ ማጥናቱም ቀርቶ በጨለማ ይታደራል።

እንደ ወይዘሮዋ ገለፃ በዚህ ሁሉ ሰቆቃ ውስጥ ኑራቸውን ለሚገፉት ሴቶች መሠረት ደንጋዩ ከተጣለ 13ኛ ዓመቱን ያስቆጠረው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ይዞ የሚመጣው ተስፋ ብሩህ ነው። የኃይል አቅርቦቱ በቀጭኑ መስመር የገጠር መንደሮችን በሙሉ ሲያዳርስ ጭስ ያጣፋው ዓይን ዳግም በተስፋ ብርሃን ይለመልማል።

ይህ ተስፋ የተጣለበት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ ማክሰኞ 13ኛ ዓመቱን ደፍኗል። የግድቡ ግንባታ ከዛሬ 13 ዓመታት በፊት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ነበር የተጀመረው። በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊም ኢትዮጵያ በታላቁ የዓባይ ወንዝ ላይ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከዓለም ደግሞ ተጠቃሽ የሆነ ግዙፍ ግድብ መገንባት መጀመሯን በማብሰር በይፋ የመሠረት ድንጋዩን አኑረዋል።

ከዚያም ወዲህ ግድቡ በበርካታ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፏል። የነበሩበትን እንደ ጭለማ የከበዱ ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎች ተሻግሮ ከወር በፊት የመጀመሪያውን ኃይል ለማመንጨት ችሏል። ኢትዮጵያውያን ራሳቸው መሐንዲስም፤ የፋይናንስ ምንጭም ሆነው ይገነቡታል የተባለለት ግድቡ 5 ዓመታትን እንደሚፈጅ ነበር በወቅቱ የተገለጸው። ሆኖም በግንባታው በተለያዩ ምክንያቶች ተጓቶ እነሆ 13ኛ ዓመቱ ላይ ደርሷል።

ከ2010 ዓ.ም ወዲህም በግድቡ የግንባታ ፕሮጀክት ተስተውለዋል የተባሉ ህጸጾች ተነቅሰውና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራዎች ተቋራጩን እስከ መቀየር እንዲሁም የተርባይኖቹን ቁጥር ከ16 ወደ 13 እስከ መቀነስ የደረሱ ርምጃዎች ተወስደው ግንባታው ቀጥሎ አሁን አጠቃላይ የግንባታ ወደመጠናቀቁ ቀርቧል።

ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የግድቡ ሥራ ተጠናቆ 95 በመቶ ላይ ደርሷል። ጉባ ላይ የከተመው ይህ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ በአሁኑ ወቅት ከ42 ቢሊዮን ሜትር ኩዩብ በላይ ውሃም ይዟል።

ኢትዮጵያውያን ከመቀነታቸው ፈተው፤ ካላቸው ላይ አውጥተው የሰበሰቡት ገንዘብም በአስራ ሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ 18 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር መድረሱንም ተሰምቷል።

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ በተገኘው መረጃ መሠረት የሲቪል ሥራው ግንባታው 98 ነጥብ 9 በመቶ የደረሰ ሲሆን የኤሌክትሪክ መካኒካል ሥራዎች አፈፃፀም 76 በመቶ፤ የውሃ ማስተላለፊያ የብረታ ብረት ሥራዎችም 87 ነጥብ 1 በመቶ መድረስን ተመልክተናል።

ከዚህም በተጨማሪ አጠቃላይ የግድቡ ግንባታ የደረሰበት አማካኝ ደረጃ 95 በመቶ ሲሆን ግድቡ የያዘው የውሃ መጠን 42 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፤ ከዋና ግድቡ ኋላ የተኛው ውሃ መጠንም 160 ኪሎ ሜትር ነው። ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚይዘው የውሃ መጠን 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ሲሆን ከግድቡ ኋላ የሚተኛው የውሃ መጠን 256 ኪሎ ሜትር መሆኑን ያመለክታል።

አሁን ላይ በሁለት ተርባይኖች እየተመረተ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል 540 ሜጋ ዋት ሲሆን ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይልም 5 ሺ 150 ሜጋ ዋት ነው። በሰዓት የሚመነጨው ኤሌክትሪክ ኃይልም 15 ሺ670 መሆኑን ሰምተናል።

ታዲያ ይህ ሁሉ ኃይል ተመርቶ እኛ ደጅ ሰተት ብሎ ሲደርስ በእጅ መፍጨት ቀርቶ ወፍጮው በቅርብ ሲተከል፤ እንጨት መሸከም ቀርቶ ምጣዱም ወጡም በኤሌክትሪክ ምድጃ ሲጣድ ጭስ ያጠፋው ዓይን አይበራም ትላላችሁ? ጥቀርሻ አፋንጫቸውን ሞልተው ጥናት ሲሉ የሚታመሙት ተማሪዎችስ ሌሊቱን ሙሉ አጥነተው ከቁም ነገር ለመድረስ ማን ከልካይ ይኖራቸዋል።

ድካምን ቀናሽ ሀብት የሚያከማች፤ ለኢንዱስትሪው አቅም የሚሆነው ይህ ፕሮጀክት በፍጥነት አልቆ ወደ ሥራ ሲገባ በተለይም ሴቶች ቀናቸው ይበራል። የኃይል አቅርቦቱ ተሟልቶ ከእኛ ተርፎ ለጎረቤት ሲቀርብ አይችሉም ላሉቱ ችለን ከማሳየት በቀር ምን ደስ የሚል እውነት ይገኛል። አይችሉም መባልን ያስቀረ፤ አንድ የመሆን መንገድን ያመላከተ፤ ታላቅ ተስፋ በመሆኑም ብዙ እናቶችን ያኮራ ፕሮጀክት እንድንለው አድርጎናል።

ለዚህም ነው መሰል የዘንድሮው የ13ኛው ዓመት መሪ ቃል በህብረት ችለናል የሆነው። እውነትም በህብረት ችለናል፤ ከእንግዲህ በኋላም ለሀገር አንድነትና ህብረት፤ በህብረት ችለን ወደፊት እንራመዳለን። የእናቶችም ጫና ተቀንሶ በጭስ የጮለጮለ ዓይናቸው በርቶ፤ እንባቸው ታብሶ ተስፋን የምናይበት ይሆናል ብዬ አበቃሁ። ቸር ይግጠመን።

**የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት**



## ልዩ እትም




ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ደማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com


# ለውጡ የታደገው - ዓባይ ግድብ!

የዓባይ ግድብ (የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ) ገጥሞት ከነበር የኮንትራት አመራርና አስተዳደር ችግር፣ የማስፈጸምና የመፈጸም ውስንነት፣ ከውስብስበ ሙስና ፣ ብልሹ አሠራርና ዝርክርክነት ተላቆ ከለየለት ክሽፈት ድኖ ነፍስ የዘራው በለውጡ ማግሥት በተሰጠው አመራር ነው። ስለሆነም የዓባይ ግድብ የለውጡ ትሩፋትና ደማቅ ዐሻራ ያረፈበት ሜጋ ፕሮጀክት ነው ማለት ይቻላል።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፣ እንደ ስሙ አንድምታው ከኢኮኖሚያዊ አውታርነት አድማስ ባሻገር ነው። የኢትዮጵያን የሕዳሴ ጉዞ ችቦ የለኮሰም ነው ይቻላል። ሲጠናቀቅ የብርሃን ጭላንጭል ለናፈቃቸው ከ50 ሚሊየን በላይ ወገኖች ጸዳል ሊሆን አሸቷል። በተደጋጋሚ በሚከሰት የኃይል መቆራረጥና እጥረት አሳሩን እየበላ ለሚገኘው ኢንዱስትሪም ሆነ ሌላ የኢኮኖሚ ዘርፍ የምስራች ይዟል።

የኤሌክትሪክ ኃይል በመሸጥ በዓመት ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘትም አልሟል። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ በቀጣናው ከፍ ሲልም በአፍሪካም ሆነ በዓለም የሚኖራትን ጂኦፖለቲካዊ ተጽዕኖ ከፍ ያደርጋል። ይህ አንድ ላይ ሲደማመር ለኢትዮጵያ ሕዳሴ መበሰር ነጮች እንደሚሉት የመስፈንጠሪያ ሰሌዳ /spring- board/ ይሆናል ።

> እነሆ አሁን የሕዳሴ ግድብ ከንድፍ አልፎ፣ ግንባታው ተገባድዶ፣ ግዙፍ ውኃ በጉያው ይዞ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ዛሬ ዓባይ ተረት ሳይሆን የሚጨበጥ እውነት ነው፤ ከዘፈንና እንጉርጉሮ ወጥቶ ኢትዮጵያን ኃይል ሆኖ ሊያበረታት ከጫፍ ደርሷል። በፈጣሪ ርዳታና በኢትዮጵያዊ ወኔ ሙሉ በሙሉ ግንባታውን አጠናቅቀን የልባችን እንደሚሞላ አልጠራጠርም

የኢትዮጵያ ሕዳሴ ወሳኝ መታጠፊያ /critical juncture/ የሆነው ይህ ግዙፍ ሕልምና ራዕይ እውን ሆኖ ከአንድም በሁለት ተርባይን 550 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የበቃው በመላው ኢትዮጵያዊ ርብርብ ነው። ከሊስትሮ እስከ እንጨት ለቃሚ ፤ ከሕጻናት እስከ አረጋውያን ፤ ካጣ ከነጣ ድሃ እስከ ባለጠጋና ባለሀብት ፤ ከሀገሬው እስከ ዲያስፓራው ፣ ወዘተረፈ ጠጠር ያልጣለ የለም። ከዓመት ልብሱ ከእለት ጉርሱ ቀንሶ ፣ ከልጆቹ ጉሮሮ ቀምቶ የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ ገዝቷል። ገንዘብ አበርክቷል። ለግሷል። ጉልበቱንና እውቀቱን አዋጥቷል። ከፍ ሲልም ሕይወቱን ሰውቷል።

በሀገሪቱ ታሪክ ኢትዮጵያዊ በሞላ ያለ ልዩነት እስላም ክርስቲያን ፤ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ሀድያ፣... ሳይል በአንድነት ሠራዊትና ደጀን የሆነለት ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። በነገራችን ላይ በሀገሪቱ ታሪክ በብዙ ሚሊየን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለአንድ ሜጋ ፕሮጀክት ይሄን ያህል ገንዘብ አዋጥተው አያውቁም። የዛሬው ትውልድ በሕዳሴው ያሳየው ርብርብ የቀደሙትን ትውልዶች ክብረ ወሰን ሁሉ ሰባብሯል ማለት ይቻላል። ተደቅኖበት ከነበረ የለየለት የክሽፈት አደጋ ታድጎ በእነዚህ ቀውጢና ፈታኝና እልህ አስጨራሽ ዓመታት ሁሉ ጥርሱን ነክሶ በአጭር ታጥቆና ህልቆ መሳፍርት ለሌለው ጫና አንድ ጊዜም ሸብረክ ሳይል ለዚህ ያበቃው የለውጥ ኃይልም ያለ ምንም ስስትና ንፍገት በልኩ እውቅና ሊቸረው ይገባል።

የእንችላለን መንፈስን ለኢትዮጵያውያን ከፍ ሲልም ለመላው አፍሪካ ያጋባው የሕዳሴው ግድብ ዳግማዊ ዓድዋ ነው። ካለምንም ርዳታና ብድር በዜጎች አበርክቶና በመንግሥት በጀት እየተገነባ ያለ ተምሳሌታዊ ብሔራዊ ፕሮጀክት ነው። እስካሁን ወደ 200 ቢሊየን ብር የሚጠጋ ወጪ የተደረገለት ሲሆን ፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ አፈፃፀም 95 በመቶ፤ የግድቡ አጠቃላይ የሲቪል ሥራው ግንባታ ደረጃ ደግሞ 98.9 በመቶ ደርሷል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ሁለተኛ ተርባይንን የኃይል ማመንጨትን ካስጀመሩ በኋላ አስተላልፈውት የነበር ጥልቅና ወካይ መልዕክት ለዚህ ጥሩ አብነት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ መልዕክታቸው፡-

“በታሪክ ውስጥ ማለፍና ታሪክ ሠርቶ ማለፍ የሚባሉ ሁለት ነገሮች አሉ። በታሪክ ውስጥ ማለፍ ዕድል፣ ታሪክ ሠርቶ ማለፍ ግን ዕድልም ድልም ነው። ይሄ ትውልድ በዓባይ ግድብ ጉዳይ ባለ ዕድልም ባለ ድልም ነው። የሺ ትውልድ ጥያቄ በሚመለስበት ዘመን ተገኝቶ ግድቡ ሲገደብ በዓይን ማየት፣ በእጅ መዳሰስ፣ በእግር መርገጥ ባለ ዕድል ሲያደርግ፤ ለግንባታው ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ከለገሡት፣ በዲፕሎማሲና በሚዲያ ለዓባይ ከሚከራከሩት፣ ታሪክ ሠሪ ጀግኖች ወገን መሆን ደግሞ ባለ ድል ያደርጋል። እነሆ አሁን የሕዳሴ ግድብ ከንድፍ አልፎ፣ ግንባታው ተገባድዶ፣ ግዙፍ ውኃ በጉያው ይዞ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። ዛሬ ዓባይ ተረት ሳይሆን የሚጨበጥ እውነት ነው፤ ከዘፈንና እንጉርጉሮ ወጥቶ ኢትዮጵያን ኃይል ሆኖ ሊያበረታት ከጫፍ ደርሷል። በፈጣሪ ርዳታና በኢትዮጵያዊ ወኔ ሙሉ በሙሉ ግንባታውን አጠናቅቀን የልባችን እንደሚሞላ አልጠራጠርም። እንኳን ደስ ያለን!!” ነበር ያሉት።

የመጀመሪያውን የውሃ ሙሊት ሐምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ እንዲይዝ ተደርጓል። ሁለተኛው የውሃ ሙሊት ደግሞ ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም 13 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በመያዝ ተጠናቋል። በሶስተኛው የውሃ ሙሊት ደግሞ 22 ቢሊየን ሜትር ኪዩብ ገደማ ውሃ መያዝ ችሏል። ይህ ሀገራዊ ግዙፍ የብርሃን እሸት የምስራች እንካችሁ ብሏል።

ከየካቲት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በአንድ ተርባይን ብቻ 275 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። የሁለተኛው ተርባይን ደግሞ 275 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል። አራተኛው የውሃ ሙሊትም ተጠናቋል። ግድቡ የያዘው የውሃ መጠንም ወደ 42 ቢሊየን ሜትር ኩብ አድጓል። ግድቡ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ የሚያመርተው ኤሌክትሪክ ኃይል 5ሺ150 ሜጋ ዋት ይደርሳል። ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚይዘው ውሃ መጠን ወደ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ከፍ ይላል ተብሎ ይጠበቃል።

በ2016 በጀት ዓመት ስምንት ወራት ውስጥ ለታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባት ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን እና የግድቡ ግንባት ከተጀመረበት 2003 አንስቶ እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከሀገር ውስጥ፣ ከውጭ እና ከቦንድ ሽያጭ ልገሳ እና ከልዩ ልዩ ገቢዎች 19 ቢሊዬን ያህል ሀብት ማመንጨት ተችሏል። ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሌላ ንግግር ስንመለስ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ 3ኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቁን በግድቡ ቦታ ተገኝተው ሲያበስሩ፡-

“የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ ደስ የሚያሰኝ ታላቅ ድል ነው ። ሆኖም ዓባይ ለኢትዮጵያ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ለዓለም ተሰጥቷል።” ብለዋል። በእሳቸው አመራር ግድቡ ገጥመውት የነበሩ ስር የሰደዱ ብልሹ አሠራሮች፣ ሙስናና ደካማ የኮንትራት አስተዳደር ተለይተው የእርምት ርምጃ መወሰዱ ታላቁን የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ከክሽፈትና ከለየለት ውድቀት ከመታደግ አልፎ ለኢትዮጵያውያን እራትና መብራት ሊሆን ሁለተኛ እሸት የምስራች ብሎ ለአጠቃላዩ ተዘጋጅቷል።

የግብፅን፣ የሱዳንን፣ የአሜሪካና የምዕራባውያንን፣ እንዲሁም የዓረብ ሊግን ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጫናን በጥበብና በማስተዋል መቋቋም ተችሏል። ግብፅ የግድቡን ጉዳይ የዓለም የደህንነትና የሰላም ስጋት አድርጋ ለማሳየት መጀመሪያ ራሷ በኋላ በዓረብ ሊግ አይዞሽ ባይነት ቱኒዚያን በመጠቀም ጉዳዩን ከአፍሪካ ሕብረት በማውጣት ወደ መንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት አጀንዳነት ለማሳደግ ጥራለች። ሆኖም ሀገራችን በጥብቅ ዲፕሎማሲያዊ ዲስፕሊንና በጥበብ በተመራ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ሀገራትን ከጎኗ በማሰለፍ የተደገሰላት ደባ እንዲከሽፍ አድርጋለች። የግድቡ ጉዳይ የተፋሰሱ ሀገራትና የአፍሪካ ሕብረት እንጂ የመንግሥታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ጉዳይ አለመሆኑን ማረጋገጥ ችላለች።

በዚህም ድርድሩም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አፍሪካ ሕብረት ተመልሷል። ምንም እንኳ ግብጽና ሱዳን ሰበብ አስባብ እየደረደሩና ፍላጎታቸውን በሌላ መንገድ ለማራመድ ላይ ታች እያሉ ቢሆንም፤ ጣልቃ ለመግባት አሰፍስፈው የነበሩ ምዕራባውያንም እርማቸውን እንዲያወጡ አድርጋለች። ሆኖም ዛሬም ሆነ ጥንት ግብፅ አልተኛችልንም። ዓባይን ከመነሻው ለመቆጣጠር ከ11 ጊዜ በላይ ልትወረን፣ ልታስገብረንና ቅኝ ልትገዛን ሞክራ እንዳልተሳካላት የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። በዲፕሎማሲው መድረክ ብትረታም ሀገርን ለከዱ ጡት ነካሾች የገንዘብ፣ የጦር መሳሪያ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ድጋፍ በማድረግ ሀገራችንን ወደ ለየለት ቀውስና ትርምስ ለመክተት ቀን ከሌት እየሰራች ነበር።

ግድቡ በአሁኑ ሰዓት ከ42 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በላይ ውሃ በመያዝ ራሱን መከላከል የሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ግብፅ ለዘመናት ኢትዮጵያ ሰላም ሆና አንድነቷ የሚጠናከርና ልማቷም የሚፋጠን ከሆነ ዓባይን ጨምሮ ገና የውሃ ሀብቷን ታለማለች በሚል በስጋት ላይ ያነጣጠረ ስጋት ከውስጥ ተላላኪዎቿ ጋር በመሆን ኢትዮጵያውያንን ለመበታተን ሰርታለች። ሆኖም የግብፅና የተላላኪዎቿ የቀን ቅዠት በጀግኖች ልጆቿ ይመክናል። እየመከነም ይገኛል ።

ያለ ችግር ለአራት ዙር የውሃ ሙሌት እንዳከናወንነን ሁሉ ከዚህ በኋላ የሚቀረን ሙሊት ያለ ምንም ስጋት ይከናወናል። በዚህም ቅኝ ካለመገዛት ጋር ብቻ ተያይዞ የነበረውን ነፃነትና ሉዓላዊነት በኢኮኖሚያዊ በብልፅግና ለመድገም የተጀመረው ጉዞ እውን ይሆናል። እናም ኢትዮጵያ በድህነትና በተመፅዋችነት አንገታቸውን ደፍተው የነበሩ ዜጎች አንገታቸውን ቀና አድርገው በኩራት እንዲራመዱ የሚያደርግ ብሔራዊ (ፍላግሺፕ) ፕሮጀክት ባለቤት መሆን ችላለች።

ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ እንዳሉት፣ በድህነትና በኋላ ቀርነት የሚማቅቅ ሕዝብ የተሟላ ሉዓላዊነት ሊኖረው አይችልም። ስንዴ እየለመኑ፣ እየተመጸወቱ ሉዓላዊነቷን ያላስደፈረች ፤ በነፃነት ታፍራና ተከብራ የኖረች ብሎ መመጻደቅን ድሉን ሙሉ አያደርገውም። ሆኖም የመጀመሪያው፣ ሁለተኛው፣ ሶስተኛውና አራተኛው የሕዳሴው ግድብ ውሃ ሙሊት መከናወኑ፤ 2ኛው ዩኒት ኃይል ማመንጨት መጀመሩ የቀጣናውን ጂኦፖለቲክስ እንደ አዲስ በይኖታል። የግብፅን የውሃ ዲፕሎማሲና ፖለቲካም ከንቱ አድርጎታል። ሆኖም ከዚህ ትልቅ ሥዕል ዓይንን ለማንሳት የሚያስገድዱ ጦርነቶችና ቀውሶች በሰላም እንዲፈቱ ጎን ለጎን ጥረት ሊደረግ ይገባል። ሰላም በሌለበት የተሟላና የተሳካ ልማት ማረጋገጥ ያዳግታልና።

የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አረጋዊ በርሄ በአንድ መድረክ ላይ እንደተናገሩት፤ ታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ፤ ከግድብ በላይ ተምሳሌታዊ የሆነ ፣ የለውጡ ዐሻራ ፤ የትውልዱ ርብርብ ዳና በጉልህ ያረፈበት ሀገራዊ ፕሮጀክት ነው። ለኢትዮጵያውያን ከኃይል ማመንጨትም በላይ ፋይዳው የጎላ፤ ግንባታው ለይቻላል መንፈስ መሠረት የጣለ ፤ በአሁኑ ወቅት ግድቡ ሕዝቡ ባሳየው ቁርጠኝነት እና ተሳትፎ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑንም ያበሰረ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ታሪክ በመተባበር እንደ አንድ ሀገርና ሕዝብ በመሆን ድል የተደረገበት መድረክ የዓድዋ ድል ነው:: በወቅቱ የዘመቱት ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፣ ተዋግተውም ማሸነፋቸው ለኢትዮጵያ ታላቅ ድል እና ዛሬም ድረስ የሚዘከር ገድል መሆን ችሏል:: ዓባይ ግድብም በተመሳሳይ በመላው ኢትዮጵያውያን ጥረት የተገነባ አኩሪ ገድል ነው።

ግድቡ ፖለቲካዊም ሆነ ዲፕሎማሲያዊ እንድምታ ያለው ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ኢትዮጵያ እንዳታድግ ለሚጥሩ ኃይሎች ወሽመጣቸውን የቆረጠ ታላቅ ገድል ነው ብለዋል። የኢትዮጵያን ዕድገት የማይፈልጉ ሀገራት ቀድሞ ይዘው በቆዩት ያረጀ ያፈጀ አቋም ሊቀጥሉ ይፈልጋሉ:: ይሁንና ልክ የአንድነት ተምሳሌት እንደሆነው ዓድዋ አንድ መሆን ሲቻል በትብብር የማይገረሰስ ነገር አይኖርም:: በትብብር ውስጥ መሆን ጠላትም ሆነ ሌላ ፈተና ከፊት ለፊት እንዳይቆም የሚያደርግ ነው:: የሕዳሴ ግድቡንም በተባበረ ክንድ እዚህ ማድረስ የተቻለ በመሆኑ ማንም ወደ ኋላ ሊመልሰው አይችልም::

በመላው ሕዝብ ጥረት ከለውጡ በኋላ ለግድቡ የሚደረገው ድጋፍ ከወትሮው አይሎ መቀጠሉን ገልጸው፤ ለግድቡ እየተበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ፤ ግድቡን ለማጠናቀቅ እስከ አሁን ገቢ እየተሰባሰበ ያለው በቦንድ ሽያጭ ፣ በ8100 A አጭር የጽሁፍ መልዕክት አማካኝነት እንዲሁም በደረት ላይ የሚደረግ ፒን በመሸጥ ሲሆን ፤ ድጋፉ አሁንም ቀጥሏል። ለግድቡ ግንባታ የሚሰበሰበው ገንዘብ በየዓመቱም እየጨመረ መጥቷል። ለአብነት በአጭር የጽሑፍ መልዕክት 8100 A ላይ በሚደረጉ ድጋፎች አማካኝነት በአንድ ወር ውስጥ እስከ 13 ሚሊዮን ብር ድረስ መሰብሰብ ተችሏል። ይሄ ደግሞ ይበል የሚያሰኝ ተግባር እንደመሆኑም መላው ኢትዮጵያዊ ለሕዳሴው የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። በመሆኑም አስቦ መጀመር ብቻ ሳይሆን፤ ከመጀመር ማግስት የሚታዩ ሕጸጾችን አርሞ መፈጸም የሚችል፤ ፕሮጀክትን ከውድቀት መታደግ የለውጥ መንግሥት ሲተባበር ደግሞ ከሕዳሴው በላይ እልፍ ህፋሴዎችን እውን ማድረግ እንደሚችልም የታመነ ነው።።

ሻሎም ! አሜን ።

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት



ልዩ እትም

# የህዳሴ ግድቡ መጠናቀቅ - ለኢኮኖሚው እድገትና ግስጋሴ

አስቴር ኤልያስ



ጉባ መገኛ ወረዳው ነው፤ ክልሉ ደግሞ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ። ይህ ንብረትነቱ የኢትዮጵያውያን የሆነው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ፣ የግንባታው መሠረተ ድንጋይ የተቀመጠው መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ሲሆን፣ ዛሬ 13 ዓመት ሞልቶታል። ዘንድሮ "በኅብረት ችለናል" በሚል መሪ ሐሳብ በተለያየ መርሐግብር የሚከበር መሆኑ ተጠቅሷል።

የህዳሴ ግድቡ ዛሬ ላይ ለመድረሱ ግን የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በከፈለው ከፍተኛ መስዋዕትነት መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። ወደፍጻሜው ለመቃረቡም በመንግሥት በኩል በተፈጠረው ቁርጠኝነት ነው። ግድቡ የመሠረት ድንጋይ ከተጣለበት ጊዜ አንስቶ እስካሁኗ ሰዓት ማነቆው እጅግ ብዙ እንደነበር ይታወሳል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ የህዳሴ ግድቡን እንዳታጠናቅቅ በብዙ ተደክሟል።

በተለይም የኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን የሦስትዮሽ ድርድር ሁሌም እንከን እንዲኖረው በግብፅ በኩል በብርቱ ሲሠራበት ሰንብቷል። ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ምንም አይነት የልማት ሐሳብ እንዳይኖራት ለዘመናት ስትባዝን የኖረች ግብፅ፣ የህዳሴ ግድቡ የመሠረት ድንጋይ ሲቀመጥ በኢትዮጵያ ላይ የማስፈራሪያና የማስጠንቀቂያ ዶፍ ስታዘንብ መክረሟ የሚታወቅ ነው።

ከማስፈራራትና ከያዙኝ ልቀቁኝ በኋላ ዶሴዋን በመያዝ፤ 'ሲሆን ሲሆን ግድቡ እንዳይገነባ በማደርገው ጥረት ከጎኔ ይቆማሉ፤ ካልሆነም ኢትዮጵያ ላይ ጫና ያሳድሩልኛል' ወዳለቻቸው አካላትም፤ ሀገራትም ዘንድ ተንከራታለች። ይሁንና ኢትዮጵያ በግብፅ ግልምጫም ሆነ ዛቻ እንዲሁም በሌሎቹ ሀገራት ጫና ከአቋሟ ዝንፍ ሳትል ግንባታዋን ሌት ተቀን ስታስኬደው ከርማለች።

ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ ያጋጠማት ፈተና በርከት ያለ ከመሆኑም በላይ በየምክንያቱ ብዙ ነገሮችን እንድታጣ ተደርጋለች። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ኢኮኖሚዋ እንዲዋዥቅ በብዙ ተጥሯል። ምክንያቱ ሌላ ይምሰል እንጂ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር ባሉ ዜጎቿ ጫና ተፈጥሯል።

ግብፅ የህዳሴ ግድቡን ወደፀጥታው ምክር ቤት በማመላለስ ኢትዮጵያ በብዙ ጫና ውስጥ እንድታልፍ ከማድረጓም በተጨማሪ ሐሰተኛ በሆነ መረጃዋ፤ አንዳንድ አቅላቸውን በሳቱ አካላት ግድቡን ለማፈንዳት እስከማሰብ ተደርሷል። ስለ ዓባይ ግድብ ምንም የማያገባው የዓረብ ሊግም በጉዳዩ ላይ መግለጫ እስከማውጣት ደርሷል።

ይሁንና የቅኝ ግዛት ስምምነት ላይ ተጣብቃ አልላቀቅም ያለችው ግብፅ ጩኸትም ሆነ የግብፅን የተቃውሞ ስልት ተከትላ በምታሳየው የአቋም መዋዠቅ ወዲህ ወዲያ የምትለው የሱዳን ሁኔታም ኢትዮጵያን ከሥራዋ ለአፍታም ቢሆን አላስቆማትም። ይልቁኑ ከወራት በኋላ ኢትዮጵያውያኑ እንደ አካላቸው ክፋይ የሚያዩት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፍጻሜውን ሊያገኝ ተቃርቧል። አዲስ ዘመንም የግድቡን 13ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ለሚያዘጋጀው ልዩ ዕትም ግድቡ የሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ምን ይሆን ሲል ምሑራንን ጠይቋል።

ምሑራኑ እንደሚሉት፤ በመጀመሪያ ደረጃ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በርከት ያሉ ተግዳሮቶችን ተሻግሮ ለፍጻሜው መድረሱ ከምንም በላይ ትልቅ ስኬት ነው። ብዙዎች ይህ ግድብ እውን እንዳይሆን አቅማቸው የፈቀደላቸውን ሁሉ ማድረጋቸው አይካድም። በብዙ ጥረውና ደክመው የነበረ መሆኑም የሚረሳ አይደለም።

ካነጋገርናቸው ምሑራን መካከል አንዱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በንግድ ሥራ ኮሌጅ የኢኮኖሚክስ መምህር የሆኑት ብርሃኑ ደኑ (ዶ/ር) ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው። የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽልና ቀጣይነት እንዲኖረው ከማድረግ አንጻር አስተዋፅዖው ከፍ ያለ ነው።

ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያውያኑ ጥንካሬ የተገነባው እና ሊጠናቀቅ ጫፍ ላይ የደረሰው የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ለዘመናት ወደኋላ ቀርቶ የነበረውን የኢኮኖሚ እድገት እና ግስጋሴ ወደፊት ለማስፈንጠር ሚናው የጎላ ነው ይላሉ። ሀገሪቷ ልታድግ የምትችልበትን፣ ምርታማነት የሚጨምርበትን፣ በከፍተኛ ደረጃ የሥራ ዕድል የሚከፈትበትንም ዕድል የሚፈጠር እንደሆነ ያስረዳሉ።

ብርሃኑ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ የኢኮኖሚ እድገት እና ጠቀሜታ ማለት አንደኛ የሕዝብን ኑሮ የሚያሻሽል ማለት ነው፡። የሕዝብ ኑሮ ማሻሻል የሚቻለው ደግሞ የሥራ እድልን በመፍጠር ነው። ሕዝብ የሥራ እድል ተፈጥሮለት የሚሠራ ከሆነ የገቢ ምንጭ ተገኘ ማለት ነው። ገቢን ከፍ ለማድረግ ዋንኛው መሠረት የሆነው ምርታማነትን መጨመር እና ማበራከት ነው።

ስለዚህ ሁሉ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ወይም በሁሉም ክፍለ ኢኮኖሚዎች ማለትም በአገልግሎት መስጫ፣ በኢንዱስትሪ እና በግብርናው ዘርፍ ላይ ሁሉ የኤሌክትሪክ ኃይል በከፍተኛ ደረጃ አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው። ዘርፎቹም በተሳለጠ ሁኔታ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የኤሌክትሪክ ኃይል ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው ነው። ስለሆነም ወደፍጻሜው የተቃረበው የህዳሴ ግድቡ ለዚህ ሁነኛ መፍትሔ ነው።

እርሳቸው እንደገለጹት፤ ከዚህ ጎን ለጎን ቀጣይነት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት መቻል ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸውን የምርት አይነቶች በተገቢው መንገድ ማምረት እንዲችሉ ያደርጋል። በየኢንዱስትሪው እና በየፋብሪካው ያሉ ማሽኖች የምንጠቀምባቸው በኤሌክትሪክ ኃይል ነው። ስለዚህም እነዚህ ሁሉ ቀጣይነት ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል አገኙ ማለት በጣም ከፍተኛ የሆነ ምርታማነትን ማምጣት ያስችላቸዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሥራ አጥነት ጠፍቶ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና ሥራ እየተስፋፋ ሲሄድ የሰው ኃይል የሚፈልግ በመሆኑ በርካታ ሰዎች የሥራ እድል ይፈጠርላቸዋል። ኢኮኖሚው እያደገ ሲሄድ በርካታ ዘርፎች የሰው ኃይል ፍላጎት ይኖራቸዋል።

ይህ ማለት ተምረው ሥራ አጥተው የተቀመጡ ዜጎችን ወደ ሥራው መስክ እንዲሳቡ የሚያደርግ ይሆናል የሚሉት ብርሃኑ (ዶ/ር)፣ በርካቶች በሥራ መስክ ተሠማሩ ማለት ገቢ አደገ ማለት ነው ይላሉ። የግለሰብ ገቢ ሲያድግ የራሱ የግለሰቡን ገቢ ከማሻሻል አልፎ በሀገር ደረጃ የመንግሥት ገቢ ከፍ ለማድረግ የራሱ አስተዋፅዖ እንዳለውም ያስረዳሉ። ምክንቱም ዜጎች ሥራ አግኝተው መሥራት ሲጀምሩ ታክስ ከፋይ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ለመንግሥት ገቢ የሚያበረክተው የራሱ የሆነ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። ዜጋውም ሆነ ሀገርም ተጠቃሚ ሆኑ ማለት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ የተያያዘ እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ሲሉ ያመለክታሉ።

የህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ በዓመት በአማካይ 15 ሺ 759 ጊጋ ዋት ሰዓት ኢነርጂ በማመንጨት ለሀገር አቀፍ የኤሌክትሪክ ትስስር ሥርዓት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፤ ኤሌክትሪክ ያልተዳረሰባቸው የገጠር መንደሮችና ከተሞች የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ለማድረግና አቅርቦቱን አሁን ካለበት 44 በመቶ ወደ 90 በመቶ ከፍ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት የዚህ ፕሮጀክት ድርሻ ከፍተኛ ነው።

የህዳሴ ግድቡ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ሲታይ የባሕር ትራንስፖርትና የዓሣ ሀብት ልማት ትልቅ ድርሻ እንዳለው መረጃው የሚጠቅስ ሲሆን፣ 74 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ውሃ የመያዝ አቅም ያለው ሰው ሠራሽ ሐይቅ ስለሚፈጠር በአካባቢው በታንኳ እና በጀልባ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ እንዲሁም በዓለማችንም ተጠቃሽ የቱሪስት መዳረሻም እንደሚሆንም ያመለክታል። በተለይም በግድቡ ዙሪያ የተፈጠረው ሰው ሠራሽ ሐይቅ እየሰፋ ሲሄድና ግንባታው ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅም ከ78 በላይ ደሴቶች የሚፈጠሩ በመሆናቸው ይህም ዋንኛ የቱሪስት ማዕከል እንዲሆን የሚያስችለው መሆኑም ተጠቅሷል።

እንደ ጽሕፈት ቤቱ መረጃ ከሆነ፤ የውሃ አካሉን ተከትሎ ሪዞርቶች የሚገነቡ ይሆናል። የውሃ አካሉ ለዓሣ ልማት እና ለመሳሰሉት ኢኮኖሚያዊ አማራጮች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ቀደም ሲል ተካሂዶ ይፋ በተደረገ ጥናት መሠረትም በዓመት ከ10 ሺ እስከ 50 ሺ ቶን ዓሣ ሊመረትበት እንደሚችል ተጠቁሟል። እስከ 80 ኪሎ ግራም የሚመዝኑ የዓሣ ዝርያዎች በግድቡ መገኘታቸውን ተመልክቷል። ይህ የዓሣ ሀብት በከፍተኛ ደረጃ እየተራባ ሲሆን፣ ግድቡ በቀጣይም ለዓሣ ልማቱ በጣም ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ ታምኖበታል።

የኦሮሚያ ክልልዊ መንግሥት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የቀድሞ ዋና ዳይሬክተርና በአሁኑ ወቅት በቻይና የሦስተኛ ዲግሪያቸውን በመማር ያሉ አቶ አማን አሊ እንደሚሉት፤ ይህ ታላቅ ግድብ እንደቀላል የሚታይ ነገር አይደለም። በእርግጥ ሀገራችን ብዙ የሚነገርላት ታሪክ ያላትና የዚያ አኩሪ ታሪክ ባለቤትም ናት። ኢትዮጵያ በብዙ ጎዳናዎችም ድል ማስመዝገብ የቻለች ናት። ለምሳሌ ዓድዋን መጥቀስ ይቻላል። ኅብረት እና አንድነትን በመፍጠር የተለያየ ታሪክ መሥራት የቻለ ሕዝብ ነው። ይህም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከእነዚህ ታላላቅ ታሪክ ጋር መታየት የሚችል ነው።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ግብፅ የህዳሴ ግድቡ እውን እንዳይሆን የምታደርገው ጥረት ሁሉ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋ እንዳያድግ በማሰብ ነው። ምክንያቱም ግድቡ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው። በተለይም ከሥራ አንድ ሀገር የማይቆራረጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አገኘ ማለት ተከታታይነት ያለው እድገት ለማስመዝገብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

የህዳሴ ግድቡ ተጠናቅቆ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንደሚያመጣለትም ሕዝቡ ስለሚያውቅ ከጉድለቱ ሁሉ ሲለግስ እንደነበር አቶ አማን አስታውሰው፤ ትናንት ከባዶ ነገራቸው ስጦታ ያበረከቱ ዛሬ በተለያየ መስክ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ጊዜ ቀርቧል ሲሉ ያስረዳሉ።

የህዳሴ ግድቡ የሁላችንም ንብረት በመሆኑም ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳውም በተጨማሪ አንድ በማድረጉ ላይ ትልቅ ትርጉም አለው የሚሉት አቶ አማን፣ እኛ ያለን ሀብት ነገ ተነገወዲያ እየበረከተና እየሰፋ ገቢ የሚያስገኝ ነው። ከዚህ በኋላም ልክ እንደታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሁሉ በሌሎችም ሀብቶቻችን ላይ የተለያዩ ሥራዎች መሥራት የሚቻል በመሆኑ ኢኮኖሚው እያደገና የበለጸገ የሚሄድ ይሆናል ብለዋል።

ኢትዮጵያን ያለ ህዳሴ ግድብ ብናስባት በትክክል የምንደግመው ያለፈውን አይነት ኢኮኖሚያዊ ኋላ ቀርነትን ነው የሚሉት ብርሃኑ (ዶ/ር)፣ በኢኮኖሚ ኋላ ቀርነት ማለት ለልመና ራስን መዳረግ እንደማለት ነው ሲሉ ያስረዳሉ። ስለዚህም በቅርቡ የሚጠናቀቀው የህዳሴ ግድብ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቅ ፋይዳ ያለው ነው ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ አንዱ እና ትልቁ ነገር ከኋላ ቀርነታችን ሊያላቅቀን ያልቻለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማጣታችን ነው። ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል የምንጠቀምባቸው የምርት መገልገያ መሣሪያዎችን ማንቀሳቀስ አንችልም። ፈጥነን በማምረት ተወዳዳሪነትን ማሳየት አንችልም። በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪነትን አሳይተን እና ገበያዎችን ሰብረን ገብተን የምናመርታቸውን እቃዎቻችንን በተሻለ ሁኔታ መሸጥ እና መገበያየት አንችልም። ስለዚህ የግድቡ መጠናቀቅ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው ነው።

ምሑራኑ እንደሚሉት፤ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ በኋላ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ተጠቃሚ ለመሆን የህዳሴ ግድቡን ሳናጠናቅቅ 'እፎይ!' ልንል አይገባም። ስለዚህ ፍጻሜው ስር ደርሰን ልናርፍ አይገባም። እስከ ዛሬ ድረስ የየበኩላችንን በማድረግ ወደፍጻሜው ተቃርበናል። ይህን ስናደርግ ደግሞ ሳንልፈሰፈስ፣ ሳንደክምና ለፕሮፖጋንዳ እጅ ሳንሰጥ ነው። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በዚህ በመጨረሻው ትንቅንቅ ላይ ተሳታፊ ከሆነ ከፍጻሜው የሚገኘውን ትሩፋት ተቋዳሽ ይሆናል ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት ትሩፋቱን ልንቋደስ ከጫፍ እንደመድረሳችን ለፍጻሜው እንቀደመው ሁሉ ከሁላችንም ያላሰለሰ ድጋፍ ያሻል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት



## ልዩ እትም

# የኢትዮጵያውያን የመቻል አቅም ማሳያው - ዓባይ ግድብ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያውያን የማይደፈር የሚመስለውን ደፍረው፣ የማይቻል የሚመስለውን ችለው በአንድነት የጀመሩትን፣ በአንድነት በማጠናቀቅ ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ። ለእዚህ ደግሞ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። በከፈሉት ዋጋም ልክ ዛሬ የግድቡን ግንባታ 95 በመቶ አድርሰዋል። :

መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን በዓባይ ወንዝ ላይ የዓባይ ግድብን ለመገንባት የመሠረት ድንጋይ ካኖሩ እነሆ 13 ዓመታት ተቆጠሩ። የመላው ኢትዮጵያውያንን ርብርብ የጠየቀው የዚህ ግድብ ግንባታ በእነዚህ ዓመታት የመላ ኢትዮጵያውያን ርብርብ ተደርጎበታል፤ በሌላ በኩልም በውጭ ኃይሎችና በሀገር ውስጥ ጠላቶች በብዙ ተፈትኗል።

«ትዕግስት ፍሬዋ ጣፋጭ ነው» እንዲሉ ታዲያ የመላው ኢትዮጵያውያን ተስፋ የሆነው የዓባይ ግድብ በብዙ ጥረትና ትጋት ዛሬ ላይ ደርሶ የኢትዮጵያውያን የመቻል አቅም ማሳያ ሆኗል። ፕሮጀክቱ በገጠሙት ውጣ ውረዶች ምክንያት ይጠናቀቃል ከተባለበት ጊዜ እጅግ ቢዘገይም፣ ከታቀደለት ገንዘብ በላይ ከፍተኛ ወጪ ቢጠይቅም፣ ኢትዮጵያውያኑ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ አንድነታቸውን አጠናክረው በመቀጠል ከማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ አድርሰውታል። በመሆኑም ግድቡ የኢትዮጵያውያን የመቻል ሚዛን የተጠበቀበት እንዲሁም የማድረግ አቅም ማሳያ ምልክት ሆኗል።

ይህ በሀገር ልጅ ጥሪት ብቻ እየተገነባ ያለ ግዙፍ ፕሮጀክት ኢትዮጵያውያን «እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን» በሚል መርሕ ከሕይወት መስዋዕትነት ጀምሮ ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ አበርክተውታል። በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግሥት ለፕሮጀክቱ ትልቅ ትኩረት በመስጠቱ ግንባታው ሳይስተጓጎል መቀጠል ችሏል። በመሆኑም ግድቡ ዛሬ 13ኛ ዓመቱ ሲከበር አጠቃላይ የግድቡ ግንባታ አፈጻጸምም በአማካይ ከ95 በመቶ በላይ ደርሷል። ይህንን የመቻል ማሳያ በግሉ ዘርፍ ኩባንያዎችን በማንቀሳቀስ የሚታወቁት ኢትዮጵያውያን ታዋቂ ሰዎች መላ ኢትዮጵያውያን በእጅጉ አስተሳስሮ ለፍጻሜ የተቃረበ ብለውታል።

የቀድሞው የሜድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ሥራ አስፈጻሚ አረጋ ይርዳው (ዶ/ር) የዓባይ ግድብ በሀገሪቱ አሉ ከሚባሉ ማናቸውም ፕሮጀክቶች እጅግ ግዙፉና ታሪካዊ ፕሮጀክት መሆኑን ይገልጻሉ። ግድቡ የእያንዳንዱ ዜጋ ዐሻራ ያረፈበት፣ የሀገሪቷ ኢኮኖሚ እድገት አጋር፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጉጉት የሚጠብቀው፣ መላ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው መጓዝ እንዲችሉ አንድነትን በመፍጠር ትልቅ ምሳሌ የሆነ ፕሮጀክት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

«አንዳንድ ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ሲገቡ ይሄ ቢቀድም ያኛው ቢዘገይ ይባላል። » ያሉት አረጋ(ዶ/ር)፣ ዓባይ ግድብ ላይ ግን እንዲህ አይነት አስተያየቶች የሉም» ሲሉ ገልጸዋል። ምክንያቱ ደግሞ ኢትዮጵያውያንን አንድ ያደረገና ሁሉም ሰው በአንድ አይነት ስሜት በጉጉት የሚጠብቀው ፕሮጀክት በመሆኑ ነው ብለዋል።

ወደፊትም ሁለት፣ ሦስት፣ አራት... መሰል ፕሮጀክቶች እየመጡ ተግባራዊ እንደሚሆኑ ተስፋ አለኝ ሲሉም አመልክተው፣ ፕሮጀክቱ ዛሬ በ13 ዓመት የግንባታ ጉዞው 95 በመቶ መድረስ መቻሉም እጅግ እንዳስደሰታቸውና እንዳስደመማቸው ገልጸዋል።

የፕሮጀክቱ ግንባታ 95 በመቶ በመድረሱ ሁለት ጉዳዮችን እንደሚመለከቱ የጠቀሱት አረጋ (ዶ/ር)፣ አንደኛው እንደ መሐንዲስ የምመለከተው ግድቡ ቦታ ላይ የተሠራው የሲቪል ሥራው (ግንባታው) ብቻ ከሆነ እሱ ምንጭ (ሶርስ) እንደሆነ ተናግረዋል፤ በግድቡ ቦታ የተሠራው የሲቪል ሥራ ትልቅ መሆኑን አስታውቀዋል። በዚህ ሥራ የተገኘውን ምንጭ ወደሚፈለገው አካባቢ ማከፋፈል ሌላው ሁለተኛው ሥራ እንደሆነ ጠቁመዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ሁለተኛው ሥራ የተገኘውን የኤሌክትሪክ ኃይል (ሀብት) ካለበት ቦታ ወደ ሚፈለገው አካባቢ ማሰራጨት ያስፈልጋል። ይህን ሀብት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ተደራሽ መሆን እንዲችል መስመር የመዘርጋቱ ሥራም ሌላኛው ፕሮጀክት ነው።

ስለዚህ ፕሮጀክቱ 95 በመቶ ደረሰ ሲባል የሲቪል ሥራው የደረሰበት ደረጃ እና የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራዎቹን ጨምሮ ከሆነ እሰየው ነው የሚሉት አረጋ (ዶ/ር)፤ የግድቡ ጀነሬተሮች ተከላ ተጠናቅቆ ከዚህ በኋላ የስርጭት ሥራ ብቻ የሚቀር ከሆነም በግልጽ ማስቀመጥ ተገቢ እንደሆነ አስታውቀዋል።



አረጋ ይርዳው (ዶ/ር)



አቶ ሳሙኤል ታፈሰ

በእሳቸው እምነት የግድቡ ሥራ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀቀ የሚባለው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ደጅ ሲደርስ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ሁለተኛው ፌዝ ብዙ ሥራ ይኖረዋል የሚል ዕምነት እንዳላቸው አስገንዝበዋል። ያም ቢሆን አይቻልም የተባለው ተችሎ ሥራው ሳይስተጓጎል ዛሬ ላይ መድረሱ መላው ኢትዮጵያውያንን የሚያስደስትና የሚያስደንቅ ነው ብለዋል።

ብዙ ሰዎች ግድቡ ብዙ ዓመት እንደወሰደና ከተቀመጠለት ወጪ በላይ እንደጠየቀ ሲናገሩ ይደመጣል ያሉት አረጋ (ዶ/ር)፤ ግድቡ የቱንም ያህል ጊዜና ገንዘብ ቢወስድ ብዙ ነገር የሠራ፣ የለወጠና ብዙ ያተረፍንበት ነው ሲሉም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ቴክኖሎጂን በማምጣት ኢትዮጵያውያን በዚህ ሙያ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ ጉልህ አበርክቶ አድርጓል። አፍሪካ ብዙ ግድቦች የሚያስፈልጋት እንደመሆኗ ይህን ዕውቀት በሀገሪቱ መፍጠር መቻሉ ትልቅ ዕድል ነው። በመሆኑም ከኤሌክትሪክ ኃይል በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን ክህሎታቸውንና ሙያቸውን ጭምር ኤክስፖርት ማድረግ የሚችሉበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ስለዚህ ግዱቡ የወሰደው ጊዜና ገንዘብ ካበረከተው አስተዋፅዖ አንጻር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ግድቡ ለኢትዮጵያውያን ትምህርትና ሥራ ከመሆን ባለፈ ትልቅ ሀገራዊ ዕድገት አምጥቷል ብለዋል።

መላው ኢትዮጵያውያን የተረባረቡበት የዚህ ግድብ ግንባታ ሲጀመር አንስቶ ሁሉም የኢትዮጵያ መንግሥታት ድርሻ እንደነበራቸው የጠቀሱት አረጋ (ዶ/ር)፤ ሀገሪቷን የሚመራ መንግሥት ሁሉ መንግሥት ነው። መንግሥትነት እንደማንኛውም ሥራ በቅብብሎሽ የሚሄድ እንደመሆኑ የግድቡን ሥራ ለጠነሰሱትም፤ ለጀመሩትም፤ መሐል ላይ ላደረሱትም ሆነ ላጠናቀቁት መንግሥታት እኩል ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል፤ ሊመሰገኑም ይገባል ብለዋል። ወደፊትም ተቀብለው የሚሠሩ በመኖራቸውም ለሁሉም እንደየተሳትፏቸው ዋጋ መስጠት እንደሚገባ ገልጸዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ከመንግሥት ባለፈም በርካታ ሰዎችም ተሳትፎ አላቸው፤ ሼር በመግዛትና በሌሎች ድጋፎች የተረባረቡ ሁሉ መመስገን ይኖርባቸዋል። ምንም ሼር ያልገዙና ያላዋጡ ወደፊት የሚመጡ ትውልዶችም በተጠቃሚነት የሚያግዙ እንደመሆናቸው ሊመሰገኑ ይገባል።

እንደዚህ አይነት ግድብ ወደፊት ጥገና የሚያስፈልገውና ቀጥለው መሠራት ያለባቸው የተለያዩ ሥራዎች እንደሚኖሩትም አስታውቀው፣ ሥራው መጪው ትውልድ ተረክቦ በቅብብሎሽ የሚያስቀጥለው መሆኑንም ተናግረዋል። ስለዚህ ፕሮጀክቱን ወደፊት የሚያስፋፉትና የሚጠቀሙትም ጭምር ይመሰገናሉ። ምክንያቱም ማመንጨት ብቻ ሳይሆን መጠቀምም ያስፈልጋል፤ ደንበኛ ንጉሥ ነው እንደሚባለው የሚጠቀሙትንም ማመስገን ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን የውጭ ወራሪ ጠላትን ለመመከት በአንድነት ቆመው ባደረጉት ተጋድሎ የጦርነት ስጋትን ማስወገድ እንደቻሉ ሁሉ፤ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያውያን በዓባይ ወንዝ ላይ በገነቡት ግድብ ድህነት የተባለውን ጠላት ተባብሮ ማጥፋት እንደሚቻል አሳይተዋል ሲሉ አረጋ (ዶ/ር) ገልጸዋል። ዓድዋና የዓባይ ግድብ በመንፈሳቸው ተመሳሳይነት እንዳላቸው ጠቅሰው፣ አንድነትን በማጠናከር ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነን ድህነት የተባለውን ጠላት ማጥፋትና ሀገሪቷ እንድትበለጽግ መሥራት ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ የቤት ሥራ ነው ብለዋል።

‹‹ብዙዎቻችን በተለያዩ ጉዳዮች ላንስማማ እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን በዓባይ ግድብ ጉዳይ ከከተማ እስከ ገጠር ያለው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለ ልዩነት አንድ አቋም ነው ያለው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልገዋል። ሁሉም መልማትና መበልጸግ ይፈልጋል››

አረጋ (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ ወደፊት ሀገራት የሚለኩት በወታደር ኃይላቸው ሳይሆን፤ በኢኮኖሚያቸው ነው፤ አንድ ሀገር ትልቅና ኃያል ሆኖ የሚታየው በኢኮኖሚ ነው። ኢኮኖሚን ከማዳበር አንጻር ደግሞ የዓባይ ግድብ የሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ትልቅ አቅም ይሆናል። ለዚህም ዓረብ አገራት በነዳጅ አማካኝነት በዶላር እንደሚንበሸበሹ ሁሉ ኢትዮጵያም ከነዳጅ የበለጠ ንጹሕ የሆነውን የኤሌክትሪክ ኃይል በምትሸጥበት ጊዜ በኢኮኖሚ የበለፀገች ትልቅ አገር መፍጠር ትችላለች።

የሰንሻይን ኢንቨስትመንት ግሩፕ ባለቤት አቶ ሳሙኤል ታፈሰ በበኩላቸው የዓባይ ግድብ ብዙ የተለፋበትና ፈተና የታየበት የመላው ኢትዮጵያውያን ኩራት መሆኑን ይገልጻሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያን ዕድገት የማይፈልጉ ሀገራት ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባውን ግድብ ለማስተጓጎል ብዙ ድንጋይ ፈንቅለዋል። ኢትዮጵያውያን ተስፋ ሳይቆርጡ በርብርብ ግድቡን ዛሬ ላይ አድርሰውታል። አጠቃላይ የግድቡ ግንባታም አሁን ላይ 95 በመቶ መድረሱ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እጅግ እንዳስደሰታቸው አቶ ሳሙኤል ተናግረዋል።

የግድቡ ግንባታ ዛሬ ላይ 95 በመቶ መድረስ መቻሉ አለቀ እንደማለት ነው በማለት ያስረዱት አቶ ሳሙኤል፤ የቀሩት ሥራዎች ቀሪውን የውሃ ሙሌትና የተርባይን ተከላ ማጠናቀቅ መሆናቸውን ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህ እንደ ሀገር የሚያኮራና ትልቅ ለውጥ ነው። ዛሬ ነዳጅ የሚፈልገው መኪና በአዳዲስ ቴክኖሎጂ በኤሌክትሪክ የመተካት ዕድሉ ሰፊ ነው። የኤሌክትሪክ ኃይል ግን የማይቋረጥ ፍላጎት ያለውና በምንም ቴክኖሎጂ የማይተካ ለፋብሪካም ሆነ ለማንኛውም አገልግሎት አስፈላጊ በመሆኑ እጅግ ተመራጭ ነው። ከዚህ በኋላም ሙሉ ለሙሉ ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት የሚችልበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። ይህም እጅግ የሚስደስትና የሚያኮራ ነው ብለዋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ ዛሬ ላይ መድረሱን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በጉጉት ሲጠብቀው መቆየቱን አቶ ሳሙኤል ጠቅሰው፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ካለው ላይ ቀንሶ ተሳትፎ ያደረገበትና በሙያው፣ በጉልበቱና በገንዘቡ ብዙ ያወጣበት እንደሆነ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የግድቡ ትልቅና ከባዱ ሥራ የሲቪል ሥራው ሲሆን የሜካኒካል ሥራ ደግሞ የመጨረሻውና ቀላል ሥራ እንደመሆኑ ተርባይኑ ማምጣትና መግጠም በመሆኑ እዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ እጅግ የሚያስደስትና ለመላው ኢትዮጵያውያን ትልቅ የምሥራች ነው።


ግድቡ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ኢትዮጵያዊ አንድነትን በማጠናከር ትልቅ ምሳሌ ነው የሚሉት አቶ ሳሙኤል፤ በሀገሪቱ አሁን ላይ የእርስ በእርስ ግጭቶችና መከፋፈሎች ቢኖሩም በዓባይ ግድብ ጉዳይ ግን መላው ኢትዮጵያዊ አቋሙ አንድና አንድ ነው በማለት ያስረዳሉ።

«ብዙዎቻችን በተለያዩ ጉዳዮች ላንስማማ እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን በዓባይ ግድብ ጉዳይ ከከተማ እስከ ገጠር ያለው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያለ ልዩነት አንድ አቋም ነው ያለው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልገዋል። ሁሉም መልማትና መበልጸግ ይፈልጋል» በማለት ግድቡ የሁሉምና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የሚስተሳሰር እንደሆነ አስረድተዋል።

የኤሌክትሪክ ኃይል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን እንደሚሰጥ ጠቅሰው፣ እንደ ሀገር የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ጉልህ ነው ይላሉ። አንድ ፋብሪካ ቢከፈት የኤሌክትሪክ ኃይል ከሌለ ምንም ጥቅም እንደማይኖረው አስታውቀው፣ በየትም አገር ውድ የሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል በሀገር ውስጥ መኖሩ በሀገሪቱ በርካታ ፋብሪካዎች እንዲከፈቱና ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ዕድል ይሰጣል ብለዋል። ከዚህ ባለፈም የኃይል ምንጩን ለጎረቤት ሀገራት በመሸጥ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪም እንዲሁ ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ይዞ የሚመጣው በረከት የኢትዮጵያን መጻኢ ተስፋ ብሩህ ያደርጋል ሲሉ አቶ ሳሙኤል አስታውቀዋል።

ከውጭ ድጋፍ ሳይገኝ በኢትዮጵያውያን አንጡራ ሃብት ብቻ የተገነባውን የዓባይ ግድብን ግንባታ ለመጀመር ጀምሮም ለማጠናቀቅ በየዘመኑ የነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥታት ጥረት ማድረጋቸውን እሳቸውም ጠቅሰው፤ ለእዚህ ሚናቸው ሊመሰገኑ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ሀገሪቷ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሆና ግንባታው ሳይስተጓጎል እንዲቀጥል መደረጉ መንግሥትን እጅግ የሚያስመሰግን እንደሆነ የገለጹት አቶ ሳሙኤል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም በህዳሴ ግድብ ጉዳይ ያለውን አቋም አንድ በማድረግ በጉልበቱ፣ በገንዘቡ፣ በሙያውና በተለያዩ ድጋፎች ተረባርቦ ዛሬ ላይ ያደረሰ በመሆኑ ትልቅ ምስጋና የሚገባው ነው በማለት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእንኳን ደስአላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



# ጎብኚዎቹን አምባሳደሩ ያደረገው ግድብ

ወርቅነሽ ደምሰው



ግድቡ እስከ አሁን ከ300 ሺ በሚበልጡ ኢትዮጵያውያን ተጎብኝቷል፤

የአባይ ግድብ ግንባታ የዛሬ 13 ዓመት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በይፋ ከተበሰረበት አንስቶ ኢትዮጵያውያን ግድቡ እውን እንዲሆን ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል። መንግስታቸው ባደረገላቸው ጥሪ መሰረት ድጋፋቸውን አደባባይ በመውጣት ባረጋገጡትና ግንባታውን ለመደገፍ ቃል በገቡት መሰረት ለግድቡ ግንባታ የሚያስፈልገውን የፋይናንስ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያውያኑ ለግንባታው ተጠናክሮ መቀጠል ትልቅ አቅም በመሆን በርካታ ተግባሮችን ሲያከናወኑ ቆይተዋል።

ከእነዚህ ተግባሮች መካከል በግንባታው ስፍራ በአካል በመገኘት በስፍራው እየተካሄደ የሚገኘውን ርብርብ ተመልክተዋል፤ በዚህም መሰረት ጋዜጠኛው እየተከናወነ ያለውን ተግባር በመዘገብ፣ ባለሀብቱ ለተጨማሪ ድጋፍ ራሱን በማዘጋጀት፣ ዲፕሎማቱ በዲፕሎማሲው መስክ በመፋለም፣ የመከላከያ፣ የፖሊስና ሌሎች የጸጥታ አካላት ግንባታው ያለምንም የጸጥታ ችግር ተጠናክሮ እንዲቀጥል በድጋሚ ቃል በመግባት ለግድቡ ግንባታ ተጨማሪ አቅም መሆን ችለዋል።

መምህር መለሰ በቀለ ግድቡን የመጎብኘት እድል አግኝተው በ2009 ዓ.ም ጎብኝተዋል። መምህሩ ግድቡን ለመጎብኘት እድሉን ሲያገኙ ከመጠን ያለፈ ደስታ ተሰምቷቸው እንደነበር ያስታውሳሉ።

ኢትዮጵያ ግድቡን በራሷ አቅም በኢትዮጵያውያን የተባበር ክንድ ለመገንባት ይቻላል ብላ ስትነሳ ሕዝቡ ለግንባታው ድጋፉን በሰላማዊ ሰልፍ ማረጋገጡን ጠቅሰው፣ የገባውን ቃል በቻለው አቅም ሁሉ ሲደግፍ መቆየቱን መምህር መለሰ ይገልጻሉ። ይህ ሁሉ የኢትዮጵያውያን አሻራ ያረፈበትን ግድብ ግንባታ ሂደት ለመጎብኘት እድሉን አግኝተው ቦታ ላይ በተገኙበት ወቅት በተመለከቱትና በተሰጣቸው ማብራሪያ በእጅጉ ተደንቀዋል፤ ተገርመዋል።

እሳቸው ግድቡን የጎበኙበት ወቅት ግንባታው ገና በጅምር ላይ እንደነበር አስታውሰው፣ በዚያ ደረጃም እየተሰራ የነበረው ስራ ግን ለኢትዮጵያውያን የተስፋ ብርሃን የፈነጠቀ ነበር ይላሉ። የግድቡን ግንባታ ብቻ ሳይሆን ግድቡ የሚገኝበትን ቦታና የአካባቢው ውበት ምን ያህል አስደማሚ ስለመሆኑ በቃላት መግለጽ እንደሚከብድ ይገልጻሉ። ስፍራው ከፍተኛ ሙቀት ያለበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውያን ይህን ሙቀት ተቋቁመው ለአገራቸው እየከፈሉ ያሉት መሰዋዕትነት ትልቅ ዋጋ ያለው መሆኑንም መምህሩ ያስታወሳሉ።

መምህር መለሰ ግድቡን በጎበኙበት ወቅት ግድቡ ገና ጅምር ላይ የነበረ ቢሆንም፣ ለሀገሪቱና ለመጪው ትውልድ ትልቅ ተስፋ ይዞ እየመጣ መሆኑን በሚገባ ተገንዝበዋል። ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን አይችሉም ሲሉን እንደምንችል ያሳየንበት፣ የማንነታችን አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ነው›› በማለት የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል።

ግድቡን ከጎበኙ በሁዋላም ግድቡ ስለደረሰባቸው የተለያዩ ምእራፎች አፈጻጸምና ለውጥ በሚዲያ መረጃውን ሲከታተሉ መቆየታቸውን ተናግረው፣ በተለይ ከለውጡ በኋላ የተደረጉ ማስተካከያዎች ተከትሎ በርካታ ትላልቅ ተግባሮች መከናወናቸውን እንደሚያውቁ ያመላክታሉ።

የግድቡ የውሃ ሙሌት በተለያዩ ዙሮች መካሄዱ፣ ግንባታው ሃያ አራት ሰዓት እየተካሄደ አሁን ትልቅ ደረጃ ላይ መድረሱ፣ ግንባታው በቅርቡ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት ዝግጁ እንደሚሆን ማሳያ እንደሆኑ ይገልጻሉ።

‹‹ የግድቡ ግንባታ አፈጻጸም 95 በመቶ ያህሉ ተጠናቅቆ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ መድረሱን በሚዲያ ስከታተል መጀመሪያ ግንባታውን ስጎበኝ ከተሰማኝ ደስታ የበለጠ ተሰምቶኛል። ያኔ የተመለከትኩት እዚህ ደርሶ ማየት መቻሌ ተስፋዬ ይበልጥ እንዲለመልም፤ ስለመጪው ዘመን ብሩህ ጊዜ እንዳይ አስችሎኛል›› ሲሉ አብራርተዋል።

የግድቡ ግንባታ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ እያንዳንዱ ዜጋ ድጋፍ ሲያደርግ እንደነበረው በትምህርት ቤቶች ተማሪዎች፣ መምህራንና ሁሉም የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በሚችለው አቅም ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው፣ መምህራን በተለያዩ ዙሮች ከአራት ጊዜያት በላይ ቦንድ በመግዛት የራሳቸው አስተዋጽኦ ማድጋቸውን አመልክተዋል፤ በእሳቸው በኩል ግንባታው እስኪጠናቀቅ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ይናገራሉ።

‹‹ግድቡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ ሆነ በማህበራዊ ጉዳዮቻችን ላይ ትልቅ ለውጦችን ያመጣል ብዬ አስባለሁ›› ያሉት መምህር መለሰ፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ‹‹ የአገራችን እድገት ማስፈንጠሪያ ሊሆን የሚችል፣ ከእኛ አልፎ ለጎረቤት አገር የሚተርፍ ትልቅ ፕሮጀክት ነው።›› ሲሉም አስታውቀዋል። አገራችን ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ጭምር ተቋቁማ የገነባችው ግድብ በመሆኑ ግንባታው ተጠናቅቆ ለማየት በጉጉት እየጠበቅን ነው›› ብለዋል።

‹‹ ኢትዮጵያውያን በተባባረ ክንድ የገነቡት፣ የእያንዳንዱ ዜጋ አሻራ ያረፈበት ግድብ እንደመሆኑ ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ሁሉ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ እስከሚጠናቀቅ የበኩላችን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅብናል›› ያሉት መምህሩ ግድቡን እንደ አይናችን ብሌን እየጠበቅን ለትውልድ ማስተላለፍ ይገባናል ሲሉም አስገንዝበዋል።

ጋዜጠኛ ጸጋዬ ጥላሁን ግድቡን ከጎበኙት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች አንዱ ነው። ጋዜጠኛው በ2011 ዓ.ም ግድቡን በጎበኘበት ወቅት የግንባታው አፈጻጸም 67 በመቶ አካባቢ ደርሶ እንደነበር ያስታውሳል።

በወቅቱ ግድቡ የሚገነባበት ጉባ ደርሶ የግንባታውን ሂደት እንደተመለከተ፤ ‹‹ይህ ፕሮጀክት እውን ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለችው ነው? እኛ እየሰራነው ነው? ይህን ያህል አቅምስ አለን? ›› የሚል ጥያቄ አዘል ግርምት ተጭሮበታል። በተለይ የኮርቻ ግድብ እና ሌሎችም ትላልቅ ቦታዎችን መጎብኘቱ የግድቡን ትልቅነት ይበልጥ ገዝፎ እንዲመለከት እንዳደረገው ተናግሯል።

ጋዜጠኛው ሌላው ግርምት የፈጠረበት የግድቡ ሠራተኞች ተነሳሽነት መሆኑን ጠቅሶ፣ አድናቆቱን ችሯቸዋል። ‹‹እዚያ በረሃ ውስጥ ሆነው ሙቀትና ሀሩሩን ተቋቁመው የግድቡን ሥራ የሚሰሩ ሠራተኞች ስመለከት ምን ያህል የሀገር ፍቅር እንዳላቸው ተረድቻለሁ ይላል። ለሀገር እድገትና ብልጽግና ብለው የሚከፍሉትን መስዋዕትነት እንዲመለከትም አስችሎታል።

ፕሮጀክቱን ሲመለከት ‹‹ኢትዮጵያ ይህን ያህል ፕሮጀክት የመገንባት አቅም አላት ወይ የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ ያደረገው ቢሆንም፣ በየጊዜው እየተሰራ ያለው ሥራ መቻሏን አሳይቷል›› ሲል ጋዜጠኛ ጸጋዬ ተናግሯል። አሁን የግድቡ ግንባታ 95 በመቶ መድረሱን ሲሰማ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማው ጠቅሶ፣ ‹‹በሕይወቴ እንደዚህ አይነት ሰፊ ቦታ ያያዘ ትልቅ ፕሮጀክት፣ ሃያ አራት ሰዓት ሥራ የሚሰራበት ፕሮጀክት አይቼ አላውቅም›› ሲል የተሰማውን ገልጧል። ‹‹እውነቱን ለመናገር እንደዚያን ጊዜ ተደስቼ አላውቅም ፤ ልዩ ስሜት ነው የተሰማኝ።›› ሲልም አብራርቶ፣ ሁኔታው በድጋሚ ግድቡን ለመጎብኘት ከፍተኛ ጉጉት እንዲያድርበት እንዳደረገውም አስታውቋል።

‹‹ግድቡ ትልቅ ፕሮጀክት ነው፤ ኢትዮጵያውያን እድለኞችን ነን፤ ወንዙና ግድቡ የሚሰራበት ስፍራ ፈጣሪ በተፈጥሮ ምን ያህል ሀብት እንደሰጠን ማየት የሚቻልበት ነው። መስማማትና መግባባት ቢኖር ምንያህል ማደግ እንደሚቻልና ሀብት እንዳለን ያየሁበት ነው። የግድቡ ግንባታ ለኛ ኢትዮጵያውያን ልዩ ፕሮጀክታችን መሆኑን አይቼበታለሁ›› ሲልም አብራርቷል። ላለፉት አምስት ዓመታት በተከታታይ ቦንድ መግዛቱን ያነሳው ጋዜጠኛው አሁን የግድቡ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ እንደመሆኑ እሱ በሚችለው አቅም የበኩሉን ድጋፍ ማድረጉን እንደሚቀጥል አረጋግጧል።

ጋዜጠኛው እንዳስታወቀው፤ የሚዲያ ባለሙያዎች በሚችሉት አቅም ስለግድቡ ግንባታ ሕዝቡን በማሳወቅ፣ በማስተማር እና ግንዛቤ በማስጨበጥ እያንዳንዱ ዜጋ ግንባታው እስከሚጠናቀቅ ድረስ የራሱን አስተዋጽኦ ማድረጉን አጠናክሮ እንዲቀጥል መስራት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ፕሮጀክት ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ላይ እየተሰሩ ላሉ ሌሎችም ፕሮጀክቶች እንደ ሚዲያ ባለሙያ መስራት አለባቸው። ሕዝቡም በሚችለው አቅም ፕሮጀክቱን ከጅምር አንስቶ በአንድነትና በትብብር እንደሰራ ሁሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ድጋፍ በማድረግ እና ሌሎች ፕሮጀክቶች እንዲሰሩ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት የሚዲያ ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም፤ የግድቡ ግንባታ ከ95 በመቶ ላይ መድረሱ ምን ያህል ትልቅ ዋጋ እንዳለው የምናውቀው መነሻውን ስንመለከት ነው ይላሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት ጀምሮ አባይን ለመገደብ ሃሳብ ያልነበረው መሪ የለም። ሲሉም ጠቅሰው፣ ግደቡን ለመገንባት ያልተቻለበት ዋንኛ ምክንያት በውጭ ሴራና በውስጥ ሽኩቻ የተነሳ ነው። ያም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ ተቋቁማ ግድቡን በመገንባት የግድቡን ግንባታ 95 በመቶ ማድረስ ተችሏል ብለዋል።

የግድቡ ግንባታ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ በርካታ ዜጎች ግድቡን ስፍራው ላይ ተገኝተው መጎብኘታቸውን የጠቀሱት አቶ ኃይሉ፤ ከየመስሪያ ቤቱ፣ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ ወዘተ. የተወጣጡ እያሌ ሰዎች ግድቡን መጎብኘታቸውንም ይገልጻሉ። እስካሁንም ከ300ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን፣ ከ400 በላይ ሚዲያዎች እና የተለያዩ ዲፕሎማቶች እና የአገራት ልዑካን (የሳውዲ፣ ኳታር እና የመሳሳሉት) ቡድኖች ግድቡን ጎብኝተውታል። የቀድሞው የሱዳን ፕሬዚዳንት ኦማር አልበሽርን ጨምሮ የሱዳንና የግብጽ ጋዜጠኞች ግድቡን መጎብኘታቸውን አስታውቀዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአገሪቷ የጸጥታ ሁኔታ እንደ ፊቱ በየብስ ትራንስፖርት ግዱብን ሄዶ ለመጎብኘት አስቸጋሪ ሆኖ መቆየቱን ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግድቡ እየተጎበኘ ያለው በአውሮፕላን በመሄድ መሆኑን ተናግረዋል። በአሁኑ ወቅት ግድቡን እየጎበኙ የሚጎበኙት በውጭ አገር ሆነው ስለግድቡ ሲወራ ይሰሙ የነበሩ የዲያስፖራዎች መሆናቸውን ገልጸዋል። እሳቸው እንደሚሉት፤ ዲያስፖራዎች እስካሁን ለግድቡ ድጋፍ ለማድረግ ድንበርና ርቀት ሳይገድባቸው ካሉበት ሆነው በቻሉት አቅም ሲደግፉ ኖረዋል። ለግድቡ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርገዋል። ከዚህ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስለግድቡ በመከራከር፣ በዓለም አደባባይ ድምጻቸውን በማሰማት እና በተለያዩ ጊዜያት ሰላማዊ ሰልፎች በማድረግ ከአገራቸው ጎን በመቆም ለግድቡ ድጋፍ ሲያደርጉ ቆይተዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በመላ ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች በቡድን በመደራጀት በዘመናዊው የሚዲያ አማራጭ በኦንላይን በመጠቀም፣ የተለያዩ ጆርናሎችን በመጻፍ፣ በተለይ በአረብ ሚዲያ እየተጠቀሙ በግድቡ ላይ ያላቸውን አዎንታዊ አቋም በመግለጽ ትልቅ ሥራ እየሰሩ ናቸው። ከዚህ አልፎ የአረቡን ዓለም ለማንቃት ኢትዮጵያውያኑ ብቻ ሳይሆኑ የሌሎች አገራት (የሱዳን፣ የአልጀሪያ---) ጋዜጠኞች ጭምር ሲሳተፉ ቆይተዋል። እነዚህ ዲያስፖራዎች ትልቅ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ እየሰሩ ናቸው።

እንደዚህ አይነት ሥራ የሚሰሩ ዲያስፖራዎች ወደ አገራቸው ሲመጡ ደግሞ ግድቡን ለመጎብኘት እንዲችሉ የጉብኝት ፕሮግራም ይመቻችላቸዋል ያሉት አቶ ሀይሉ፤ በ2016 ዓመት ብቻ ዲያስፖራዎች በሦስት ዙር ግድቡን መጎብኘታቸውን አስታውቀዋል። ማስተባባሪያ ጽሕፈት ቤቱ ለጎብኙቱ የሚሆን በጀት እንደሌለው ተናግረው፣ ዲያስፖራዎች በቡድን ሆነው በራሳቸው በጀት ቻርተር አውሮፕላን ተከራይተው ግድቡ ድረስ በመሄድ ጎብኝተው እንደሚመለሱ አስታውቀዋል።

ዲያስፖራዎች ለጉብኝት መልስ ያላቸው ስሜት ለየት ያለ እንደሆነም ጠቅሰው፣ ግድቡን ሲመለከቱ በጣም የተለየ ስሜት እንደሚፈጥርባቸው ይናገራሉ። ዲያስፖራዎቹ ተጨማሪ ቦንዶች በመግዛት ድጋፍ እንደሚያደርጉ ጠቅሰው፣ ግድቡን እየገነቡ ላሉ ዜጎች ጭምር ድጋፍ እንደሚያደርጉም ነው የተናገሩት። ወደመጡበት ሀገር ሲመለሱም የሀገሪቱን /የግድቡ/ አምባሳደር በመሆን ዲያስፖራው ቦንድ እንዲገዛ በመቀስቀስ እንደሚሳተፉ ያስረዳሉ።

ማስተባባሪያ ጽሕፈት ቤቱ፤ ሕዝቡ ግድቡን እንዲጎብኝ ለማስቻል ሁለት ነገሮች ታሳቢ ያደረገ ሥራ ሲሰራ መቆየቱን ያስታወቁት አቶ ኃይሉ፤ የመጀመሪያው ሕዝቡ ግድቡ ድረስ ሄዶ መገብኘት እንዲችል ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ግድቡን በምስል ማሳየት የሚችል የሕዳሴ ግድብ ፓርክ መሥራት ነው። ፓርኩን በአዲስ አበባ ከተማ ዓለም ባንክ አካባቢ ለመገንባት የሚያስችል ዲዛይን ተሰርቶ ለአዲስ አበባ ከተማ ጽዳትና ውበት ጽሕፈት ቤት መስጠቱን ጠቁመው፤ የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳትና ውበት ጽሕፈት ቤት ሥራውን ተግባራዊ ሳያደርግ ይዞ መቆየቱን ይገልጻሉ።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ ማስተባባሪያ ጽሕፈት ቤቱ እስካሁን ካሉት ፓርኮች የተለየ ትልቅና ዘመናዊ የሆነ የውሃ ፓርክ ለመስራት ያለመ ሥራ በሙሉ ጨርሶ ለአዲስ አበባ ጽዳትና ውበት ጽሕፈት ቤት የሰጠው ትልቅ የውሃ ፓርክ እንዲሰራ በማሰብ ነው። የፓርኩ ዲዛይን የሚገርም በመሆኑ የግድቡን ሞዴል በሚገባ ሊያሳይ እንዲችል ተደርጎ የተሰራ ነው። ይህ እንዲሆን የተደረገበት ዋንኛ ምክንያት በተለይ ግድቡ ድረስ መሄድ ለማይችሉ ሰዎች የግድቡን ሞዴል በማየት ግድቡ አጠቃላይ ገጽታ ይህንን ይመስላል የሚል እይታ እንዲኖራቸው ለማድረግ በማሰብ ነው። ለግድቡ ደህንነት ጥንቃቄ ሲባልና ግንባታውም በማጠናቀቂያ ምእራፍ ያለ በመሆኑ ሰዎች በየብስ ትራንስፖርት ግድቡ ድረስ ሄደው እንዲጎበኙ ለማድረግ አሁን የሚቻልበት ሁኔታ አለመኖሩን ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

‹‹ወደፊት የአባይ ግድብ ለአገሪቱ ገቢ የሚያስገኝ የቱሪዝም መስህብ እንደሚሆን እናምናለን›› አቶ ኃይሉ፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ ከ78 በላይ ደሴቶችና ሪዞርቶች እንደሚኖሩትና አሳ የሚመረትበት መሆኑን ጠቅሰው ግድቡ ሲጠናቀቅ ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩትም ጠቁመዋል።



# የመንግሥታት መቀያየር ያላነቀፈው የሕዝብ ራዕይ

**ዳግም ከበደ**

የዛሬ 13 ዓመት መጋቢት 24 የመሰረት ድንጋዩ ተጥሎ የተጀመረው የዓባይ ግድብ 95 በመቶ ያህሉ ግንባታ መጠናቀቁን ይፋ ተደርጓል። የመላው ኢትዮጵያውያን የዘመናት ሕልም የሆነው ግድብ በመጨረሻም መሬት ነክቶ ወደ መጠናቀቂያ ምእራፍ ላይ ደርሷል። በፕሮጀክቱ ላይ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ ከደሃ እስከ ሀብታም ሁሉም የድርሻውን ተወጥቷል፤ ዛሬም ይህ ጥረት አልቆመም።

ከጥንታዊት እስከ ዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አታካችና አድካሚ ታሪካዊ ሂደት ታልፎ በግድቡ እውን መሆን ዜጎች የሚኮሩበት ትውልድም አንገቱን ቀና የሚያደርግበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። «የአባይ ግድብ ውሃ ለብቻችን ይገባናል» በሚል ትምክህት ለዘመናት የጎነጎኑት ሴራ ያልበገረው የኢትዮጵያውያን ትግል ፍሬ አፍርቶ ወደ ይቻላል ልእልና እየተንደረደረ ነው። እዚህ ለመድረስ ግን የመጣነው ርቀት በእጅጉ ረጅም ነበር።

ነገስታት በአባይ ውሃ ጉዳይ ከጠላት ጋር ተናንቀዋል፤ አድካሚ ዲፕሎማሲያዊ ንትርክ ውስጥ ገብተዋል። መሪዎች ካለፉት ስርዓቶች የተቀበሉትን አደራ መሬት ለማውረድ ብዙ ኳትነዋል። በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳይ ልዩነት የነበረ ቢሆንም፣ በዓባይ ጉዳይ ግን አንድ አይነት ራዕይ ከመያዝ የገደበ አልነበረም። ይህ ቅብብሎሽ ማብቂያው 2003 ዓ.ም ሆኖ ግድቡን ገንብቶ የኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨትም በላይ የሆነው የኢትዮጵያውያን በድህነት ላይ የመዝመት «ሀሁ» መሬት ሊነካ ችሏል።

በግንባታ ሂደቱ አያሌ እሰጣ ገባና ዲፕሎማሲያዊ ግብግቦችም ላለፉት 13 ዓመታት ተደርገዋል፤ አሁን ላይ የአሸናፊነት ድምዳሜው ማብሰር የሚቻልበት ምእራፍ ላይ ተደርሷል።

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ለግድቡ ግንባታ እውን መሆን ሕዝብ የከፈለው መስዋዕትነት ታላቅ ነው። የዜጎችን ጥቅም ለማስጠበቅና የኢትዮጵያን ሉዕላዊ የመልማት መብት እውን ለማድረግ ደግሞ ለዘመናት አገሪቱን ያስተዳደሩ መሪዎችና መንግሥታት ጉልህ አስተዋፆኦ አበርክተዋል።

ዛሬ የአባይ ግድብ ግንባታ የተጀመረበት 13ተኛ ዓመት በመላ ኢትዮጵያ ይከበራል፡፡ በአሉ ዘንድሮ የሚከበረው ግንባታው በማጠናቀቂያ ምእራፍ ላይ ሆኖ ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችን የግድቡ ግንባታ መሰረተ ልማት የተጣለበትን ይህን 13ተኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ምእተ ዓመትን ወደ ኋላ ዘልቆ፤ ወደፊት ደግሞ በርካታ አስርት ዓመታትን ተንደርድሮ «የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ መንግሥታትና መሪዎች» ለአባይ ግድብ ግንባታ ያበረከቱትን አስተዋፆኦና ተጋድሎ እናወሳለን።

አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ኢትዮጵያን ዘለግ ላሉ ዓመታት በዓለም አቀፍ መድረክ በዲፕሎማትነት አገልግለዋል። ኢኮኖሚስትም ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ አገሪቱን ያስተዳደሩ መሪዎች በአባይ ውሃ ዙሪያ ብሄራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ሚናን ተወጥተዋል። ወደ ኋላ መለስ ብለውም ንጉሰ ነገስት ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የድንበር ጉዳይን አስመልክቶ ያደረጉት ስምምነት፤ የአባይን ውሃ በተመለከተ የደረሱት ውሳኔም አንዱ ማሳያ መሆኑን ያስታውሳሉ።

በወቅቱ የእንግሊዝ መንግሥት ጫና የኢትዮጵያን ከአባይ ውሃ የመጠቀም መብት የሚነፍግ ስምምነት ለማድረግ ቢሞከርም አፄ ሚኒሊክ ግን ለድርጊቱ እንዳልተበገሩ የሚገልፁት አምባሳደሩ፤ ግብፅን ጨምሮ በርካቶች ጉዳዩን በጥልቀት ሳይመረምሩ ወቀሳ ሲሰነዝሩ ይደመጣል ይላሉ። ነገር ግን ንጉሱ በጊዜው የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ የማይሰጥ ከዓለም አቀፍ ሕግም ጋር የማይጣረስ ስምምነት ማድረጋቸውን ይናገራሉ።

ውሃውን ጨርሶ ላለማቆም ስምምነት ላይ ቢደርሱም ኢትዮጵያ ከአባይ ተጠቃሚ እንዳትሆን የሚደነግግ ፊርማ አለማኖራቸውን ያስረዳሉ። ይህ ውሳኔ የሚኒሊክን ብልህነትና የሚያሳይ ከመሆኑም ባሻገር ግድቡም በእርሳቸው የአስተዳደር ዘመን ባይገነባ እንኳን መጪው ትውልድ እንዲሰራው መንገድ የጠረገ ነው ሲሉ ይገልፃሉ።

የአባይ ግድብ ሲነሳ በአስተዳደር ዘመናቸው ለትውልዱ መነሳሳት ታላቅ ራዕይን ያሻገሩት ሌላኛው መሪ አፄ ኃይለስላሴ መሆናቸውን አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ጠቅሰዋል። ንጉሱ በአስተዳደር ዘመናቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከቀደሙት ነገስታት የተቀበሉትን አደራ ለማስጠበቅ የሚያስመሰግን ስራ መስራታቸውን ይገልፃሉ። በተለይ በእርሳቸው የንግስና ዘመን ግብፅ የአስዋን ግድብን መስራት ስትጀምር ሊግ ኦፍ ኔሽንን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች፣ በሁለትዮሽ ግንኙነት ወቅት ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማድረጋቸውን ይናገራሉ። የግብፅ ድርጊትም የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ መሆኑን በመግለፅም «ኢትዮጵያ አልፈቀደችም፣ ጥቅማችንንም በግልፅ ይነካል» በማለት ተቃውሞ ያሰሙ እንደ ነበር ይገልፃሉ።

አፄ ኃይለስላሴ የግብፅን ድርጊት በይፋ ከመቃወም ባሻገር ኢትዮጵያ የአባይን ውሃ ለመጠቀም የሚያስችላት የግድብ ግንባታ እንድታከናውን ጥረት ማድረጋቸውን የሚናገሩት አምባሳደሩ፤ በጊዜው የገንዘብና የፖለቲካው ሁኔታ ምቹ ስላልሆነላቸው ጥረታቸው ሳይሳካ ቢቀርም ዲዛይን እስከማሰራት የደረሰ ሙከራ ማድረጋቸውን ይናገራሉ። ይህም ንጉሱ እንደ ቀደምት መሪዎች ኢትዮጵያ የአባይ ውሃ ተጠቃሚ እንድትሆን ራዕይ እንደነበራቸው የሚያሳይ እርምጃ መሆኑን ያስረዳሉ። «እኛ ባንሰራው መጪው ትውልድ ጊዜው ሲፈቅድ እውን ያደርገዋል» በማለት ለመጪው ትውልድ አደራ ማስቀመጣቸው የሚያስመሰግናቸው መሆኑን ይገልፃሉ።

«ኢትዮጵያ ለዘመናት ከጉያዋ የሚፈሰውን የአባይ ወንዝ ገድባ ተጠቃሚ እንድትሆን ከጥንት ጀምሮም የሕዝቡ ፍላጎት ነበር። መሪዎችም ይህንን ራዕይ ለማስፈፀም ይጥሩ ነበር» የሚሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ አፄ ኃይለስላሴ ከመንበረ ስልጣናቸው ወርደው የደርግ መንግሥት በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ሲሞክር የዓባይ ወንዝን ለመገደብና ለማልማት ብርቱ ጥረት ያደርግ እንደነበር ይገልፃሉ። መንግሥታት ቢቀያየሩም በአባይ ጉዳይ ግን አንድ አይነት አቋም በመያዛቸው ምክንያት ዘመናት ሲቀያየሩ ከአባይ ወንዝ የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብትን ለማስከበር የሚደረገው ጥረት በዚያው ልክ እየጠነከረ መምጣቱን ያስረዳሉ።

የደርግ መንግሥት በአባይ ጉዳይ ላይ የነበረው አቋም ከአፄ ኃይለስላሴም የጠነከረ እንደነበር የሚናገሩት አምባሳደር ጥሩነህ፤ በሚከተለው ርዕዮተ ዓለም ምክንያት ግን የምእራባውያኑን ድጋፍ ማግኘት እንዳልቻለ ይገልፃሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ የደርግ መንግሥት ፍላጎትና እቅዱን መሬት ላይ ለማውረድ እንቅፋት አልተፈጠረበትም። በዚህ ምክንያት ከጣሊያን መንግሥትና ከሳሊኒ ኮንስትራክሽን ጋር በመተባበር ለኢንዱስትሪ፣ ለእርሻ ለመሰል የልማት ስራዎች የአባይ ውሃን ለመጠቀም የተግባር ስራዎችን ጀምሮም ነበር።

ከሕዝቡና ከቀደሙት መንግሥታት የተጋራው ከአባይ ውሃ የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብትና ራዕይ መሬት ለመንካት ጫፍ ላይ ደርሶ እንደነበር ያስረዳሉ። በዚህ ድርጊት የተበሳጩት ግብፆች የጣሊያን መንግሥት ለኢትዮጵያ ብድር እንዳይሰጥ በሴራ አስከልክለው የነበረ ቢሆንም ደርግ ግን ውጥኑን መሬት ለማስነካት ጥረት ማድረጉን ቀጥሎ እንደነበር ያስታውሳሉ። የመንግሥት ለውጥ በመምጣቱና በፕሮጀክቱ ለመቀጠል ፍላጎት በመጥፋቱ ምክንያት በጊዜው እውን ሳይሆን መቅረቱን ያስረዳሉ።

ኢሕአዴግ የሚያስተዳድረውን መንግሥት ይመሩ የነበሩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘመናት ራዕይ የነበረውን የአባይን ወንዝ የመገደብ ጥልቅ ፍላጎት በድፍረት እውን የሚያደርግ መሰረተ ድንጋይ በመጣል ታሪክ ሰርተዋል የሚሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ ወቅትን ያገናዘበ ብልህነት፣ ድፍረትና የአመራር ጥበብ በአባይ ግድብ ዙሪያ መውሰዳቸው ሊያስመሰግናቸው እንደሚገባ ይናገራሉ።

ከአንድ መሪ የሕዝብን ፍላጎት አገናዝቦ ተገቢውን ጊዜና አጋጣሚ ጠብቆ መሰል ውሳኔ ላይ መድረስ የሚጠበቅ ነው የሚሉት አምባሳደሩ፣ ያ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ይጠብቁት የነበረው ጊዜ እንደነበር ይናገራሉ። የሕዝብን ምኞትና ሕልም እውን ያደረገና መሬት የወረደ እርምጃ እንደሆነም ይገልፃሉ። በዚህ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሊመሰገኑ እንደሚገባቸው ደግመው ይገልፃሉ። ይህ ውሳኔያቸውም የአባይ ግድብ የህዝብ ራዕይ እንደሆነ የታየበት፣ የቀደሙት መንግሥታትንም ጥረት መሬት ያወረዱበት አጋጣሚን የፈጠረላቸው መሆኑን አስታውቀዋል። በጥቅሉ የመንግሥታት መለዋወጥ የመላው ኢትዮጵያውያንን ፍላጎት የሆነው ራዕይ ላይ እንቅፋት እንዳልፈጠረ ያስረዳሉ።



አምባሳደር ጥሩነህ ዜና

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአባይ ግድብ ከመገንባት ባሻገር የናይል ተፋሰስ አገራት በፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የጋራ አቋም እንዲይዙ፣ ኢትዮጵያም ተፈጥሯዊ መብቷን እንድትጠቀም፣ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡም የኢትዮጵያን የመልማት ፍላጎት እንዲረዳ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማድረጋቸውን አምባሳደሩ አመልክተዋል፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕልፈት በኋላም ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን የያዙት አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በሶስትዮሽ ድርድርና ዲፕሎማሲያዊ ጥረት የግድቡ ግንባታ ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ማድረጋቸውን አምባሳደር ጥሩነህ መናገራቸውን አስታውቀዋል። በተለይ በሱዳን በተደረገው ድርድር ላይ «ኢትዮጵያ ግንባታውን እያካሄደች ስምምነት ላይ ትደርሳለች» የሚለው ሃረግ፣ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅም መጠበቅ ወሳኝ እንደነበር ይገልፃሉ።

የመንግሥታቱ ተመሳሳይ አቋምና ቁርጠኝነት የተሞላበት ትግል የግንባታው ሂደት ፈተናዎችን እየተሻገረ ወደ ውጤት እንዲደርስ ያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ትልቅ እውቅናና ምስጋና ሊቸረው እንደሚገባ ይገልፃሉ።

የአባይ ግድብ ጥቅል አፈፃፀም 95 በመቶ አልፏል። አራት ጊዜያትም የውሃ ሙሌት ተከናውኖ ከ42 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ውሃ በላይ ይዟል። ሁለት ተርባይነሮችም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ጀምረዋል። ይህን ኃይል የማመንጨት ስራ በያዝነው ዓመት ወደ አምስት ተርባይነሮች ለማሳደግና ኃይል ማመንጨት እንዲጀምር ስራዎች እንደሚሰሩ መንግሥት አሳውቋል። ይህንን ሂደት አስመልክቶ አምባሳደሩ በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት በግድቡ ግንባታ መፋጠንና ዳር መድረስ ላይ ያለውን ሚና እንደሚከተለው ገልጸውታል።


ኢሕአዴግ በለውጡ መንግሥት ብልፅግና ሲተካ የአባይ ግድብ ግንባታን ለማስቀጠልና በርካታ ማስተካከያዎች ለማድረግ ተገድዶ ነበር ሲሉ ጠቅሰው፤ በተለይ የኢትዮጵያን ውስጣዊ የፖለቲካ ቀውስ እንደ ልዩ አጋጣሚ ተጠቅመው ግንባታውን ለማስተጓጎል ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩትን ግብፅና መሰል ኃይሎች ሕልም የተቀጨበት ዲፕሎማሲያዊ ድል መመዝገቡን ይናገራሉ።

የልእለ ሃያሏ አገር አሜሪካ መሪ ሆነው የመጡት ዶናልድ ትራምፕ እና አስተዳደራቸው ኢትዮጵያ እየገነባች ያለችውን የአባይ ግድብ ግንባታ ለማስተጓጎል ግልፅ ጫና በማድረግ ለግብፅ ወግነው እንደነበረም አስታውሰው፣ በተለያየ ጊዜ በነበረው የሶስትዮሽ ድርድር ሂደት ላይ ዲፕሎማሲያዊ ብልጠት የተሞላባቸው ውሳኔዎች በኢትዮጵያውያን ተደራዳሪዎችና በመሪዋ በመወሰዱ ሴራው ሊከሸፍ መቻሉን አምባሳደር ጥሩነህ ያስረዳሉ።

« ያ ወቅት ግብፆች ‹የግንባታ ሂደቱን ማስተጓጎል የምንችለው አሁን ነው› በማለት ተደራጅተው የመጡበት ጊዜ ነበር» የሚሉት አምባሳደሩ፤ የአሜሪካ መንግሥትም የአረብ አገራትን ከእስራኤል ጋር ለማስማማት ያደርግ በነበረው ጥረት ግብፅን ለመጠቀም በማሰቡ ኢትዮጵያን የመስዋዕትነት በግ በማድረግ በጋራ የተነሱበት እንደነበር ያነሳሉ።

የለውጡ መንግሥት ባልተረጋጋበት፣ ኢኮኖሚውም ፈተና ውስጥ ገብቶ በነበረበት ወቅት ይህን መሰል ጫና መምጣቱ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ስጋት የደቀነበት እንደነበርም አስታውሰው፣ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ተዳክማና ኢኮኖሚዋ ደቅቆ የነበረ ቢሆንም ወኔው፣ ጥንካሬውና አንድነቱ በመኖሩ ምክንያት መንግሥት የትራምፕ አስተዳደርን ግፊት ተቋቁሞ ሕዝቡን ዳግም ለአንድ ዓላማ በማሰለፍ፣ ሀብት በማፍሰስ አሁን የደረሰበት 95 በመቶ የግንባታ አፈፃፀም ላይ አድርሶታል ብለዋል። ይህ የሚያሳየው የሕዝብ ራዕይን ሁሉም መንግሥታትና መሪዎች ተፈፃሚ ለማድረግ ያሳዩት ቁርጠኝነትን መሆኑን አመልክተው፣ በዚህም ምስጋና ሊቸራቸው እንደሚገባ ይገልፃሉ።

የአባይ ግድብ ዛሬ ለደረሰበት አፈፃፀም እንዲበቃ የሕዝቡ ራዕይ እና ለዘመናት የዘለቀ ቁጭት ምክንያት መሆኑን አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ይገልፃሉ። «አባይ የኔ ነው። የተፈጥሮ መብቴን መጠቀም አለብኝ» የሚል ተነሳሽነት በየዘመናቱ በሕዝቡ ውስጥ ማደሩም ከነገስታቱ ጀምሮ ያሉ አስተዳዳሪዎች ራዕይን እንዲጋሩና ማስቻሉን ይጠቁማሉ። የማድረግ አቅምን ገንብቶና ምቹ ወቅትን ጠብቆ ራዕዩ እንዲሳካ ለማስቻል መሪዎች የተጠቀሙት የአመራር ሰጪነት ጥበብም ሊደነቅ ይገባል ይላሉ። በዚህ ቅብብሎች የአባይ ግድብ ሊጠናቀቅ የመጨረሻው ምእራፍ ላይ መድረሱ የመላው ኢትዮጵያውያን ድል ነው ብለዋል።



# ዓባይ የሁሉም ምንጭ

ዋሰልኝ አየለ

«ዓባይ የግብጽ ሕይወት ነው» የሚለው የግብጽ ትርክት ዓለም አቀፍ ሆኗል። ይህ ቃል ግን በምሁራኖቻቸው ተቀርጾ በፕሮፖጋንዳቸው ዝነኛ የሆነ ነው። ለመሆኑ ዓባይ ለኢትዮጵያ ምንድነው?

ዓባይ ለኢትዮጵያ ሁሉንም ነገር ነው። የሁሉም ነገር ምንጭ ነው። ይህ የሆነው በትርክት ሳይሆን በተፈጥሮ እና በሕዝብ ነው። ዓባይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ጋር የተቆራኘ መሆኑን የሚያረጋግጠው በሕይወት እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ ሁሉ ያለ መሆኑ ነው። የሰው ልጅ መሠረታዊ ነገር ውሃ ቢሆንም፤ ዓባይ ግን ከውሃነትም ባሻገር ነው። ዓባይ ቋንቋ ነው። ዓባይ ባህል ነው። ዓባይ ትውፊት ነው። ዓባይ ሥነ ልቦና ነው። ዓባይ ታሪክ ነው።

ዓባይ ቋንቋ ነው ሲባል፤ ግዝፈትን፣ ኃይለኛነትን፣ ለጋስነትን... ለመግለጽ ያገለግላል። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ውስጥ በሴትም በወንድም ዓባይ የሚባሉ ሰዎች አሉ። በተረቶቻችን ውስጥ ግዝፈትን፣ ለጋስነትን፣ ሃይለኘነትን ለመግለጽ በብዛት እንጠቀመዋለን። በአጠቃላይ ዓባይ ኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነትና ምንነት ነው።

ይህን የዓባይን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁጭት ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩን የሕዝብ ሀብት የሆኑት የሥነ ቃል የጥበብ ውጤቶች ናቸው። ዓባይ ለኢትዮጵያ የጥበብ ምንጭ ሆኖ ኖሯል። እነሆ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ሆኖ አሁን የኃይል ምንጭ ሊሆን ነው። የመሠረት ድንጋይ የተጣለበትን 13ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የዓባይን እና የኢትዮጵያን ሕዝብ ቁርኝት እናስታውስ።

የባህል ጥናትና የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ ሥነ ቃል የአንድ ማህበረሰብ ምንነት ነው። ምክንያቱም ሥነ ቃል በመንግሥት ትዕዛዝ ወይም በአንድ ወገን ጫና የሚፈጠር ሳይሆን ማህበረሰባዊ ሥነ ልቦና የሚገለጽበት ነው። ሕዝብ ብሶቱንና ደስታውን የሚገልጽበት ነው። እነዚህ የስሜት መግለጫ የሆኑ የሥነ ቃል ሀብቶች ደግሞ የሚፈጠሩት ከሚታየው ነባራዊ ሁኔታ ነው። ለዚህም ነው የአንድ ማህበረሰብ ታሪካዊ ታሪክ ሲጠና ትውፊቱ መነሻ የሚሆነው።

እንግዲህ ዓባይ የኢትዮጵያውያን ማንነትና ምንነት ባይሆን ኖሮ ሥነ ቃሎቻችን እንዲህ በዓባይ አይጥለቀለቁም ነበር ማለት ነው። በተረትና ምሳሌዎቻችን ውስጥ ዓባይ አለ፤ የደስታና የሀዘን እንጉርጉሮዎቻችን ውስጥ ዓባይ አለ፣ በባህል ዘፈኖቻችን ውስጥ ዓባይ አለ፣ በስም አወጣጣችን ውስጥ ዓባይ አለ... ዓባይ በብዙ ነገሮቻችን ውስጥ አለ።

ዓባይ እንዲህ እንደ ዛሬው በቁጥጥራችን ሥር ከመዋሉ በፊት በአስቸጋሪነቱ ተዘምሮለታል። ይሄውም በክረምት ወራት የዓባይ ወዲያ ማዶና የዓባይ ወዲህ ማዶ ሰዎችን ስለማያገናኝ ነው። ያኔ በዘመኑ ድልድይ የሚባል ነገር ስለማይታወቅ በዋና እና በእግር በመሻገር ብቻ ስለነበር ስለአስቸጋሪነቱ ተዘፍኖለታል። አብዛኞቹ ተረትና ምሳሌዎች፣ እንጉርጉሮዎች ግን ስለግዙፍነቱ ነው።

ከተረትና ምሳሌዎቻችን ውስጥ፤ ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል፣ ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል፣ ዓባይ ቢሞላ ተሻገር በሌላ፣ ዓባይ አንተ አየኸኝ ከደረት እኔም አየሁህ ከጉልበት፣ ዓባይና ስንቅ እያደር ይቀላል፣ ዓባይን በጭልፋ፣ የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው፣ የሰው ቤት ዓባዩ... የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። አብዛኞቹ ግዙፍነቱን የሚገልጹ ሲሆኑ አንዳንዶቹም ተጓዥነቱንና አስቸጋሪነቱን የሚገልጹ ናቸው። ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል የሚባለው አንድ ሰው ትንሽ ነገር ሲያደንቅ ነው፤ ከዚህም የበለጠ አለ ለማለት ነው። ለምሳሌ የአንዲት የገጠር ከተማን ሕዝብ ብዛት ለሚያደንቅ ሰው እነ አዲስ አበባን ለመግለጽ «ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል» ሊባል ይችላል። የዓባይ ግዙፍነት ሌሎች ነገሮችን ለመግለጽ እንደ ማንፃፀሪያ ያገለግላል ማለት ነው። ዋና ዓላማችን ተረትና ምሳሌዎቹን ማብራራት ስላልሆነ እንደየዓውዳቸው እንጠቀማቸዋለን።

አሁን ከተረትና ምሳሌዎች (ምሳሌያዊ ንግግሮች) ወደ ቃል ግጥሞች እንሂድ። የቃል ግጥሞች በጣም ብዙ ናቸው። በተለይም በባህል ዘፈኖች ውስጥ ይደጋገማሉ። የባህል ዘፈኖች ሲባል በካሴት ወይም ሲዲ እና ዲ ቪ ዲ የወጡትን ሳይሆን እረኞችና ገበሬዎች የሚዘፍኑትን ለማለት ነው። ዓባይ ኢትዮጵያ ውስጥም ከእረኛ ጀምሮ እንደሚታወቅ የምናውቀውም በእነዚህ የሥነ ቃል ዘፈኖቹ ነው። ለምሳሌ የፍቅር ዘፈኖችን እንይ።

በድሮው ጊዜ ዓባይን መሻገር የሚቻለው በበጋ ወቅት ውሃው በመጠኑም ቢሆን ሲቀንስ ተጠብቆ ነበር። እንደ ዛሬው ድልድይ የለም፣ መኪና የለም። አንድ ከዓባይ ወዲህ ማዶ ያለ ኮበሌ ከዓባይ ወዲያ ማዶ ያለች ጉብል ካፈቀረ መገናኘቱ ከባድ ነበር። የሚገናኙት የበጋ ወቅት ጠብቀው ነው። የፍቅረኛው ናፍቆት ሲጠናበት በማሽላ ይመስላታል። እንዲህም ሲል ያንጎራጉራል።

**ዓባይ ወዲያ ማዶ ማሽላ ዘርቼ**
**ወፎች ጠረጠሩት መሻገሪያ አጥቼ**

«ወፎች« ተብለው የተገለጹት ፍቅረኛውን የሚነኩበትን ሌሎች ወንዶች ነው። በዚህ ቅኔ ለበስ ግጥም ውስጥ ብሶቱን ይገልጻል። ከዓባይ ወዲያ ማዶ አፍቅሬ ማግኘት አልቻልኩም ማለቱ ነው። ባስ ሲልበት ደግሞ እንዲህ በማለት ፈጣሪን ይማጸናል።

**አንቺ ወዲያ ማዶ እኔ ወዲህ ማዶ**
**አንገናኝም ወይ ተራራው ተንዶ?**

ተራራ ተብሎ የተገለጸው የዓባይ ውሃ ነው። የያኔው አፍቃሪ ጸሎት ሰምሮ እነሆ ዛሬ ተራራው ተንዷል። ከዓባይ ወዲህ ማዶ ያለ አፍቃሪ ከዓባይ ወዲያ ማዶ ያለች ፍቅረኛው እንዲህ ህልም አትሆንበትም። ያ የከለከለው ተራራ በዓባይ ድልድይ ተንዷል። በፈለገው ቀን ሄዶ ፍቅረኛውን ማግኘት ይችላል።

የዓባይ ውሃ ክረምቱን ሙሉ እንዲህ ሰውን ያቆራርጥ ነበር። መገናኘት የሚቻለው በበጋ ወቅት ነው። ፍቅሩ ብሶበት የበጋ ወቅት የሚጠባበቀው አፍቃሪ እንዲህ ሲል ተስፋ በቆረጠ አንጀት ይዘፍናል።

**ዓባይ ጉደል ብለው አለኝ በታኅሣሥ**
**የማን ሆድ ይችላል እስከዚያ ድረስ?**

ታኅሣሥ የበጋ ወቅት የመጀመሪያው ወር ነው። ይሄን የበጋ ወቅት መጠበቅ ያልቻለ አፍቃሪ፣ ያለው አማራጭ በዋና መሻገር ነው። በርግጥ ይህ የሚሆነው ደግሞ ዋና ለሚችል ሰው ነው። ዋና የሚችለው ደግሞ እንዲህ ሲል ይዘፍናል።

**እስኪ ልሻገረው ዓባይን በዋና**
**የጎጃም ልጅ ወዶ ምን እንቅልፍ አለና!**

አፍቃሪው የሸዋ ሰው ሊሆን ይችላል። ወደ ጎጃም ለመሻገር ደግሞ በመሃል ዓባይ አለ። በነገራችን ላይ ዓባይ ውሃው ብቻ አልነበረም አስቸጋሪ። ወደ ወንዙ የሚያስገቡ መንገዶች ሁሉ ዳገትና ገደል ናቸው። በዋና እንኳን ለመሻገር ብዙ አስቸጋሪ መንገዶችን በእግሩ ሄዶ ነው። የወንዝ ዳር መንገዶች እንደሌላው ምቹ አይደሉም። ወደ ወንዙ ሲወርድ ቁልቁለት አለ፤ ከተሻገረ በኋላ ደግሞ አቀበት (ዳገት) አለ። ቁልቁል ሲወርድ እሷን ለማግኘት ነውና ይጨንቀዋል (በዚያ ላይ የውሃው ስጋት አለ) ከተሻገረ በኋላ ደግሞ በችኮላ አቀበቱን ይወጣዋል። ይሄኔ እንዲህ እያለ ይዘፍናል።

**ዓባይ ቁልቁለቱን እምባዬ እያነቀኝ**
**ዓባይ አቀበቱን ላብ እያጠመቀኝ**
**መቅረትስ አልቀርም**
**እስከዚያው ጨነቀኝ።**

የዓባይ ውሃ መሙላት አንዳንዴ ደግሞ ጥሩ አጋጣሚም ይፈጥራል። ይህ የሚሆነው ከዓባይ ወዲያ ማዶ ያለችዋ ተፈቃሪ አፍቃሪዋ ጋ ወዲህ ማዶ እንደመጣች ውሃው ከሞላ ነው። ምክንያቱም አትሄድም። ይህን አጋጣሚ ሲያገኝ

**ዓባይ ሞላ አሉ ሞላ አሉ**
**እንደ ዕድሌ ሁሉ**

እያለ ይዘፍናል። አንዳንዱ ደግሞ እንዲህ በማለት ቀጭን ትዕዛዝ ይሰጣል።

**ዓባይ ቢሞላ ቢሞላ**
**ዞረሽ ነይ በሌላ!**

በርግጥ እሷን ብቻ ሳይሆን ለራሱም እንዲህ ብሏል።

**ዓባይ ሞላ ብየ ሞላ ብየ**
**አልቀርም ሸግየ**

አንዳንዱ ደግሞ ትንቢት ይገለጥለታል። የዓባይ መሙላት እንዲህ አስቸጋሪ ሆኖ አይቀርም ያለ አፍቃሪ እንዲህ ብሎ ነበር።

**ዓባይም ቢሞላ ቢሞላ**
**አለው አሉ መላ**

የዚህ ትንቢት ፈጣሪ፣ «መላው» ምን እንደሆነ አልነገረንም፤ «አለው አሉ መላ» ብሏል። እነሆ መላው ተገኝቶ ዛሬ የዓባይ መሙላት ፍቅረኞችን መለያየት አልቻለም። ሰውየው የተናገረው ነገር ምናልባትም ድልድይ ሊሰራ እንደሚችል ታይቶት ነበር ብለን እንያዝለት።

የሥነ ቃል ዘፈኖችና ምሳሌያዊ አነጋገሮቻችን ብዙ ጥልቅ ሃሳብ ያላቸው ናቸው። ዓባይ ከኢትዮጵያውያን ጋር ያለውን ባህላዊና ታሪካዊ ትውፊት የሚያሳዩ ናቸው። የዓባይንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥነ ልቦናዊ ትስስር ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው።

ዓባይ የጥንት ኢትዮጵያውያን አበው ብቻ አይደለም። ዓባይ ለዚህ ትውልድም ገናና ማንነት ነው። ይሄ ትውልድም ገናና ዐሻራውን ያሳረፈበት ነው። ይሄ ትውልድም የተጠበበበት ነው። ስለዓባይ ያልዘፈነ የለም፤ ያልተቀኘ የለም፣ ያልገጠመ የለም፣ ያልሳለ የለም፣ ያልተወነ የለም! ዓባይ ለብዙ ከያኒያን የጥበብ ምንጭ ሆኗል። ለዛሬው ዘፋኞችን ብቻ እናያለን። የሁለት ዘፋኞችን ስንኞች መልዕክት እንያቸው።

በ2003 ዓ.ም የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ ሲጣል ከዜናው እኩል ተሰምቷል። ስለሕዳሴው ግድብ ለሚሰሩ ፕሮግራሞች ሁሉ ማጀቢያ ነበር። የድምጻዊት ገነት ማስረሻ «ዓባይ ጭስ አልባው ነዳጅ» የተሰኘው ዘፈን አሁን ድረስ የፕሮግራሞች ማጀቢያ ነው። ከዚያ ወዲህ ስለሕዳሴው ግድብ ብዙዎች ቢዘፍኑም ቀዳሚ በመሆኑ ይመስላል ይደጋገማል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ስንኞቹ ጥልቅ መልዕክት አላቸው። እስኪ ጥቂቶችን እንያቸው።

**አደባልቆት ሲሄድ ጥቁር እና ነጩን**
**ግዮን አበሻ ነው ማን ይነካል ምንጩን!**
**ዓባይ አንተ እያለህ ታላቁ ወንዛችን**
**መሳለቂያ አንሆንም በድህነታችን።**

አዎ! ዓባይን የሚያህል ግዙፍ ሀብት ይዘን መሳለቂያ ሆነናል። ለመዝገበ ቃላት የድህነት ትርጉም መፍቻ ሆነናል። ይሄ ሁሉ ሲሆን ከኢትዮጵያ ተነስቶ የኢትዮጵያን ጋራና ሸንተረር አቆራርጦ፣ የኢትዮጵያን አፈር እያደባለቀ የሚሄድ ነው። «አደባልቆት ሲሄድ ጥቁር እና ነጩን» የሚለውን ቅኔ በየራሳችን መተርጎም ነው።

**ዘመን ቢያስታርቀን ከዓባይ ብንስማማ**
**ይዘን ተጠጋነው አካፋና ዶማ**

ዓባይ ለዘመናት ለቀረርቶና ለፉከራ የግጥም ምንጭ ብቻ ሆኖ ኖሯል። እነሆ 2003 ዓ.ም ላይ ግን ታሪክ ተቀየረ። አካፋና ዶማ ይዘን ተጠጋነው።

**ማደሪያ ሳይኖረው ግንድ ይዞ ይዞራል**
**የሚባለው ተረት ከእንግዲህ ይቀራል**
**እንዲህ እንደ ዛሬው መልካም ቀን ሲመጣ**
**ግንድም ይዘህ አትዞር ማደሪያም አታጣ።**

አዎ! ተረት እውን ሆነ። «ዓባይ ማደሪያ የለውም ግንድ ይዞ ይዞራል» የሚለው ተረትና ምሳሌ ራሱ ተረት ሆነ። ዓባይ ማደሪያ አገኘ፤ ሥራው ግንድ ይዞ መዞር ሳይሆን ኃይል ማመንጨት።

**ዓባይ እኔና አንተ ሳይሉን ቸር ሆነን**
**ፎከሩብን እንጂ ማን አመሰገነን!**
**በራሳችን ውሃ በረሳችን አፈር**
**ተዘባበቱብን ተመጠጠ ከንፈር!**

ዓባይ ለዘመናት ለኢትዮጵያ ምንም ሳይጠቅማት ግብጽንና ቅኝ ገዥ ሀገራትን ሲያወዳጅ ኖሯል። ግብጽን አበልጽጓል። ኢትዮጵያ ግን አልተመሰገነችም፤ እንዲያውም መሳለቂያና መዘባበቻ አደረጓት። በራሷ ውሃና አፈር መሳለቂያ ሆነች፤ በሌለችበት እንደፈለጋቸው ይፈራረሙበታል፤ ይወዳጁበታል። አቅም የላትም፣ አትገነባውም የሚል ንቀት መሆኑ ነው።

**ስንት ዘመን ቁጭት ስንት ዘመን ግጭት**
**ስንት ዓመት በጣሳ ስንት ዓመት በወጪት!**
**ፍሰስበትና በሀገርህ ሜዳ**
**የሚቆጣም ካለ ያበጠው ይፈንዳ!**

አሁን ተረቱም ፉከራውም ይበቃል፤ «ዓባይን በጭልፋ፣ ዓባይን በወጪት...» የሚሉ ተረትና ምሳሌዎች ወደ እውን ይቀየሩ። እነሆ ዓባይ ይገደብ እንደማለት ነው፤ «አትገድቡም» የሚል ካለም ኢትዮጵያውያን ያውቁበታል ለማለት ነው።

መቼም የዓባይ ነገር ከተነሳ ከወንዙ እኩል ስመ ገናና የሆነችው ድምጻዊት እጅጋየሁ ሽባባው (ጂጂ) በሁላችንም ልብ ውስጥ ናት። አንድ ለሙዚቃ ምንም ቅርበት የሌለው ሰው «እስኪ የአንድ ዘፋኝ ስም ተናገር» ቢባል «ጂጂ» ማለቱ አይቀርም። ጂጂ ከዓድዋ እና ከዓባይ እኩል ስሟ ይነሳል፤ ምክንያቱም ዓድዋንም ዓባይንም በብዙዎች ልብ ውስጥ እንዲሰርጹ አድርጋለች። መዝፈን ቢሉ ዝም ብሎ መዝፈን ሳይሆን ልብን ሰርስረው በሚገቡ ጥልቅ ስንኞች በመቀኘት ነው።

ጂጂ ለዓባይ የዘፈነችው ሊገደብ ነው ሲባል አይደለም፤ ማንም ባላሰበበት ወቅት ነው። እውነተኛ ጥበብም እንዲህ ነው፤ ቀድሞ ይተነብያል፤ የሌሎችን ዓይንና ልብ ይከፍታል። ጂጂ ዓባይን እንዲህ ስትለው ኖራለች።

**የማያረጅ ውበት የማያልቅ ቁንጅና**
**የማይደርቅ የማይነጥፍ ከዘመን የፀና**
**ከጥንት ከፅንስ አዳም ገና በፍጥረት**
**የፈሰሰ ውሃ ቀድሞ ከገነት**

ጂጂ የዓባይን ታሪካዊና ጥንታዊነት ነው የነገረችን። ዓባይ የማያረጅ ውበት መሆኑ ደግሞ ቀደም ሲል ያየናቸው የማህበረሰቡን ሥነ ልቦና የሚገልጹ ሥነ ቃሎችም ይነግሩናል። ከሰው ልጅ ፍጥረት ጋር ያለውን ቁርኝትና የሥልጣኔ አስጀማሪነቱን ትነግረናለች። «ግርማ ሞገስ የሀገር ፀጋ የሀገር ልብስ» እያለች የዓባይና የኢትዮጵያን ታሪካዊና ተፈጥሯዊ አንድነት ትነገረናለች።

**ዓባይ**
**የበረሃ ሲሳይ**
**ብነካው ተነኩ! አንቀጠቀጣቸው**
**መሆንህን ሳላውቅ ሥጋና ደማቸው!**

ይሄ እንግዲህ የዘመኑን ወቅታዊ ሁኔታ እንኳን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ዓባይ ለግብጻውያን ሥጋና ደማቸው ነው፤ ሲነካ ያንቀጠቅጣቸዋል። ለዚህም ነው በመገናኛ ብዙኃኖቻቸው የውሸት ዜና ሳይቀር የሚያሰራጩት። ግብጾች ምንም ዓይነት ውስጣዊ ችግር ቢያጋጥማቸው ከዓባይ ፕሮፖጋንዳ ዝንፍ አይሉም። እንዲህ ዓይነቱን እውነታ ነው የጂጂ ስንኞች የሚነግሩን።

**የሚበሉት ውሃ የሚጠጡት ውሃ**
**ዓባይ ለጋሲ ነው በዚያ በበረሃ**

ልብ በሉ እነዚህን ስንኞች! የሚበሉት ውሃ፤ የሚጠጡት ውሃ። እንዲህ ላወቁበት ውሃ የሚጠጣ ብቻ ሳይሆን የሚበላም ነው። ውሃን የምናውቀው እንደሚጠጣ ነው፤ በልማድ ውሃ ይበላል አንልም፤ በሳይንሳዊ ጥበብ ግን ውሃ ይበላል። ልክ እንደ ግብጽ ላወቀበት ማለት ነው። «ውሃ እንዴት ይበላል?» ሳይንሳዊ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስለኝም!

**ዓባይ ዓባይ**
**ዓባይ ወንዛወንዙ**
**ብዙ ነው መዘዙ!**

አዎ! የዓባይ ጉዳይ የባለቤቶች ብቻ አልሆነም። ከአውሮፓ እስከ እስያ፣ ከአፍሪካ እስከ አሜሪካ በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ እጃቸውን አስገብተውበታል። ሀገራት ተጣልተውበታል፤ ተወዳጅተውበታል። በዓለም አደባባይ ስሙ የተነሳባቸው አጋጣሚዎች ብቻ ናቸው። ዓባይ ጓዙም መዘዙም ብዙ ነው።

**ዓባይ የወንዝ ውሃ አትሆን እንደሰው!**
**ተራብን ተጠማን ተቸገርን ብለው**
**አንተ ወራጅ ውሃ ቢጠሩህ አትሰማ**
**ምን አስቀምጠሃል ከግብጾች ከተማ?**

ዓባይ ሰው አይደለም፤ እንዳደረጉት ይሆናል። ከገደቡት ይገደባል። በዚህ የጂጂ ስንኝ ውስጥ እንደ ሰው ታናግረዋለች። መልዕክቱ የሚነግረን ግን እኛም እንደ ግብጾች ማድረግ እንዳለብን ነው።

እጅጋየሁ ሽባባውም ሆነች ሌሎች ከያኒያን ዓባይን በጥበባቸው ገልጸዋል። ከእነዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የእረኞችና የገበሬዎች እንጉርጉሮዎች ቀድመው ዓባይን ተረድተውታል። ከዚህ የምንረደው ዓባይ ግብጽ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥም ሕይወት እንደነበር ነው። ከዚህ በኋላ ዓባይ የጥበብ ብቻ ሳይሆን የኃይልም ምንጭ ይሆናል!





# “በሚመጣው ዓመት መጨረሻ አስራ ሶስቱም ተርባይኖች ሥራ ይጀምራሉ”

*አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር)*

*የሕዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ሥራ አስፈፃሚ*

ምሕረት ሞገስ

በተለያዩ የዓለም ሴራዎች እና ከውስጥም ባሉ ሰፋፊ ችግሮች ሳቢያ ከድህነት ጋር ተጣብቃ የኖረችው ሀገር፤ ከመሠረቱ የሕዝቡን ሕይወት መቀየር የሚችል ብድር ይሰጠኝ በዓባይ ወንዝ ላይ ኃይል ማመንጫ ልገንባ ስትል ሴረኞቹ ከለከሉ። ርዳታቸው ሕዝቡ ቀሉ እየቀረጠመ እስከ ዓለም ፍፃሜ እንዲኖር በማሰብ ነውና፤ የማይጠቅም ርዳታ እና ብድር በመስጠት ኢትዮጵያ ዘመኗን በድህነት እንድትማቅቅ ምኞታቸው መሆኑን በተግባር አሳዩ። ይህ ከሆነ እነሆ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ተቆጠረ፤ ይህንን የተረዳ አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ እልህ ውስጥ ገብቶ ቆየ።

ለእዚህ ዘመን ከነዳጅ በላይ የሚያስፈልገው የኤሌክትሪክ ኃይል በመሆኑ እና ኢትዮጵያን ካለችበት ድህነት ለማላቀቅ ዋናው ጉዳይ ይህ ነው በሚል የወቅቱ መንግሥት በቀዳማይ ኃይለሥላሴ ዘመን የተዘጋጀውን የሕዳሴው ግድብን ለመገንባት ማቀዱን በ2003 ዓ.ም ይፋ አደረገ። የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በይፋ የመሠረት ድንጋይ አስቀመጡ። ዘመናትን በዕልህ ያሳለፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ በደስታ አበደ። ርዳታ እና ብድር ቢከለከልም በራሳችን አቅም እንገነባለን ሲል ቃል ገባ። ቃሉንም በተግባር አሳዩ።

እነሆ አሁን ይህ ሕልም የሚመስል ዕቅድ ተግባር ላይ ውሉ ፍሬ እንደሚያፈራ ታየ። አሁን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ሥራ ለመጀመር ጫፍ ደርሷል። ይህን መሠረት በማድረግ ከሕዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር) ጋር ያደረግነውን ቆይታ በሚከተለው መልኩ አቅርበንላችኋል መልካም ንባብ፡-



**አዲስ ዘመን፡- የዘንድሮውን መጋቢት 24 ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው?**

**ዶ/ር አረጋዊ፡-** ባለፉት 13 ዓመታት ብዙ ውጣ ውረዶች ነበሩ። ሕዝቡ ተነሳስቶ የልማት ሥራውን ለማገባደድ በቁርጠኝነት አስተዋፅኦ ሲያድግ ቆይቷል። በእነዚህ ዓመታት እስከ አስራ ዘጠኝ ቢሊየን ብር የሚጠጋ ገንዘብ አዋጥቷል፤ ከገንዘብ በተጨማሪ በጉልበት ሠርቷል። ከመደበኛው የዲፕሎማሲ ሥራ ጎን ለጎን የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ላይ ሀገር ቤትም ሆነ ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ብዙ ተንቀሳቅሷል። ይህ ራስን ለመለወጥ እና ሀገርን ለማልማት የሚያደርገው ጥረት መጨረሻ ላይ ግድቡን ለማጠናቀቅ አስችሎታል ማለት እንችላለን። የቀረው ጥቂት ብቻ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ይህም ቢሆን ግን ብዙ ግብዓትን የሚጠይቅ በመሆኑ፤ ቁርጠኝነቱን አሁንም መቀጠል አለበት።

ይህ የሕዳሴው ግድብ የቁጭት ልማት ነው። የሕዝቡ ቁጭት እና ቁርጠኝነት ከዳር ያደረሰው የሕዳሴው ግድብ የሚያስገኘው ጥቅም ሲታይ ደግሞ፤ ሕዝቡ የበለጠ የጋራ ልማት ምን ያህል እንደሚጠቅም በደንብ ያረጋግጣል። በዚህ በዓል ጽሕፈት ቤታችን ለሕዝቡ ምስጋና የሚያቀርብ ሲሆን፤ በቀጣይም በርታ ብሎ ከዚህ በኋላም ኢትዮጵያ የብዙ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ባለቤት በመሆኗ በእነዚህ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ላይም ተመሳሳይ ግድብ እንሰራለን። ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለጎረቤት ሀገራትም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማምረት መረባረብ አለበት የሚል ጥሪ እናቀርባለን።

**አዲስ ዘመን፡- የሕዳሴው ግድብ አሁን በምን ደረጃ ላይ ነው?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-** አሁን ያለበትን ደረጃ በተለያዩ ሚዲያዎች ሲገለጽ እንደነበር ይታወቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላም ማጣት ችግርም ሆነ የኑሮ ውድነትን እና ሌሎችም ብዙ ችግሮች ቢያጋጥሙትም ተቋቁሞ ያለማቋረጥ ባደረገው አስተዋፅኦ አሁን ወደ 95 በመቶ ግድቡ ተጠናቋል ማለት ይቻላል። የሲቪል ኢንጂነሪንግ ሥራዎች ለማለቅ እጅግ ተቃርበዋል። ስለዚህ አሁን 98 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ አካባቢ ደርሷል።

ነገር ግን ኤሌክትሪካል እና መካኒካል ሥራዎች ትንሽ የተወሰነ ጊዜ ይጠይቃሉ። በዚህ ዓመት ቴክኒካል ሥራዎቹን በማቀላጠፍ አምስቱ ተርባይኖች ሥራ ይጀምራሉ የሚል ዕቅድ ይዘናል፤ ይሳካልናል ብለን እናምናለን። በቀጣይ ዓመት ደግሞ ቀሪዎቹ ተርባይኖች ሥራ እንደሚጀምሩ ኢንጂነሮቹ ዕቅዳቸውን በሪፖርት መልክ አቅርበዋል። ስለዚህ በሚመጣው ዓመት መጨረሻ አስራ ሶስቱም ተርባይኖች ሥራ ይጀምራሉ የሚል ተስፋ አለን። ያ ማለት በግድቡ ኃይል የማመንጨት ሥራችን ሙሉ ለሙሉ ስኬታማ ሆነ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ በኋላስ የሕዝቡ ተሳትፎ ምን መምሰል አለበት ይላሉ?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-** የገንዘብ ተሳትፎ አሁንም አስፈላጊ ነው። በእውነቱ ሕዝቡ ገንዘብ ማዋጣቱን አላቋረጠም። አሁን ግድቡ ላይ እየተገኘ ያለው ውጤት መመዝገብ የቻለው አንድም ሕዝቡ ድጋፉን ባለማቋረጡ ነው። ግድቡ ‹‹ሕይወቴን ይቀይርልኛል፤ ከርዳታ እና ከብድር ውጭ የሆነ የዕድገት ፈለግ እያሳየኝ ነው። ከብዙ ጫና ነፃ ያወጣኛል፤ የኢኮኖሚ ነፃነቴን ያጎናፅፈኛል፤›› ብሎ ስላመነ አሁንም ሕዝቡ ድጋፉን ቀጥሎበታል።

ግድቡ የሕዝቡ አንድነት የሚጠናከርበት ከመሆን ባሻገር፤ የገንዘብም ሆነ የሀብት ማከማቸት ጥቅምንም አሳይቷል። አሁንም የቦንድ ግዢም ሆነ ርዳታው እየቀጠለ ነው። ለምሳሌ አንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ብር በዓመት ተሰብስቧል። በዚህ ስድስት ወር ደግሞ ካቀድነው በላይ እየተሰበሰበ ነው። ለምሳሌ በትንሹ በየጊዜው በ‹‹8100 A›› በስልክ ጥሪ በየወሩ ወደ 12 ሚሊየን ብር ይሰበሰባል። ይህ ገንዘብ ተጠራቅሞ ብዙ ይሆናል።

> **በቦንድ ግዢም ሆነ በስጦታ አስተዋፅኦ የማድረግ እንቅስቃሴው አሁንም ያለማቋረጥ እየቀጠለ ነው**

በቦንድ ግዢም ሆነ በስጦታ አስተዋፅኦ የማድረግ እንቅስቃሴው አሁንም ያለማቋረጥ እየቀጠለ ነው። የሚገርመው ሕዝቡ በብዙ ጫና ውስጥ ሆኖ ሳይቀር ለሕዳሴ ግድቡ ማዋጣቱን አላቋረጠም። ይህ በጣም አስደናቂ ነው። ስለዚህ ለቀጣይ ልማትም ሆነ ለእዚህ ግድብ መጠናቀቅ እና አዲስ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ለመድረስ ያለው ጉጉት እና ፍላጎት እንዲሁም ያለው ሀገራዊ ስሜት ትልቅ መሆኑን አይተናል። በጽሕፈት ቤታችን የሕዝቡ አስተዋፅኦ እጅግ የሚያስደስተን መሆኑን ለመግለፅ እወዳለሁ።

ግድቡ እስኪያልቅ ድረስ ሕዝቡ ተነስቷል። በዛ መንፈስ መቀጠል አለበት። ከዛ ቀጥሎ ግድቡን ማነፅ ቢያልቅም፤ ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችም አሉ። የአካባቢ ጥበቃ ሥራ አለ። አካባቢውን በአረንጓዴ ልማት መሸፈን ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። በአረንጓዴ ልማት መሸፈን ካልተቻለ ውሃው አፈሩን እየጠረገ ወደ ግድቡ ይገባና የግድቡን እድሜ ሊያሳጥረው ይችላል። ስለዚህ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የአካባቢ ጥበቃ ሥራው ላይ ጠንክሮ መሳተፍ የግድ ነው።

ሌላው የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ የመስመር ዝርጋታ እና የኃይል ማከማቻ ግንባታ ሥራ ነው። ኤሌክትሪክ በየገጠሩ መዳረስ አለበት። በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የገጠር አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያገኙ ዝርጋታው መከናወን አለበት።

ከዚህ በኋላ በዋነኛነት መሠረታዊ ሥራዎች የሚባሉት የአካባቢ ጥበቃ ሥራውን ማካሔድ እና የዝርጋታ ሥራውን ማቀላጠፍ ነው። እነዚህ ሥራዎች ተያያዥ ናቸው። ስለዚህ ግድቡ ተጠናቀቀ ሲባል ሥራው አለቀ ማለት አይደለም። ለእነዚህ ሥራዎች ሕዝቡ አብይ አስተዋፅኦ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ሌላው በዋናነት መዘንጋት የሌለበት ተፅዕኖዎች አሉ። የውጭውን ተፅዕኖ ለመከላከል ሕዝቡ አንድነቱን አጠናክሮ ማንኛውም የልማት ሥራ ሀገርን የሚጠቅም በመሆኑ የግድብ ግንባታም ሆነ የአረንጓዴ ልማት እንዲሁም ሌሎች ልማቶች እንዲፈፀሙ እና ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ግብፅ በተለያየ ጊዜ በተለያየ መልኩ የምታሳየው አቋም አለ። ስለግብፅ አቋም ምን ይላሉ?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-** ግብፆች ኢትዮጵያ ራሷን እንድትችል እና የተፈጥሮ ሀብቷን እንድትጠቀም አይፈልጉም። ይህ በግልፅ መታወቅ አለበት። ምክንያታቸው ኢትዮጵያውያን ውሃ እና አፈራቸውን በአግባቡ መጠቀም ከጀመሩ እነርሱ የሚጎዱ ይመስላቸዋል። ሌላው የለመዱትን ነገር እንደሚያጡ እያሰቡ ስጋት ውስጥ ናቸው። አፈሩንም ሆነ ውሃውን ያለምንም ጠያቂ እንደፈለጉ ከመጠቀማቸው ብዛት ‹‹ውሃው የእኛ ብቻ ነው›› እስከ ማለት

ወደ20ኛ ገጽ ዞሯል

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት

ልዩ እትም



# “በሚመጣው ዓመት መጨረሻ...

ከ19ኛው ገጽ የዞረ



**በራሳችን ዕውቀት፣ በራሳችን ጥረት፣ በራሳችን ጉልበት እና በራሳችን ገንዘብ ማደግ እንደምንችል አረጋግጠናል**

ደርሰዋል። ስለዚህ የቀኝ ግዛት አስተሳሰባቸው እና ስግብግብነታቸው አለቀቃቸውም።

በቅርቡ በተካሄደው ድርድርም የሶስትዮሽ ድርድር አንፈልግም ሲሉ እንደነበር ይታወሳል። ሌላ አካል መጨመር አለበት የሚል ሃሳብ እያቀረቡ ነው። ውሃው የራሳችን ሆኖ ሌላ ውሃው ላይ የማያገባው አካል ጣልቃ እንዲገባ መፈለጋቸው የሚገርም ነው። ውሃው 86 በመቶ የሚሆነው የሚነሳው ከኢትዮጵያ ነው። ያም ቢሆን እኛ ብቻችንን እንጠቀም አላልንም። አብረን እንጠቀም፤ አብረን እንልማ ብለናል። ‹‹አብረን ተባብረን ካለማን ከራሳችን አልፈን ለሌሎችም መትረፍ እንችላለን›› ብለን ብናስረዳቸውም አልገባ ብሏቸዋል። ከተጠናወታቸው የስስት አስተሳሰብ ሊወጡ አልቻሉም።

ግብፆች ሌሎች እነርሱን የሚደግፉ ኃይሎችን በማካተት ተፅዕኖ ለመፍጠር ይሞክራሉ። በዓለም ደረጃ እንደሚታወቀው ለታላቁ የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ ብድር እንዳታገኝ አድርገዋል። በርግጥ እነርሱ መጥፎ አስበው ይህንን ቢፈፅሙትም በአንድ በኩል ይህንን መፈፀማቸው ለእኛ ጥሩ ሆኗል። ምክንያቱም ራሳችን ተፍጨርጭረን በአፍሪካ ትልቁን በዓለም ደግሞ ትልቅ ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱ አስር ግድቦች መካከል አንዱን መሆን የሚችል ግድብ በራሳችን አቅም ገንብተናል። ይህ ለእኛ ከዚህ በፊት ያልሞከርነው እና ያላገኘነው ትልቅ ትምህርት ሰጪ ሆኗል።

በራሳችን ዕውቀት፣ በራሳችን ጥረት፣ በራሳችን ጉልበት እና በራሳችን ገንዘብ ማደግ እንደምንችል አረጋግጠናል። እነርሱ ክፉ ቢያስቡም እኛ መልካም ሆኗል። በርግጥ ግብፆች አሁንም ዝም አይሉም። ነገር ግን እንዲያውም በእዚህ ግድብ ላይ አስተዋፅኦ ቢያደርጉ፤ የምናደርገውን የአረንጓዴ ዘመቻን ቢደግፉ የተሻለ ዘላቂና ቀጣይ የሆነ ተጠቃሚ ይሆኑ ነበር። ተርባይኖቹ ውሃውን አያቆሙትም፤ ሥራቸው ኃይል አመንጭተው ማለፍ ነው። ይህ ገብቷቸው ቢተባበሩ ለእነርሱም ይጠቅማቸዋል። አሁንም በእኛ በኩል ያለው አቋም ተመሳሳይ ነው። ግብፆች የተለያዩ መንገዶችን እየተጠቀሙ አፍራሽ ሃሳባቸውን ከሚያራምዱ በወንድማማችነት አብሮ ስለማደግ ቢያስቡ ይሻላቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በተደጋጋሚ ከሚያነሷቸው አስገራሚ ሃሳቦች መካከል አንደኛው እኛ ገብተን የግድቡን ሁኔታ እንቆጣጠር የሚል ነው። እዚህ ላይ ምላሾት ምንድን ነው?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-**እነርሱማ ከዚህ የሚመነጨውን ውሃ የእኛ ነው እስከ ማለት የደረሱ ናቸው። ስለዚህ ውሃው የእኛ ነው ካሉ፤ ግድቡንም ገብተው ለመቆጣጠር ማሰባቸው አያስገርምም። ይህ ሃሳብ አሁን የጀመሩት ሃሳብ አይደለም። ድሮ ገና በ640 ዓ.ም የባህር በራችን አዶሊስ እያለ በአዶሊስ በኩል መጥተው ጦርነት ከፍተዋል። ጦርነቱን ያካሔዱበት ምክንያት በአዶሊስ በኩል ገብተው የዓባይን ምንጭ ለመቆጣጠር ተመኝተው ነበር። ነገር ግን ክፉኛ ሊረሱት በማይችሉበት መልኩ ተመተው ተሸንፈው ተመልሰዋል።

ከዛ ሽንፈታቸው በኋላ ግን ግብፆች አንዴ ከተሸነፉ በኋላ በቀጥታ ራሳቸው ለውጊያ አልመጡም። ነገር ግን በተዘዋዋሪ በተላላኪዎቻቸው አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ግርግር እንዲፈጠር፣ ሀገር እንድትተራመስ እና ገብተው ቁጥጥር እንዲደረግ ብዙ እየሠሩ ናቸው። አቅም አጥተው እንጂ ወረራም ከማካሔድ ወደኋላ አይሉም ነበር። ስለዚህ ሙሉ ለሙሉ ውሃውን ለመቆጣጠር ያላቸው ዕቅድ እስከ አሁን የባዕዳን አገዛዝ አስተሳሰብ እንደተጠናወታቸው መቀጠሉን የሚያሳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከግብፃች ወደ ራሳችን እንመለስ እና በርግጥ የሕዳሴው ግድብ ቱርፋቱ ምንድን ነው?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-** የእዚህ ግድብ ጥቅም ሲነሳ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሕይወት የሚነካ ነው። አንደኛ የሚያመነጨው ኃይል እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ያላገኙ ሰዎች ኤሌክትሪክ የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል። ገጠር ኤሌክትሪክ ከገባ ሕዝቡ ከጨለማ ይወጣል። የገጠር ሕዝብ ከጨለማ ከወጣ ቀን ብቻ ሳይሆን ማታም ሥራ መሥራት ይችላል። ለገጠሩ ሕዝብ ማረሻ እና ማጨጃን ጨምሮ ሌሎችም ቀን እና ሌሊት መሠራት ያለባቸውን ሥራዎች ለመሥራት ያስችላል።

የኤሌክትሪክ ኃይል በቅርብ መኖር መሬትን ለማልማትም ሆነ ሕዝብ የሚፈልገውን ቁሳቁስ ለማሟላት ያስችላል። የሥራ ዕድልም ይፈጠራል። ስለዚህ ጥቅሙ ሰው እየገባው ነው። የኤሌክትሪክ ኃይሉን ሽያጭ ላይ በማዋልም የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ያስችላል። እኛ ያላመረትናቸውን መድኃኒት እና ሌሎችም እጅግ ወሳኝ የሆኑ ምርቶችን እና የተለያዩ ግብዓቶችን የመሳሰሉ ከውጭ የሚገቡ ነገሮችን ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ የምናገኝበት ሁኔታ ይኖራል። የሚያስፈልገንን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ይረዳል ማለት፤ ራሳችንን ችለን የማንንም ርዳታ እና ብድር ሳንጠብቅ ማደግ እንችላለን ማለት ነው። ይህ በመላው ሕዝብ ላይ በጎ ተፅዕኖ አለው። ይህ ፕሮጀክት ትልቅ ነው በሚል በሁሉም የሚደገፈው፤ ለእዚህ ነው። አዲስ የኢኮኖሚ ግንባታ የራስን አቅም በነፃነት በመጠቀም ቀጣይነት ያለው ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በዓድዋ ድል ስመሳው አፍሪካውያን ሞዴል መሆን ችለናል። በተመሳሳይ መልኩ ከሕዳሴው ግድብ ጋር በተያያዘ ስሚመጣው ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሞዴል በመሆን በኩል የሚኖረን አስተዋፅኦ ምን ያህል ነው?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-** እስከ አሁን ድረስ በዓለም ተዘርግቶ ያለው የኢኮኖሚ መስተጋብር ድሮ ቀኝ ገዢዎች ባሰመሩት መሥመር ላይ የተመሠረተ ነው። ለታዳጊዎች እንሠራለን፤ እንደግፋለን ይላሉ፤ ነገር ግን ውሸት ነው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀምሮ ኢትዮጵያ ርዳታ እና ብድር ታገኛለች። ነገር ግን ከድህነት እና ከብድር ከርዳታ አልወጣችም። ለምን የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አለብን። ምክንያቱም የሚሰጡን ርዳታም ሆነ ብድር አንቆ የሚይዝ ገመድ አለው።

በኃያላኑ መንግሥታት ቤት ነፃ ምሳ የለም። ርዳታም ሆነ ብድር የሚሰጡን በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ለእነርሱ ብድር ወለድ እየከፈልን፤ ለርዳታቸውም እጅ እየነሳን እጃችን ተጠምዝዞ እንዲኖር እያደረገን ነው። ከዚህ ታግለን ነፃ መውጣት አለብን። የእዚህ ግድብ ታላቅነት የሚገለፀው በዚህ መልኩ ነው።

ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች በዚህ ገመድ የታሰሩ ናቸው። አፍሪካውያን የማናድገው ለእዚህ ነው። የባዕዳን አገዛዝ ከተወገደ በኋላ የሆነው ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎች ሀገሮች ነፃ ሀገር ቢባሉም የፖለቲካ ነፃነት እንጂ የኢኮኖሚ ነፃነት የላቸውም። ኢኮኖሚው የባዕድ አገዛዝ እንደነበረው በዛው ቀጥሏል። አሁንም በተዘዋዋሪ መንገድ ብዝበዛቸው ቀጥሏል። ጣሊያን ኢትዮጵያን እንዲገዛ እነርሱም ብዝበዛቸውን እንዲቀጥሉ መላው ቀኝ ገዢዎች ሲደግፏቸው ቆይተዋል። ቁጥጥራቸው እንዲቀጥል በዓለም ላይ ጦርነት አቅደው ነበር። ኢትዮጵያ ላይ የተካሔደው ዘመቻም ሆነ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ የሠሩት ሥራ ስኬታማ መሆን አልቻለም። ምክንያቱም ሕዝቡ በአንድነት ተሳትፎ፤ ዓድዋ ላይ ዘምቶ ጣሊያንን ድል መታ።

መሸነፋቸው ቀኝ ገዢዎችን በሙሉ በጣም አስቀይሟል። ነጮች ያንን ታሪክ ለመቀልበስ ብዙ ጥረት አድርገዋል። የአፍሪካ ሀገሮች ከዚህ ትምህርት ብዙ ወስደዋል። ታግለው አባርረዋል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን መርሳት የሌለብን የኢኮኖሚ ነፃነታቸውን ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ነፃነታችንን አልተጎናጸፍንም።

ስለዚህ ይህ ግድብ ያለ እነርሱ ዕርዳታ እና ብድር ተጠናቆ ፍሬ ሲያፈራ፤ ለአፍሪካውያን እና ለመላው ያላደጉ ሀገሮች በጣም ትልቅ ትምህርት ይሆናል። ሀገራት የፖለቲካ ነፃነታቸውን ማግኘትን በተመለከተ ከኢትዮጵያውያን ከዓድዋ እንደተማሩት የኢኮኖሚ ነፃነትን በተመለከተም፤ ከዚህ ግድብም ሊማሩ ይችላሉ። የኢኮኖሚ ነፃነታቸውንም በምን መልክ ሊጎናፀፉ እንደሚችሉ ያስባሉ።

እናም የሕዳሴው ግድብ እንድምታው አንድነትን ያጠናክራል። አንድ ሆነን ከተነሳን ያለንን ችግር በቀላሉ መፍታት እንችላለን የሚለውን አስተሳሰብ ያሰርፃል። ነገር ግን ከሕዳሴው ግድብ በተጨማሪ አሁንም ሆነ በቀጣይ በአንድነት ለመሥራት መነሳት አለብን። አንድ ሆነን ካልተነሳን ግን ችግሮቹ እንዳሉ ይቀጥላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የሕዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት የሕዳሴው ግድብ እንዲገነባ የተቋቋመ ነው። የሕዳሴው ግድብ ደግሞ ሲጠናቀቅ ከጫፍ ደርሷል። ከተጠናቀቀ እና አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ጽሕፈት ቤቱ ዕጣ ፈንታው ምንድን ነው?**

**አረጋዊ ዶ/ር፡-** ይህ ጽሕፈት ቤት ለሕዳሴው ግድብ መገንባት የተቋቋመ ቢሆንም፤ ግንባታው ካለቀ በኋላ ሥራው ምን ይሆናል የሚለው በብዙ ሰዎች ውስጥ ጥያቄ ነው። ነገር ግን ብዙ ሥራዎች አሉበት። ኢትዮጵያ ከዘጠኝ ያላነሱ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አሏት። እነዛ ወንዞች ልጓም አላደረግንባቸውም፤ እንዲሁ እየፈሰሱ ነው። ስለዚህ እነዛ ላይም ትላልቅ የሕዳሴ ግድብን የሚያክሉ ወይም ተመሳሳይ ግድቦችን መሥራት እና ሀገር ማልማት ይጠበቅብናል። ስለዚህ አንዱ ትልቁ ሥራ ይህ ነው። ሌላው ከላይ እንደገለፅት ጽሕፈት ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ሥራንም ይሠራል።

አካባቢውን በደን ማልበስ ያለበለዚያ በደለል ምክንያት ግድቦቹ የሚኖራቸው አጭር ዕድሜ ነው። አካባቢዎቹ በደን ካልተሸፈኑ እና ወደ ግድቦች የሚገባው ውሃ ንፁህ ካልሆነ ደለል እየሞላ አገልግሎታቸው አጭር ይሆናል። ይህንን የመሳሰሉ ብዙ ሥራዎች ስላሉ ጽሕፈት ቤት እነዚህን ታሳቢ አድርጎ ዝግጅት እያደረገ ነው።

ተሞክሮዎችም ማሰባሰብ እና ወደ ሌላ የሥራ መስክ እና ወደ ሌላ ወንዞች ምልከታ እንዲደረግ የሚሠራበት ሁኔታ ይኖራል። አሁንም ለሚመለከታቸው አካላት እያሳሰበ ነው። በቅርቡ ከሥራ አስፈፃሚው አካል ጋር በነበረን ግንኙነት ይህ ነገር ተነስቶ ጥናት እንዲቀርብ አቅጣጫ ተሰጥቷል። ስለዚህ የጽሕፈት ቤቱ ሥራ እንዲሁ የሚቆም አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡-ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**ዶ/ር አረጋዊ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።



የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት

ልዩ ዕትም

# የግድቡን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች ስናስብ ...

**ወንድይራድ ሰይፈሚካኤል**



ኢትዮጵያ ተፈጥሮ ከለገሳት ሀብቷ እንዳትጠቀም ሲሸረቡ የኖሩት ሴራዎች በፅናት ታልፈው፣ «ኢትዮጵያውያን የውጭ ርዳታ ካላገኙ በስተቀር ግዙፉን ግድብ አይገነቡትም...» የሚሉት የንቀት ሃሜቶች ነጭ ውሸት መሆናቸው ተረጋግጦ፣ በዘር፣ በእምነትና በፖለቲካ ልዩነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን በግድቡ ጉዳይ ግን ልዩነት እንደሌላቸው አስመስክረው ... ኢትዮጵያውያን በዓባይ ወንዝ ላይ የጀመሩትን የዓባይ ግድብ ግንባታ ለማጠናቀቅ ከመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሰዋል፡፡

ምርታማነትን በመጨመር ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት ለማስመዝገብ አስፈላጊ ከሆኑ መሠረታዊ ግብዓቶች መካከል አንዱ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት አንዱ እንደመሆኑ የግድቡ ግንባታ ወደ ማጠናቀቂያ ምዕራፍ መሸጋገር ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ የአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብት በዓመት ስምንት በመቶ አማካይ እድገት እንዲያስመዘግብ ከተፈለገ፣ የሀገሪቱ ኃይል የማመንጨት አቅም በአማካይ 12 በመቶ ማደግ አለበት፤ ይህ ማለት ለአንድ በመቶ የምጣኔ ሀብት እድገት አንድ ነጥብ አምስት በመቶ የኃይል አቅርቦት እድገት ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ የኃይል አቅርቦት ሁሉንም የምጣኔ ሀብት ዘርፎች ማንቀሳቀሻ ሞተርና የምርታማነት መጨመሪያ መሳሪያ ነው፡፡

ዝቅተኛ ኃይል ተጠቅሞ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ያስመዘገበ ሀገር በየትኛውም የዓለም አካባቢ የለም፡፡ ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸው የዓለም ቁንጮ የሆኑት ሀገራት ከፍተኛ ኃይል የተጠቀሙና ለኃይል አቅርቦትም ብዙ ገንዘብ ያፈሰሱ ናቸው፡፡ አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት በሌለበት፣ አስተማማኝ የምጣኔ ሀብት እድገት ሊመዘገብ አይችልምና፡፡

የኃይል አቅርቦት እስትንፋሱ ከሆነው የአምራች ዘርፉ በተጨማሪ፣ የግብርናና የአገልግሎት ዘርፎችም አብዛኛው ተግባራቸው ያለ ኃይል (መብራት) የሚታሰብ አይደለም፡፡ በአጭሩ ኃይል የኢኮኖሚ ሞተር፣ የደም ስር፣ እስትንፋስና የህልውና ዋስትና ነው፤ የኃይል አቅርቦት ከሌለ፣ ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አይኖርም፡፡

ኢትዮጵያም የኃይል አቅርቦትን አስተማማኝ አድርጋ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እድገት በማስመዝገብ ብልጽግናን እውን ለማድረግ፣ የአስተማማኝ ኃይል አቅርቦት ዋስትና እንደሚሆን የሚጠበቀውን የዓባይ ግድብን በዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ትገኛለች፡፡ ሀገሪቱ ከድህነትና ኋላቀርነት ተላቅቃ ፈጣንና ዘላቂ ኢኮኖሚ በመገንባት ሕዝቦቿን ከረሀብና ከልመና ለማላቀቅ በምታደርገው ጥረት የተፈጥሮ ሀብቷን አሟጣ መጠቀም ግድ ይላታል። ከግድቡ ጀርባ ያለው መሠረታዊ ሐቅም ይኸው ነው።

ግድቡ በኢትዮጵያውያን ሀብት የሚገነባ የብሔራዊ ኩራት መገለጫ የሆነ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክት ነው፡፡ ግንባታው ሲጠናቀቅ የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብትና ፖለቲካዊ የመደራደር አቅም በእጅጉ እንደሚያሳድገው ይጠበቃል፡፡ ከሚያስገኘው የኃይል አቅርቦት ጥቅም በተጨማሪ፤ በግንባታ ሂደት ላይ ሆኖ ያስገኛቸው የሥራ እድል ፈጠራ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የቁጠባ መጠን እድገትና ሌሎች ጥቅሞች በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ ቀላል የማይባል አበርክቶ አላቸው፡፡

ግድቡ የኃይል አቅርቦትን በማሳደግ ለምጣኔ ሀብታዊ መነቃቃትና እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በየቤቱና በየፋብሪካዎች የሚያጋጥመውን የኃይል መቆራረጥ በማስወገድ የሥራ እንቅስቃሴን ይጨምራል፡፡ የኃይል አቅርቦት ተደራሽ ያልሆኑ አካባቢዎች የኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ እነዚህ አካባቢዎች ማገዶ እንጨትንና አካባቢን በካይ የሆኑ የኃይል ምንጮችን እየቀነሱ ወደ ታዳሽና ለአካባቢ ምቹ ወደሆኑ የኃይል አማራጮች እንዲሸጋገሩ ያስችላቸዋል፡፡ ይህም ጊዜን በመቆጠብ እንዲሁም በሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የሚያስችል እድል በመፍጠር፣ በተለይም የሴቶችን የሥራ ጫና በመቀነስ፣ ምርታማነትን ይጨምራል፡፡ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙና ተጨማሪ ምርት፣ የሥራ እድልና ገቢ እንዲገኝም ያደርጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለጎረቤት ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ያስችላል፡፡ ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ኃይል ስታቀርብ ከሀገራቱ የምታገኛቸው ሌሎች ጥቅሞች ስለሚኖሩ ግድቡ ሰጥቶ የመቀበል ፖሊሲን ያሳድጋል፤ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ከሌሎቹ ሀገራት ሌሎች ጥቅሞችን በተሻለ ዋጋና መተማመን ለማግኘት ያስችላል፤ የኢትዮጵያን የመደራደር አቅም ያሳድጋል፡፡ የምጣኔ ሀብት ትስስርን ያጠናክራል፤ አንዱ ሀገር የሌላውን ሀገር ጥቅሞች እንዲያከብር ያደርጋል፡፡

በተለይም ግድቡ በኃይል እጥረት ለሚሰቃየው የአምራች ዘርፉ ሁነኛ መፍትሔ በመሆን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ለማሳካት ለተያዘው እቅድ ዓይነተኛ ግብዓት ይሆናል፡፡ በኃይል እጥረት ምክንያት ከአቅም በታች እያመረቱ ያሉና ሥራ ያቆሙ አምራቾች የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያገኙና በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ፣ የሥራ እድልና ገቢ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ይህም የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ተጨባጭ ለውጥ እንዲያስመዘግብ ያስችላል፡፡

የግድቡ መገንባት ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ይጋብዛል፡፡ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አንድ መስፈርት አድርገው የሚመለከቱት የሀገሪቱን የኃይል አቅርቦት አስተማማኝነት ነው፡፡ ግድቡ የኃይል አቅርቦትን አስተማማኝ ስለሚያደርግ ተወዳዳሪ የሆነ ዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ በመሳብ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (Foreign Direct Investment-FDI) ሌላ የውጭ ምንዛሪ ይዞ ይመጣል፤ ወደ ሀገሪቱ የመጣው የውጭ ምንዛሪ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ኤክስፖርት ሲደረግ ሌላ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛል፡፡

**የግድቡ መገንባት**

**ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ይጋብዛል። ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አንድ መስፈርት አድርገው የሚመለከቱት የሀገሪቱን የኃይል አቅርቦት አስተማማኝነት ነው። ግድቡ የኃይል አቅርቦትን አስተማማኝ ስለሚያደርግ ተወዳዳሪ የሆነ ዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ በመሳብ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል**

ከዚህ በተጨማሪም ግድቡ ሲጠናቀቅ በግድቡ አካባቢ ብዙ ደሴቶች ስለሚፈጠሩ አዳዲስ የቱሪዝም አቅሞች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ የንግድና ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴዎች ተጨማሪ የሥራ እድልና ገቢ ይፈጥራሉ፡፡ ይህም የግድቡ ኢኮኖሚያዊ ሚናዎች ተደራራቢ ውጤቶችን የሚያስገኙ በረከቶች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡


በግድቡ ምጣኔ ሀብታዊ ሚና ላይ ያተኮረው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማኅበር (Ethiopian Economics Association) ጥናት እንደሚያሳየው፣ ግድቡ በኢትዮጵያ በዝቅተኛ የትምህርትና የገቢ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ዜጎች ገቢያቸውን በዓመት በስምንት ነጥብ ስምንት በመቶ ያሳድጋል፡፡ ሱዳንና ግብጽም ከግድቡ ቀላል የማይባል የምጣኔ ሀብት ጥቅም እንደሚያገኙ የጥናቱ ውጤቶች ያሳያሉ፡፡ ይህም ግድቡን ለፍትሃዊና አካታች ጥቅም በአብነት ሊጠቀስ የሚችል ፕሮጀክት ያደርገዋል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በምጣኔ ሀብትና በፖለቲካ መስኮች የሚኖራትን ተፅዕኖ እንደሚሳድገው ይጠበቃል፡፡ የግድቡን ግንባታ በብርቱ የሚቃወሙ አካላት የተቃውሟቸው ዋናው ምክንያታቸውም ይህ ተጠባቂ ተፅዕኖ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ግድቡ የኢትዮጵያን የመደራደር አቅም በማሳደግ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖዋ እንዲጨምር ዓይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

ግድቡ ለኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ግንኙነት ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለኢትዮጵያ አዎንታዊ ምስል የሚያሰጥ ፕሮጀክት ነው፡፡ የግድቡ ግንባታ በርካታ መሰናክሎችን አልፎ የተከናወነ በመሆኑ ሌሎች ሀገራትና ተቋማት በሀገሪቱ ፕሮጀክት የማስፈፀም አቅም ላይ መተማመን እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህ አዎንታዊ ምስል ደግሞ ለጋሽ ሀገራትና ተቋማት ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን ድጋፍና ብድር እንዲያሳድጉ ያግዛል፡፡ ለጋሾች ለኢትዮጵያ የልማት ፕሮጀክቶች በሚሰጧቸው ድጋፎች ውጤታማነት ላይ እምነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ የውጭ ባለሀብቶችም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በኢንቨስትመንት ለመሰማራት መተማመኛ ይሆናቸዋል፡፡

የግድቡ መጠናቀቅ በኢኮኖሚው ዘርፍ ብቻ ከላይ የተዘረዘሩትን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ያስገኛልናል ማለት ነው፤ በርግጥ ከግድቡ የምናገኛቸው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ የግድቡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ደግሞ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎችን የሚያስገኙ በረከቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የግድቡ ግንባታ ዋነኛ ዓላማ ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ በመሆኑ ግድቡ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት የማይተካ ሚና እንደሚኖረው የታወቀ ነው፡፡ እንግዲህ የግድቡን ግንባታ መጠናቀቅ ስናስብ ተዘርዝረው የማያልቁትን እነዚህን ጥቅሞቹ የሚያስገኙልንን ዓይነተ ብዙ በረከቶችን በተስፋና በጉጉት እንጠብቃለን፡፡ በተስፋ እንደጀመርነው በፅናት ጨረስነው!





# የሕብረተሰብ ተሳትፎ መገለጫ

**ሰሚራ በርሀ**

የሁሉም ኢትዮጵያውያን ዐሻራ እያረፈበት ያለው የዓባይ ግድብ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ ግንባታው ከተጀመረ እነሆ 13 ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ ከምሥረታው ጊዜ አንስቶ አሁን ለደረሰበት የማጠናቀቂያ ምዕራፍ የሕብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ እንደመሆኑ፣ በተለያዩ ሕዝባዊ ንቅናቄዎች፣ ማህበራዊ ተሳትፎዎች ወዘተ፣ ለግንባታው ሀብት ሲሰበሰብ ቆይቷል፤ እየተሰበሰበም ይገኛል፡፡

ገቢ ለማሰባሰብ ይደረጉ ከነበሩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ዋነኛው የቦንድ ሽያጭ ነው፡፡ ይህ የቦንድ ሽያጭ በተለያየ መጠን ዜጎች እንደየአቅማቸው በስማቸው በመግዛት ዐሻራቸውን እንዲያሳርፉ ትልቅ መነሳሳትን ፈጥሯል፡፡

በዚህም እንቅስቃሴ ሠራተኞች በመሥሪያ ቤታቸው፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው፣ ወላጆች ከራሳቸው አልፎ በልጆቻቸው ስም፣ በተለያየ መጠን ቦንዱን በመግዛት በፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ ዐሻራቸውን አሳርፈዋል፡፡ የመከላከያና የፖሊስ አባላት፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በየተቋሞቻቸው ስም እንዲሁም በውጭ ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቦንድ በመግዛት ዐሻራቸውን አኑረዋል፡፡ በዚህ ቦንድ ግዥ ያልተሳተፈ ኢትዮጵያዊ የለም ማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ነው ድጋፉ የተደረገው፡፡

ግድቡ በተጀመረበት ዓመት ግንባታው በአምስት ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል ግምት ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም፣ በተለያዩ ምክንያቶች በጊዜው መጠናቀቅ ሳይችል ቀርቶ የተለያዩ ሂደቶችን እያለፈ አሁን በ13ኛ ዓመቱ ከማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ደርሷል፡፡

የግድቡ ግንባታ የተለያዩ ምዕራፎችን አልፏል፤ እያንዳንዳቸው ምዕራፎች የግንባታው ስኬቶች በመሆናቸው ኢትዮጵያውያንም በልዩ ሁኔታ እያሰቧቸው እዚህ ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ ዘንድሮ ደግሞ በማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ በመገኘት ታላቅ የምስራች ይዞ መጥቷል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ሊጠናቀቅ የጥቂት ወራት ግምት ብቻ ተሰጥቶት ግንባታው 95 በመቶ መድረሱ ይፋ ተደርጓል፡፡ በዛሬው እለትም ግንባታው የተጀመረበትና የመሠረት ድንጋይ የተጣለበትን 13ኛ ዓመት « በሕብረት ችለናል » በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ሁነቶች እየተከበረ ይገኛል፡፡ 13ኛ ዓመቱን አስመልክቶ የገቢ ማሰባሰብ ሥራ እንደሚካሄድ ተጠቁሟል፡፡

ለግድቡ ግንባታ ገቢ ለማሰባሰብ ተብለው በሚዘጋጁት ሁነቶች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ በየዓመቱ ዜጎች በተለያየ አማራጭ ቦንድ እንዲገዙ የማድረጉ እንቅስቃሴዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ዜጎች የግድቡን ግንባታ ቦንድ በመግዛትና በመሳሰሉት ድጋፍ እያደረጉ ቆይተዋል፤ በአሁኑ ወቅትም እያደረጉ ናቸው፡፡ በርካታ ዜጎች የግንባታው መሠረት ከተጣለ አንስቶ ሳያቋርጡ በየጊዜው ቦንድ እየገዙ ይገኛሉ፡፡

ወይዘሮ ነጃት ሽረፋ አሁን ላይ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እየተዘዋወሩ አነስተኛ ሥራዎችን እየሠሩ ኑሯቸውን የሚመሩ የአራት ልጆች እናት ናቸው፡፡ ወይዘሮ ነጃት የዓባይ ውሃ ለዘመናት ወደሌሎች ሀገራት የሚፈስ እና እነዚህ ሀገራትም ይህን ውሃ ተጠቅመው መሬታቸውን ሲያለሙ ኢትዮጵያና ዜጎቿ ግን በተለያዩ ችግሮች ውስጥ መኖራቸው ሁሌም የሚያሳስባቸው እና የሚቆጫቸው ጉዳይ ነበር፡፡

«ዓባይ ሊገደብ የመሠረት ድንጋይ መቀመጡን ስሰማ ደስታዬ ወደር አልነበረውም» የሚሉት ወይዘሮ ነጃት፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ ለተከታታይ ሰባት ዓመት በእርሳቸው እና በልጆቻቸው ስም እያደረጉ ቦንድ ገዝተዋል፡፡ «ባገኘሁት አጋጣሚ በልጆቼ ስም ቦንድ ገዝቻለሁ፡፡ ግድቡ ሲጀመር የሁለት ልጆች እናት ነበርኩ አሁን የአራት ልጆች እናት ስሆን በልጆቼ ስም ቦንድ እየገዛሁ በእነርሱ ስም ዐሻራ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ» የሚሉት ወይዘሮ ነጃት፣ ልጆቻቸውም በትምህርት ቤታቸው ሲጠየቁ እንዲገዙ ያበረታቷቸዋል፡፡

በየጊዜው ይህን ቦንድ የሚገዙት ተርፏቸው ወይም በእቅዳቸው ውስጥ አካተውት ሳይሆን፣ ግድቡ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሁሉ እንዲገነባው እና እንዲጠቀምበት ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡ ወይዘሮ ነጃትም በየሰው ቤቱ ተዟዙረው በሚሰሩት ሥራ ከሚያገኙት ገንዘብ ላይ ቀንሰው በአቅማቸው ቦንድ የሚገዙትም ለዚሁ ነው፡፡

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ የሁሉም ኢትዮጵያውያን በመሆኑ ሁሉም የአቅሙን የራሱን ድርሻ የሚወጣበት ነው፡፡ ወይዘሮ ነጃትም ከ200 ብር ጀምረው ለተከታታይ ሰባት ዓመታት ያላቸውን እያወጡ ለግድቡ እዚህ መድረስ የራሳቸውን ዐሻራ አሳርፈዋል፡፡

ግድቡ ሲጠናቀቅም ብዙ ተስፋ እንዳላቸው ጠቅሰው፣ «ልጆቻችን ከስደት ተላቀው በሀገራቸው ኮርተው ሰርተው መግባት እንዲችሉ፣ መጪው ትውልድም ሰፊ የሥራ እድል አግኝቶ የሚኖርበት እንደሚሆን የኔም የሌሎች ኢትዮጵያውን ተስፋ ነው ብዬ አምናለሁ» ብለዋል፡፡

ሌላኛዋ በቦንድ ግዢው የሚጠቀሱት ባለትዳር እና የሁለት ልጆች እናት የሆኑት ወይዘሮ ምናሉ አረጋይ ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት ነዋሪ ናቸው፡፡ የሚተዳደሩት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የጽዳት ሥራ በመሥራት ነው፡፡

«የግድቡ ግንባታ መጀመር በጣም አስደስቶኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ ውሃ ያለ ጥቅም መፍሰሱ በጣም ይቆጨኝ ነበር፡፡ ከዚያም ደግሞ በዓባይ ውሃ ግብጽ ትልቋ ተጠቃሚ ስለመሆኗ መረጃ ነበረኝ» የሚሉት ወይዘሮ ምናሉ፣ የዓባይ ውሃ በሀገራችን ጥቅም ላይ ቢውል ብዙ እናቶች በቂ የኃይል አቅርቦት ይኖራቸዋል፤ ኑሯቸው ይሻሻላል የሚል ተስፋ አላቸው፡፡

የዓባይ ግድብ ግንባታ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ የአካባቢያቸው ሰዎችም በቦንድ ግዥው እንዲሳተፉ የማስተባበር ሥራን በቅርበት መሠራታቸውንም ይገልጻሉ፡፡ ወይዘሮ ምናሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የገዙት የአንድ ሺህ ብር ቦንድ ነበር፡፡ «አሁን ግንባታው እየተገባደደ ስለሆነ የመጨረሻውን ዐሻራዬን ማሳረፍ እፈልጋለሁ» የሚሉት ወይዘሮ ምናሉ፤ የዓባይ ግድብ የማይመነዘር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀብት ነው ይላሉ፡፡ ለልጆቻቸውም ይህንን ትልቅ ታሪክ ባሳረፉት ዐሻራ አማካይነት እንደሚያስተላልፉ ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ ምናሉ ቦንዱን የሚገዙት ለዚሁ ተብለው በሚዘጋጁ የማስተባበሪያ ድንኳኖች እንዲሁም ቦንድ ወደሚገኝበት ባንክ ጭምር በመሄድ ነው፡፡ ያለማቋረጥ ቦንድ በመግዛት የሚታወቁት ወይዘሮ ምናሉ፣ በአንድ ወቅት ወዳጃቸው ቦንድ እየተሸጠ እንደሆነ ሲነግሯቸው እንዳያመልጠኝ ብለው የአንድ መቶ ብር ቦንድ በስማቸው እንዲገዙላቸው ያደረጉበትን ገጠመኝንም አስታውሰዋል፡፡

ወይዘሮ ምናሉ ለተከታታይ ስምንት ዓመታት ይሄን ያደረጉት ደመወዛቸውን ጠብቀው፣ ቤታቸውን ልጆቻቸውንም እያስተዳደሩ ነው፡፡ በአነስተኛ ደመወዝ የሚኖሩ ቢሆንም፣ ለግድቡ የምሰስተው የለኝም ብለው ነው ድጋፍ የሚያደርጉት፡፡ ድጋፉ ማድረጉ የኔም ኃላፊነት ጭምር ነው በማለት ነው በዚህ ልክ የተሳተፉት፡፡

አሁን ግድቡ ሊጠናቀቅ ጥቂት ወራት እንደቀሩት የተገለጸ መሆኑን ጠቅሰው፣ በእነዚህ ጊዜያት በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ አሁንም ቦንድ እንደሚገዙ አስታውቀዋል፡፡ ሌሎችም በግዥው እንዲሳተፉ ጥሪ አስተላልፈዋል ፡፡

በከሰል ንግድ የሚተዳደሩት የሻሸመኔ ከተማ ነዋሪዋ ወይዘሮ አሰለፈች ጸጋዬ ሌላዋ ቦንድ በተደጋጋሚ በመግዛት የሚታወቁ ናቸው፡፡ ወይዘሮ አሰለፈች ለግድቡ ግንባታ ከ100 ጊዜ በላይ ቦንድ በመግዛት ነው የሚታወቁት፡፡

ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት ፌስታል፣ ከሰልና የመሳሰሉትን በመሸጥ እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ አሰለፈች፤ «የዓባይ ግድብ የእኔ ነው» ሲሉ ይናገራሉ፤ ከሚያገኙት ገቢ እየቀነሱ ቦንድ እንደሚገዙም ገልጸዋል፡፡

የግድቡ ግንባታ በተጀመረበት የመጀመሪያ ዓመት ብቻ የአንድ ሺ ብር ቦንድ መግዛታቸውን አስታውሰው፣ እስከ አሁን ያለማቋረጥ እየገዙ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ የዘንድሮውን ሳይጨምር እስከ አሁን የ640 ሺ ብር ቦንድ ገዝተዋል፡፡ 120 ሺ ብር ደግሞ በልገሳ ሰጥተዋል፡፡

«ካለኝ አነስተኛ ገቢ የዓባይ ግድብ ቦንድ እንድገዛ ያነሳሳኝ የሀገር ፍቅር ስሜት ነው» ሲሉም ጠቅሰው፣ «መኖር የሚቻለው ሀገር ስትለማና ስትኖር ነው» ብለዋል፡፡ እሳቸው ከሚያደርጉት የቦንድ ግዥና ለግሳ በተጨማሪ ሌሎች ሰዎችን በማነሳሳት በርካታ ቦንድ እንዲገዙ ማድረጋቸውንም አስታውቀዋል፡፡

ወይዘሮ አሰለፈች የግድቡ ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ ለመመልከት ሶስት ጊዜ ጉብኝት ማድጋቸውን ጠቅሰው፣ አሁን በደረሰበት የማጠናቀቂያ ምእራፍ ልዩ ደስታ እንደተሰማቸውም ገልጸዋል፡፡

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዘንድሮ የሚከበረውን የግድቡ ግንባታ የተጀመረበትን 13ኛ ዓመት አስመልክቶ በቅርቡ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ሕዝቡ ለግንባታው ቦንድ በመግዛትና በመሳሰሉት የሚያደርገው ተሳትፎ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ባለፉት 13 ዓመታት ከ18 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን በላይ ብር ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም በማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ይገኛል ያለው መግለጫው፣ ኃይል በማመንጨት ላይ ካሉት ሁለት ዩኒቶች በተጨማሪ ሌሎች ዩኒቶች ተጠናቀው በቅርቡ ኃይል ያመነጫሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ጽሕፈት ቤቱ የደረሰውን የስምንት ወራት ሪፖርት ዋቢ አድርጎ በመግለጫው ላይ እንዳስታወቀውም፤ በ2016 በጀት ዓመት ከሐምሌ 2015 ዓ.ም እስከ የካቲት 30/2016 ዓ.ም ድረስ 931 ሚሊዮን 984 ሺ 102 ብር ከሕብረተሰቡ ሊሰበሰብ ችሏል፡፡

ይህ ተሳትፎ ሀገራዊ በመሆኑ በግድቡ ላይ የራሳቸውን ዐሻራ ማሳረፍ ከፈለጉ በሌሎች የዓለማችን ክፍል ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎችም እንዲሁ በቦንድ ግዢ እና ስጦታ ባለፉት ስምንት ወራት አራት ሚሊዮን 614 ሺህ 884 ብር መሰብሰብ ተችሏል ፡፡

በየዓመቱ በዓሉን ለማክበር በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ዜጎች የግድቡን ግንባታ ሊያግዙ በሚችሉ የቦንድ ግዢ እና ስጦታ ፣ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የ8100 አጭር የጽሑፍ መልዕክት፣ በተለያዩ ሀብት ለማሰብሰብ ተብለው በተዘጋጁ ኹነቶች ገቢ የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል፡፡

የግድቡ ግንባታ የተጀመረበት 13ኛ ዓመት « በህብረት ችለናል! » በሚል መሪ ቃል በበለጠ ተሳትፎ እና የሀብት ማሰባሰብ ተግባራት ለማክበር ዝግጅት መደረጉን ጽሕፈት ቤቱ አስታውቋል፡፡ ከመጋቢት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በመላው ሀገሪቱ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ የቦንድ ሳምንት እንደሚካሄድ ጠቁሟል፡፡ በቦንድ ሳምንቱ 100 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ የታለመ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ሌሎችም ቦንድ የሚሸጡ የገንዘብ ተቋማት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዝግጅት ቦንድ ለመሸጥ መሰናዳቸውም በመግለጫው ላይ ተመልክቷል፡፡

የዓባይ ግድብ ግንባታ 13ኛ ዓመት



ልዩ እትም

# የስፖርቱ ዘርፍ ከዓባይ ግድብ ምን ይጠብቃል?

ቦጋለ አበበ

በርካታ የስፖርት አይነቶች በተለያዩ ሀገራት የሚፈጠሩት እንደ የአካባቢው መልክአ ምድር፣ እምቅ አቅም፣ ባህልና ልምድ ወዘተ መነሻ አድርገው ነው። እንደ አፍሪካ ባሉ ሀገራት ዘመናዊ ስፖርቶች የተዋወቁት ግን ከዚህ በተለየ መንገድ በብዛት ከቅኝ ግዛት ታሪክ በተገናኘ ነው። በኢትዮጵያም ዘመናዊ ስፖርቶች በብዛት የተዋወቁትና የተስፋፉት ከፋሽት ጣሊያን ወረራ እንዲሁም ከፈረንሳዮች ጋር በተገናኘ መሆኑን የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት የታደለች ሀገር ብትሆንም እንደ ሀገር የሚዘወተሩ የውሃ ስፖርት አይነቶች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ለማለት እንኳን የሚያስደፍሩ አይደሉም። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቀውና የሚዘወተረው የውሃ ስፖርት አይነት በተለያዩ ሆቴሎች በትንንሽ ገንዳዎች ውስጥ የሚከናወኑትና በኦሊምፒክ መድረኮች በኮታ የምንሳተፍባቸው ብቻ ናቸው። ለዚህ ደግሞ አንዱ ምክንያት ተደርጎ የሚቆጠረው በሌሎች ሀገራት የሚዘወተሩ የውሃ ስፖርቶች የሚፈልጉት ምቹ የውሃ አካል አለመኖር ሊሆን ይችላል። በበርካታ ሀገራት የውሃ ስፖርቶች አይነታቸው ቁጥር ስፍር የለውም። በውሃ አካላት ላይ እና ውስጥ ተከፋፍለው የሚካሄዱ የስፖርት አይነቶች ብቻ ተቆጥረው የሚያልቁ አይደሉም።

ከ250 ኪሎ ሜትር በላይ የሚንጣለለው የዓባይ ግድብ ሌላውን ትተን በውሃ አካላት ላይ የሚካሄዱ ነገር ግን በኢትዮጵያ ተሞክረው የማያውቁ በትንሹ ከሃያ የማያንሱ የውሃ ስፖርቶች እንዲፈጠሩ የማድረግ አቅም ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል። በበርካታ ሀገራት ከተለመደው የተለያዩ የጀልባ አይነቶች ውድድር አንስቶ በውሃ ውስጥና ላይ እስከሚከወኑ በርካታ ፉክክሮችን መፍጠር ይቻላል። ከዚህ ባሻገር ሌሎች በግልና በቡድን የሚካሄዱ የመዝናኛና የውድድር የውሃ ስፖርቶችን መፍጠር የሚቻልበት እድል ጠባብ እንደማይሆንም እንደ ዓባይ አይነት ግዙፍ ግድቦችን የገነቡ ሀገራትን ተሞክሮ መቅሰም ይቻላል።

በታላቁ የስፖርት መድረክ ኦሊምፒክ ውድድርና ፉክክር የሚካሄድባቸው የውሃ ስፖርቶች አንድና ሁለት አይደሉም። (swimming, diving, water polo, rowing, sailing, canoe flat-water, canoe slalom, artistic swimming, marathon swimming, and surfing)በስፋት የሚታወቁ የኦሊምፒክ ስፖርቶች ናቸው። የዓባይ ግድብ እነዚህ ስፖርቶች በኢትዮጵያ እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይቻለዋል። ከነዚህ ስፖርቶች የተወሰኑት ላይ እንኳን ጥናት አድርጎ በሂደት እንዲለመዱና እንዲዘወተሩ ማድረግ የሚቻልበት እድል ዝግ አይሆንም። ሁሉም ነገር መነሻ ይኖረዋል፣ መቼም በነዚህ ስፖርቶች አሁን ላይ በኦሊምፒክና በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ወርቅ የሚያፍሱ ሀገራት ዛሬ ለትልቅ ደረጃ የበቁት ከስፖርቶቹ ጋር አብረው ስለተፈጠሩ አይደለም። በሆኑ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ስፖርቶቹን ተላምደው፣ አጎልብተውና ሰርተውበት ነው ለትልቅ ደረጃ የበቁት። እኛም አዳዲስ ስፖርቶችን ከመሞከር የሚከለክለን ነገር የለም። ካለመሞከር መሞከር ሁሌም የተሻለ ነውና።

መጀመሪያ እኛ ካለን አቅምና ሁኔታዎች ተነስቶ በጥናቶች ላይ በመመርኮዝ ስፖርቶቹን ማስተዋወቅ፣ በሂደትም የማላመድና የማጎልበት ብሎም በፕሮፌሽናል ደረጃ ማምጣት በቀጣይ የሚታይ ጉዳይ ይሆናል።

እንደ አሜሪካ ያሉ ሀገራት በኦሊምፒክ በርካታ ወርቆችን ጠራርገው የሚወስዱት በውሃ ስፖርቶች ነው። አንድ የውሃ ዋና ተወዳዳሪ ብቻ ስምንት የወርቅ ሜዳሊያዎችን በአንድ ኦሊምፒክ ጠራርጎ የወሰደበት አጋጣሚ እዚህ ጋር ምሳሌ ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል። ያደጉት ሀገራት ያም አልበቃ ብሏቸው ዳንሶቻቸውን ጭምር በኦሊምፒክ ስፖርት እንዲካተቱ ማድረግ በኦሊምፒክ የሚሰበስቡትን የሜዳሊያ ቁጥር ለመጨመር ሌት ከቀን መስራት ከጀመሩ ሰነባብተዋል።

ኢትዮጵያ በሌሎች በተለመዱና ለረጅም ዓመታት በሚዘወተሩ ስፖርቶች ውጤታማነት ላይ ያልተመለሱ ብዙ ጥያቄዎች ቢኖሩም አዳዲስ ነገሮችን መሞከሩ ክፋት የለውም። በእጃችን ያሉትን ተጠቅመን ውጤታማ አልሆንም ማለት በአዳዲስ ነገሮች አይሳካልንም ማለት አይደለም። ማን ያውቃል ምናልባትም አብረውን ከከረሙት ይልቅ በአዳዲሶቹ ተክነን እንገኝ ይሆናል። ይህም በአትሌቲክስ፣ ቦክስ፣ ብስክሌት ወዘተ ብቻ ተወስኖ ዘመናትን የተሻገረውን የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ በሂደት ወደ ተጨማሪ ስፖርቶች ለማሳደግ በር ይከፍታል ብሎ ማሰቡ የዋህነት ሳይሆን ብልህነት ነው። ዛሬ ላይ ይህ ለብዙዎች ላይመስልና ላይዋጥ ይችላል፣ ነገር ግን ሁሉም ነገር ከትንሽ ተጀምሮ ወደ ትልቅ ደረጃ እንደሚያድግ ፈላስፋ መሆንን አይጠይቅም።

ይህን በሃሳብ ደረጃ ይዞ በባለሙያዎች ጥናት በማስደገፍ ነገን አርቆ መመልከት የሀገሪቱን ስፖርት በበላይነት ከሚመሩ አካላት ይጠበቃል።

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የስፖርት ትንሳኤ**

የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አሻራ ያረፈበት የዓባይ ግድብ ከ13 ዓመታት የግንባታ ሂደት በኋላ ዘንድሮ ይጠናቀቃል። ግድቡ የኢትዮጵያውያን የዘመናት ጥያቄ ሲመልስ የሚያመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ብቻ አይደለም። ብዙ በረከቶችንም ይዞ እንደሚመጣ ይጠበቃል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ከጨለማ ህይወት እንደሚያወጣው ሁሉ በጨለማ ለሚዳዘው የኢትዮጵያ ስፖርትም የራሱን በረከቶች ይዞ እንደሚመጣ ማሰቡና በዚያው ልክ መዘጋጀቱ ተገቢ ይሆናል።

ግድቡ ከኃይል ማመንጨት ባሻገር የሚኖረው ትልቅ ጥቅም ከቱሪዝም ጋር የተያያዘ እንደሚሆን ቀደም ሲል ተነግሯል። ለዚህም መንግሥት ምቹ የቱሪዝም መስህቦችን በአካባቢው ለመፍጠር የተለያዩ ንድፎችን እንደሚያዘጋጅ ይፋ አድርጎ ነበር። የግሉ ባለሀብትም አካባቢውን በማልማት ሊፈጥር የሚችለው ልዩ የቱሪዝም መዳረሻ በጉጉት የሚጠበቅ ይሆናል። ይህ ደግሞ ግድቡ ለተገነባበት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ለስፖርቱ እድገትና ለውጥ የራሱን ጠጠር እንደሚጥል መገመት አይከብድም።

የዓባይ ግድብ የተሠራበት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከዚህ ቀደምም ይሁን አሁን በዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ከፍ አድርገው በኩራት ያውለበለቡ በርካታ ከዋክብት የፈለቁበት ነው። ያምሆኖ ክልሉ አሁንም ድረስ በስፖርት መሠረተ ልማቶች እዚህ ግባ የሚባል ነገር የለውም። ይህም ክልሉ ያለውን የስፖርት እምቅ አቅም በተገቢውና በሚፈለገው መንገድ አውጥቶ እንዳይጠቀም አንዱ እንቅፋት እንደሆነ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ያምሆኖ አሁንም ድረስ ከዋክብት ስፖርተኞች በራሳቸው ልፋትና ጥረት ከዚያ ክልል ተነስተው በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ስም እየገነቡ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ከ31 ዓመታት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ስትመለስ የዋልያዎቹ ወሳኝ የአጥቂ መስመር ተጫዋች የነበረው ሳላዲን ሰዒድ መነሻው ከዚሁ ክልል አዋራማ ሜዳዎች ነበር።

ሳላዲን ወርቅ ከሚፈልቅበት ክልል ተነስቶ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ተፅእኖ በመፍጠር ስሙን በወርቅ ቀለም የፃፈ ኮከብ ነው። ሳላዲን በዚህ ደረጃ የሚጠቀስ በክልሉ ብሎም በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ይቀመጥ እንጂ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ዛሬም ድረስ በርካታ ሳላዲኖች መኖራቸውን ወደ ስፍራው ተጉዞ መንገድ ዳር በአዋራማ ሜዳዎች ኳስ ሲያንከባልሉ የሚውሉ ታዳጊዎችን መመልከት በቂ ነው።

ቤኒሻንጉል ጉሙዝ በእግር ኳስ ብቻ አይደለም የታደለው፣ በአትሌቲክሱም ከኦሊምፒክ እስከ ዓለም ቻምፒዮና ብሎም እስከ አፍሪካ ጨዋታዎች በወርቅ የደመቁ ከዋክብት የፈሩበት ስፍራ ነው። ኢትዮጵያ በ2016 የሪዮ ኦሊምፒክ አንድ የወርቅ ሜዳሊያ ብቻ ስታስመዘግብ በባዶ እጅ ከመመለስ የታደገችን ወርቃማዋ አትሌት አልማዝ አያና የዚሁ ክልል ፍሬ ነች። አልማዝ ሪዮ ኦሊምፒክ ላይ በ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ስታጠልቅ ለ23 ዓመታት ያልተደፈረውን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን በመንካት ጭምር ነው። በዚያው ኦሊምፒክ በ5ሺ ሜትር ሌላ ወርቅ ለማጥለቅ ተቃርባም ለጥቂት ነበር የብር ሜዳሊያ አሸናፊ የሆነችው። አልማዝ ከኦሊምፒክ ባሻገር ከዓለም ቻምፒዮና እስከ የግል የማራቶን ውድድሮች አሁንም ድረስ የኢትዮጵያ ኩራት የሆነች አትሌት ነች።

የአልማዝን ፋና ተከትላ በቅርቡ በአትሌቲክሱ ዓለም ገናና ስምና ዝና እየገነባች የምትገኘው ኮከብ አትሌት ፅጌ ዱጉማም ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ማህፀን የወጣች ናት። ይህች ጥቁር እንቁ ዘንድሮ ግላስጎው በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የ800 ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ በማስመዝገብ ክልሉ ከረጅም እስከ አጭር ርቀት ሩጫ ትልቅ አቅም እንዳለው በተግባር አረጋግጣለች። ከዚህ ታሪካዊ ድሏ ከሳምንታት በኋላ ወደ ጋና አክራ ፊቷን በመመለስ በአፍሪካ ጨዋታዎች በርቀቱ ያስመዘገበችው የወርቅ ሜዳሊያም የቅርብ ጊዜ ትውስታና ሌላ ታሪክ ነው።

ከእግር ኳስ እስከ አትሌቲክስ የጀገኑ እነዚህ አትሌቶች ከቤኒሻንጉል ክልል የተገኙት በራሳቸው ልፋትና ጥረት እንጂ በተመቻቸ መንገድ ተጉዘው አይደለም። ክልሉ አሁንም ድረስ ያለውን የስፖርት አቅም አውጥቶ እንዲጠቀም የሚያግዙ መሰረተ ልማቶች የሉትም። በግልም ይሁን በመንግስት ስር የሚገኙ የተለያዩ የስፖርት ክለቦችንም ፈልጎ ማግኘት አዳጋች ነው። በአሶሳ ከተማ የተጀመረው ትልቅ ስቴድየም እንኳን ለአስራ አምስት አመታት ግንባታው የት እንደደረሰ ዛሬም ድረስ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም።

ስፖርት የሚያድገውና የሚስፋፋው በከተማ ነው። ከተሞች ባደጉ ቁጥር የስፖርት መሰረተ ልማቶች ብሎም የስፖርት ክለቦች እያደጉ መሄዳቸው የማይታበይ ሀቅ ነው። የዓባይ ግድብ መጠናቀቅ እንደ ሀገር ይዞ የሚመጣው ፋይዳ እንዳለ ሁሉ ግድቡ የሚገኝበትን ክልል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ማሳደጉ እንደማይቀር ከወዲሁ መገመት አያዳግትም። ክልሉ አደገ፣ ከተሞች ተስፋፉ ማለት ደግሞ ስፖርቱም የእድገቱ ተቋዳሽ የሚሆንበት እድል ጠባብ አይደለም። ይህም በተመቻቹና ዘመናዊ በሆኑ መንገዶች ብዙ ሳላዲን ሰኢዶችን፣ በርካታ አልማዝ አያናዎችን ማፍራት የማይቻልበት ምክንያት እንደማይኖር ከተስፋም የዘለለ ትርጉም ይኖረዋል።